# ጦቢያ

ከአፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ልቦለድ

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ጦቢያ

ይህች ልብ ወለድ ታሪክ

ዘብሔረ ዘጌ

ይህች መጽሐፍ
በመጀመሪያ 1900 ዓ.ም. በሮማ ከተማ ታተመ።

መጀመሪያ በ፲፱፻፲፱ ዓ.ም. ድሬዳዋ ታተመ።
እንደገና በ፲፱፻፵፫፣ በ፲፱፻፷፣ በ፲፱፻፷፩፣ በ፲፱፻፷፬ ዓ.ም.
እንደገና በ፻፼ ዓ.ም. ታተመ።
እንደገና በ፪፻፻፪ ታተመ

## መግለጫ

የጽሑፍ ቅርስ የህዝቡን ትምህርታዊ ርምጃ እጅግ ለማፋጠን ስለሚገፋፋው የዓለም ህዝቦች አብዝተው ሲሠሩበት ይታያል የጽሑፍ ቅርሶች መጀመሪያ ከተጻፉበት ቋንቋ ወደ ልዩ ልዩ ልሳኖች እየተመለሱ አገልግሎታቸው በብዙ አህጉር ላይ ውጤቱን ማሳየት ይዟል።

የጽሁፍ ቅርሶችን ሰብስቦ ማባዛትና በስራ ላይ ማዋል ዛሬ የተወጠነ አዲስ ነገር አይደለም ስለዚህ በአተራረካቸው በአገላለጻቸውና በአስተያየታቸው ምዘናቸው ለስራ የሚጠቅሙንን ጥንታዊያን መጻሕፍት ለአገልግሎት እንደሚስማሙን አቃንተን እናባዛና ከስራ ላይ እናውላቸዋለን። በተነገረው መሰረት ከቆዩን መጻህፍት ውስጥ ጦቢያን አስቀድመን በማቃናት አዘጋጅተናታል።

## ጦቢያ በመጠኑ የተዘጋጀችበት መልክ፡-

ሀ - በዚች መጽሐፍ ውስጥ በአሁኑ ዘመን ደብዘዝ ብለው የሚታዩ አንዳንድ ቃላት ደራሲዋ በአዘጋጁት ጊዜ የነበረውን ስሜት እንዳይቀንሱ በማለት ለንባብ እንዲስማሙ ተስተካክለው እንዳሉ ተጽፈዋል።

ለ - መጽሐፊቱ በአገላለጽ ድርብርብ ቃላትን ስለምታበዛ ያረፍተ ነገሮቹ እጥረት ለአሳብ ቦይነት እንዲመች በማለት መሰረቱን አልለቀቀም።

ሐ - መጽሐፊቱን የማቃናቱ ተግባር የተፈጸመው በፊደላት በሐረጎችና በአረፍተ ነገሮች አሰካክ ስምምነት ላይ ነው። ነገር ግን የቆየውን የአጻጻፍ ስልት ላለማፍረስ እርማቱ መጠነኛ ነው።

መ - ጦቢያ ከደራሲዋ የተዘጋጀችበት መልክ በቀጥታ በመሃይምን አነጋገር ሆኖ አልፎ አልፎ የምሁራን አገላለጽና አንዳንድ የአገር ቤት ጥንታውያን ቃላት በመጠኑ ይዛለች። ስለዚህ የልዩ ልዩ ጠቅላይ ግዛትና አውራጆች ተማሪዎች ያለመምህር ርዳታ አንብበው ይጠቀሙባት ዘንድ በየሐረጋቸውና በየአረፍተ ነገራቸው ውስጥ የያዙትን ፍቺ በቀላሉ የሚሰጡ ቃላት መግለጮች ተደርገውላቸው በመጠኑ ተዘጋጅተዋል ቃላቱም ከመጽሐፉ በስተመጨረሻ ይገኛሉ።

## ልብ ወለድ ታሪክ

ደግ አድራጊ አበደረ፤ ክፉ አድራጊ ተገደረ።
ለጋሥ ቢለግሥ አበደረ እንጂ አልሰጠም።

አራት ተሸራ ወንጌል መሰበክ በተጀመረ ዘመን አረመኔው ከፍ ሲል ክርስቲያኑ ዝቅ ይል ነበር። በዚሁ ዘመን አረማውያን በብዛታቸውና በጉልበታቸው እየተመኩ ክርስቲያኑን እያደጋደጉ ከድንበር እየተሻገሩ አገሩን ያጠቁት ይዘርፉት ያቃጥሉትና ይመደምዱት ነበር።

ክርስቲያን የተባለውን ሁሉ የገደሉትን ገድለው የማረኩትን እንደባሪያ ይሸጡት ወይም ከቤታቸው ጥኑ ጥኑ ሥራ ያሠሩት ነበር። የክርስቲያኑም ወገን የዚያን ጊዜ ምንም በቁጥር ካረመኔው ቢያንስ ሃይማኖቱ እንዲከበር አገሩ እንዳይፈር ከድንበሩ ላይ ጠንክሮ ሲዋጋ ይኖር ነበር። ድሉ ግን አንድ ጊዜ ለክርስቲያኑ አንድ ጊዜም ላረመኔው ሲሆን ይኖር ነበር። ነገር ግን ከነዚህም ከነዚያም ወገን ከቶ ዕርቅ የሚፈልግ አንድም ሰው አልነበረም ብቻ በየጊዜውና በየወሩ በያመቱ ሲዋጉ ሲፋተኑ ሲተራረዱ ሲተላለቁ ይኖሩ ነበር።

እንደዚሁ ሁሉ አንድ ጊዜ አረመኔው አንደልማድ የክርስቲያኑን አገር ሊዘርፍ ሊገፍ ሰውንም ሊገድል፣ ሊሰልብ፣ ሊማርክ፣ ሊሸጥ መጣ በተባለ ጊዜ የክርስቲያኑ ንጉሥ ተፋጥኖ ጦሩን ባዋጁ አስከትቶ ባራት ደጃዝማቾች እግር አሳዝዞ “ሂድ ተዋጋ” ብሎ ሰደደ። ይኸውም ጦር ገሥግሦ ሂዶ አረመኔው ከድንበሩ እንዳይዘል አድርጎ ጠንክሮ ተዋጋ። ነገር ግን ያረመኔው ጦር ተዚያ ከክርስቲያኑ አሥር እጥፍ ይሆን ነበረና ክርስቲያኑ ድል ሆነ። ከነዚያ ከሄዱት ካራቱ ደጃዝማቾች ሦስቱ ከውጊያው ላይ ሞቱ። አንደኛው ግን ተያዘ። ሰዉም ሁሉ ከዚያው ላይ እንደጉድ እየተሳመጠ፣ እየተናነቀና እየተራኮተ ሞተ፤ አለቀ። የቀረውም ጥቂት ሰው ተማረከ። አንድ እንኳ ለዘር ወዳገሩ ሸሽቶ ያመለጠ ሰው አልተገኘም።

አረመኔው ግን ከድሉ በኋላ እንደፎከረው ገብቶ አገሩን ሁሉ ዘርፎ አጥፍቶ ከብቱንና ምርኮውን ይዞ ወደ አገሩ ተመለሰ።

ይኸ ወሬ በያገሩ ተዘራና ሁሉም በየዘመዱ መሞትና መማረክ ይላቀስ ፊቱን ይነጭ ጠጉሩን ይቆረጥ ጀመር። የክርስቲያኑ ንጉሥም የጦሩን ማለቅ የሦስቱንም ደጃዝማቾች መሞት ያራተኛውንም ደጃዝማች መታሰር ያገሩንም መዘረፍና መጥፋት በሰማ ወዲያው በሐዘንና በድንጋጤ ታሞ ከጥቂት ቀን በኋላ አለቀኑ ተቀሠፈ፣ ሞተ። የክርስቲያኑም አገር ባንድ ጊዜ ንጉሥ አጣ ገዢ ጠፋበት አገሩም ምድረ በዳ ሆነ።

ያ ተማርኮ የቀረው ደጃዝማችም አረመኔው ወዳገሩ እንደተመለሰ በማረከው እጅ ተሸጠ። ማራኪው ሰው ግን ሲማርከውም ሲሸጠውም ትልቅ ሰው መሆኑን ሳያውቅ እንዲያው እንደማንም ሰው ነው የሸጠው።

ያንኑ መከረኛ ደጃዝማች የገዛ አረመኔ ግን ቁመቱን ዛላው አምሮ ባየው ጊዜ "ማለፊያ ብርቱ ባሪያ አገኘሁ" ሲል ደስ አለውና ብርቱ ብርቱ ሥራ እያዘዘ እንደ ለጓሚ ሣር ያሳጭደው፡ እንደቋሚ እንጨት ያስፈልጠው እንደጎረዶማን ድንኳን ያስጭነው ተራዳም ያሸከመው ጀመር። እርሱ ግን ያልለመደው ነገር ነውና ከዚህ ሁሉ ስራ አንድ የሚሆንለት ነገር አጣ። ሣር ልጨድ ቢል የለሰለሰው የጨዋ ልጅ እጁ እንደሸንኩርት ተላጠ። ብርጭቆ ብርሌ ይጨብጥበት በነበረው ጣቱ ምሳር ቢጨብጥበት ጉብር አወጣ፤ ይህም ሆነ ያም ሆነ ያው የጥንት ደጃዝማች /የነበረው/ የዛሬው ባሪያ አዲሱ ጌታው እንዳይቆጣው ምናልባትም ባልተወለደ አንጀቱ እንዳይገርፈው እየተገጠጠ ሥራውን "አልሁህ አልሁህ" ይል ጀመር። ነገር ግን ያኮረሰው እጁ ጭራሹን ተሞሸለቀ። ተራዳ የሚሸከምበት ጫንቃውና አጉርቦ የነበረው ሁሉ ተገሸለጠና የማይሆንለት ሆነ። ጌታው ግን ለሥራው የለገመ መስሎት ይቆጣውና ለመግረፍ ያንገራግረው ጀመር። ይኸው አዲስ ገብ ባሪያ ግን "እንግዲህ የምታደርገውን አድርግ እንጂ ተችሎኝ የምሠራልህ ነገር አላገኝም" አለና ጫንቃውንም እጁንም አሳየው።

ያም አረመኔ ጌታው ባየው ጊዜ እውነትም መሥራት እንዳይሆንለት አየና "የጨዋ ልጅ ይሆን?" ብሎ ጠረጠረ። ከዚህም የተነሣ የማረከውን ሰው "የሸጥኸልኝ ባሪያ ስትማርከው ምን ለብሶ አገኘኸው?" ብሎ ጠየቀ። ያም ሰው "ብዙ ጌጥ ነበረው፤ ገፍፌ ብሸጠው ብዙ ወርቅ አወጣልኝ" አለና ነገረው። ይህን አዲስ ወሬ በሰማ ጊዜ ያ የገዛው አረመኔ ደስ አለው። ደጃዝማቹም /አዲሱ ባሪያም/ ትልቅ ሰው መሆኑን፣ ያ የገዛው አረመኔ ዐወቀና መቼም ሥራው ካልጠቀመኝ ብሎ ገንዘብ ያተርፍበት ዘንድ ፈለገ።

ከዚህ በኋላ ጠራና "አንተ ካፊር እኔ ተማረከህ ሰው ብዙ ገንዘብ አፍስሼ ገዛሁህ፣ አሁን የፈቀደኝን ብሠራህ ይቻለኛል፤ ነገር ግን ታሳዝነኛለህ። አሁንም ወደ ዘመዶችህ ላክና እልፍ ወቄት ወርቅ አስመጥተህ ስጠኝና አገርህ እንድትሄድ እለቅሃለሁ" ብሎ ነገረው። ያ ደጃዝማች ግን እንኳን አገሩ ጠፍቶ ንጉሡ ሙቶ ከብቱ ተዘርፎ በሬው ላሙ ተነድቶ ይቅርና ይኸም ባይሆን ታገሩ በጌትነቱ ሳለ ለጀግና መስጠት፣ ለድኃ መርጠብ፣ ለተራብ ማብላት፣ ለታረዘ ማልበስ እንጂ

ገንዘቡን ወደ ኋላ ማድረግ ለነገ ማለት አያውቅም ነበርና “የምከፍለውም የለኝ፣ ድኃ ነኝ፣ እንደ ወደድህ አድርገኝ” ብሎ መለሰለት።

የዚሁ ደጃዝማች ሎሌዎች ሁሉ አብረውት ሲዋጉ ከዚያው ከፊቱ አልቀዋል፤ ንጉሡም ሙቷል፤ አንድ ደጋፊ አንድ ተስፋ ታገኑ አልነበረም። ብቻ ተቤቱ ሚስቱና መንታ የተወለዱ አንድ ወንድን አንድ ሴት ልጆች ነበሩት። እነዚሁ ልጆች በዚያን ጊዜ አስራ ስድስት ዓመት ሆኗቸው ነበር። ታለባበሳቸው በቀር ወንዱም ገና ጢም አላቀነቀነም ነበርና ምንም የሚለያዩበት ነገር አልነበረም።

ለልጆቹና ለሚስቱ ፊት እርሱን ሞተ ብለው አረድዋቸው፤ እርሱ ግን ምርኮኛ ነው የነበር፤ ኋላም ታንዱ ወዳንዱ ሲል ይኸው አባታቸው ተሸጦ ኖሮ፣ ያው የገዛው አረመኔ “እልፍ ወቄት ወርቅ አምጣና ልልቀቅህ አለው” ሲባል ወሬው ደረሰላቸው። ምንም ባለመሞቱ ደስ ቢላቸው ወዲህም እንደባሪያ በመሸጡ ወዲህም ሰጥተው የሚያስለቅቁበት ገንዘብ በማጣታቸው እንደገና ይላቀሱ ጀመር። ንጉሡ ሙቶ አገር ጠፍቶ እነርሱ ለራሳቸው ደኽይተው ከወዴት ገንዘብ ይገኝ! ምን ሰጥተው ያድኑት! እንዲያው መላቀስ እንዲያው መጨነቅ ብቻ ሆነባቸው። ልጅየው ዋሕድ “ልሂድና ባባቴ ፈንታ እኔው ባሪያ ልሁንና አባቴ አገሩ እንዲመለስ ላድርግ” ቢል እናቲቱ ያው አረመኔ ሁለቱንም ይዞ ያስቀርብኛል ብላ ፈርታ አልለቀው አለች። በመጨረሻው ግን እናቲቱና እነዚያ መንቶች፤ ዋሕድና ጦቢያ፣ አውጥተው አውርደው፣ ወንዱ ልጅዋ ዋሕድ ለጌታ አድሮ ደመወዙን እያመጣ ሊያጠራቅም፣ ሴቲቱ ጦቢያ ግን እንጨት ለቅማ ውኃ ቀድታ የሚበሉትን እያሰናዳች ልታቀርብ ቤተ ሰቡ ለሎሌው ለገረዱ የሚሰጡት ገንዘብ የለምና ሊያሰናብቷቸው አሰቡና ተማከሩ።

በእውነቱ የሞያ ተፈትሎ ሎሌነት ተቀጥሮ ደመወዝ ተቀብሎ እልፍ ወቄት ወርቅ ለማጠራቀም ተረት ነው። ነገር ግን ምን ያድርጉ የቀራቸው ነገር ይኸ ብቻ ነው ሌላ የሚቻላቸው ነገር አልነበረም። ከዚህ ወዲያ እናቲቱ ቶሎ ቶሎ ትፈትል ጀመር። ዋሕድም እየዞረ የሚያድርለት ጌታ ይፈልግ ጀመር። ጦቢያም እያንጎራጎረች እንጨቷን ትለቅም ጀመር። ምግባቸውም ቅጠል ብቻ ሆነ። የምግባቸው ነገር በጦቢያ በኩል ተከተተ። እርስዋ አሉማውን አህል ገቡን ማገጡን ትሰበስባለች። ኦሞጨም አይቀር እንዲህ እንዲህ ያለውን ሥራ ሥሩን ቅጠላ ቅጠሉን እያጠራቀመች እያበሰለች አቅርባ፣ አንድነት ተጠራቅመው ልጆቹ አባታቸውን እናቲቱም ባሏን እያሰቡና እየተከዙ መበላላት ሆነ። በማግሥቱም ሁሉም እየሥራቸው ይሠማራሉ።

አንድ ቀን ወንዱ ልጅ ዋሕድ ገና ሥራን ለማግኘት ሲጠይቅና ሲያጠያይቅ ታንድ ትልቅ ከተማ ደረሰ። ከዚያ ከተማ ዳር ተመስክ ላይ መደብሩን መትቶ ወገኑን አሥማርቶ የሠፈረ ነጋዴ አየና አስቀድሞ ወሬውን ከእርሱ ለማግኘት ቀረበ፤ ቀጥሎም ያ መደብር የምን ነጋዴ እንደሆነና ወዴትስ ሂያጅ እንደሆነ ወገን ጠባቂውን ጠየቀ። እረኛውም "ሠፈሩ ያንድ ትልቅ ነጋዴ ነው፤ ይኸው ነጋዴ የሚነግድባቸው ወረቶች ዝባድ፣ የዝኆን ጥርስና ቡና ናቸው። አሁን የሚሄደው ወደ ምስር ነው" አለና አወራለት። ዋሕድም "እግዚአብሔር ይስጥህ" አለና ሲያቆም፤ "ጫኝ ሎሌ ቢያገኝ ያስገባ ይሆን" አለና ጠየቀው። ከብት ጠባቂውም ቶሎ ብሎ "እንዲህ ታልህስ ተጎረዶማኖቹ መካከል ንዳድ በሽታ ገብቶ ታመውበት የሚነሣበቱ ጊዜ ዘግይቶበት ተጨንቋል። እንዳይነሣ ጫኝ አጣ፤ አሁን ቢቸግረው "እጥፍ ደመወዝ እሰጣለሁና ጎረዶማን ፈልጉልኝ" እያለ ይፈልጋል፣ ያስፈልጋል። ከብቱም እንደምታየው እልቅ የለውም" አለና ነገረው። በዚህ ጊዜ ደስ አለውና ቸኩሎ ደኅና ዋል እንኳ አላለውም፤ ወደመደብሩ ይሮጥ ጀመር። ከሠፈሩ እንደደረሰ ዋናውን ድንኳን በትልቅነቱ ዐወቀና ቀርቦ አጋፋሪውን "ጫኝ እሆን ብዬ መጥቻለሁና ለጌታው ንገርልኝ" አለው።

አጋፋሪው ግን ያለባበሱንም ያለሳለሱንም ያነጋገሩንም ነገር አየና የማይመስለው ሆነ፤ ነገር ግን ለሁሉም ነገር አጋፋሪ ነው፤ አልነግርም ይል ዘንድ አይቻለውምና የጌታውንም ጫኝ ማጣት ያውቅ ስለነበር በግዱ ገብቶ ለጌታው "ጫኝ እሆናለሁ የሚል አንድ ደኅና ጎበዝ መጥቷል" ብሎ ነገረው። ባለቤቱም ደህና ጎበዝ መጥቷልን በሰማ ጊዜ አጋፋሪውን ተቆጣና፤ "ደህና ጎበዝ መጥቷል የምትለኝ የታመመ ጎበዝ ስፈልግ አይተኸኝ ኑሯልን? የታመመማ ተቤቴስ ተርፎኝ የለም፣ እንደምታየው" አለና አፈፍ ብሎ ቸኩሎ አጋፋሪው ግን "ኧረ ደኅና ጎበዝ ማለቴ ለጭነት የተገባ ሰውም አይመስልም ማለቴ ነበር" ብሎ ሊናገር ሲል ባለቤቱ ጊዜ ሳይሰጠው ርምጃውን ቀጠለ። አጋፋሪውም ኧረን ባፉ እንዳንጠለጠለ ከኋላ ከኋላው ተከተለ። ባለቤቱ ግን ተድንኳኑ ደጃፍ እንደ ደረሰ ወዲያና ወዲህ ቢያይ ተዚያ ማለፊያ ገና ወጣት ልጅ፣ ተዋሕድ በቀር ሌላ ለጎረዶማንነት የተገባ ሰው ከደጁ አጣ። ቀጥሎም ወደ በረኛው ዞሮ "ለጫኝነት የመጣው ሰው ወዴት ነው?" አለና ጠየቀ። ገና በረኛው ሳይመልስ ዋሕድ እጅ ነሣና "ጌታዬ እኔ ነኝ፤ ይፈቅዱ እንደሆን እርስዎን ለመከተልና ለርስዎ ጎረዶማን ለመሆን መጥቻለሁና ይፍቀዱልኝ" አለ። ባለቤቱ ግን ዋሕድን ተግር እስከ ጥፍሩ ከራሱ እስከ ጠጉሩ አመሳቅሎ አየውና ደንቆት "እንዴታ! ጎረዶማን እንዲህ ኑሮ! ጫኝ እንዲህ ነው እንጂ! ምንኛውን" እያለ ይጉተመተም ገባ። ዋሕድም ነገሩን እንደናቀበትና እንዳልተቀበለው ባየ ጊዜ "ጌታው

ከወፍራም አባያ የቀና ኮሳሳ በሬ አብልጦ ያርሳል። እንደዚሁም ለጋነቴን አይተው ካልናቁኝ ጭነት አይቸግረኝ” አለው።

ሀብታሙ ነጋዴ ግን እንዲህ ያለ ቃል ከዚህ ሕፃን ከዋሕድ ሲወጣ በሰማ ጊዜ ውቃቢው ወደደውና “ምነው እንዳንተ ያለ የደኅና ሰው ልጅ ተማዕረጉ ወጥቶ ጫኝነት ይመኛል? ንግግርህ ያማረ፣ አለባበስህ የተዋበ ሥራህ የጌታ ውቃቢህም ሁለንተናህም የጌታ፣ እንዴት የገንዘብ ስስት አድሮብህ ይህን ዓይነት ተግባር ትመርጣለህ?” ብሎ ጠየቀው። ዋሕድ ግን ዝም ብሎ ሰምቶ ሲጨርስ “ጌታዬ ኧረ የገንዘብ ስስት አድሮብኝ አይደል፣ የኔን መከራና፣ የኔን አይቶ ማጣት ሰምተው ቢሆን ኖሮ ባልፈረዱብኝም ነበር፤” አለ። ባለቤቱም አንሥቶ “እስቲ ዋሕድን ንገረኝ፣ ሰው ያላዩን አይቶ ይፈርዳል እንጂ የውስጡን ያውቅ ዘንድ አይቻለውም፤ ስለዚህ እኔም ሳላውቅ አጥፍቼ ይሆናልና ንገረኝ” አለው። ቀጥሎም ያው ሀብታም “እስኪ ለሁሉም ነገር በቅሎዬን ጫንልኝና ወደ ውጭ እንሂድ” አለው። ዋሕድም ባንድ አፍታ በቅሎውን ጫነለትና ሁለቱም አብረው ወጡ። ከድንኳኑ ጥቂት እንደራቁ ባለቤቱ “በል እስቲ የተከፋህበትን ነገር አጫውተኝ” ሲል ፈቀደለት።

ዋሕድም ግራ ክንዱን ባለቤቱ ከተቀመጠባት በቅሎ ከደጎራዩ ላይ ጣል አድርጎ በግሩ እየተከተለ ጌትዮው እያስገረ “የደኅና ሰው ዘር ያሉኝም እውነትዎን ነው፤ የደጃዝማች ልጅ ነኝ፤ በማዕረግና በጌትነት እኖር ነበር። ነገር ግን እርስዎም እንደሚያውቁት አረመኔ አገራችንን ለማጥፋት መጣ በተባለ ጊዜ ንጉሣችን ባዋጅ አስከትቶ ባራት ደጃዝማቾች አግር አሳዝዞ ‘ተዋጋ’ ብሎ ጦሩን ሰደደ። ከነዚያ ካራት ደጃዝማቾች አንዱ የእኔ አባት ነበረ። አረመኔዎቹና ክርስቲያኖቹ በተዋጉ ጊዜ እግዚአብሔር ሳይል ጊዜ ድሉ ያረመኔዎች ሆነ። ከሰዉም የሞተው ሞተ የተማረከውም ተማርኮ ተሸጠ። ካራቱ ደጃዝማቾችም ሶስቱ ከጦርነቱ ላይ ሞቱ። የእኔ አባት ግን ተማርኮ እንደባሪያ ተሸጠ፤ አሁን ግን ያ የገዛው አረመኔ ገና ጌታ ሳይሆን አይቀርም ብሎ ቀለሙን አይቶ ጠርጥሮ ‘እልፍ ወቄት ወርቅ አምጣና ልልቀቅህ’ አለው የሚል ወሬ ደረሰልን። ይህን ወሬ በሰማን ጊዜ በናቴም በእኅቴም በኔም እጅግ የመረረ ሐዘን ደረሰብን። አምጣ ያለውን ገንዘብ ሰደን እንዳናስለቅቀው ይህን ያህል ወርቅ ከኛችን የለም። ደግሞም አባቴ፤ ጥንቱንም ቢሆን መስጠት መለገሥ ያውቅ ነበር እንጂ ገንዘብ መቆጠብ አያውቅም ነበርና ገንዘብ ከወዴት እናግኝ? አሁን ንጉሡ ሰጥቶ እንዳያስፈታው እንደሚያውቁት በሐዘን ሞተ። አገር ጠፍቶ ሰዉ አልቆ ከብቱ ተነድቶ ከምሩ ተቃጥሎ ገንዘብ ከወዴት ይገኝ?

አሁን ቅጡ ቢጠፋን እህቴ ቅጠል እያበሰለች እንበላለን። እናቴ የሙያ እየፈተለች እኔ ሎሌነት ገብቼ ገንዘብ አጠራቅመን ተቀን ብዛት አባቴን ለማስለቀቅ ተስፋ አድርገን ይኸው እንደሚያዩኝ ለጌታ አዳር መጣሁ። እኔንስ ደስ ይለኝ የነበር እኔው ባባቴ ሥፍራ ተተክቼ እኔው ባሪያ ሆኜ አባቴ ወደ አገሩ እንዲመለስ ማድረግ ነበር። አባቴ እጅግ አሣምሮ በመንከባከብ ተጩንቆ አሳደገኝ። እኔም በዚህ ጊዜ ስለእርሱ ባሪያ ሆኜ ወረታውን ብከፍል ደስታዬ ነበር። ነገር ግን እናቴ “ባባትህ መከራ ሳለቅስ አንተ ደግሞ ሂደህ ታባትህ ጋር ባሪያ ሆነህ ትቀርና በመከራ ላይ መከራ ይጨምርብኛል” ብላ እንዳልሄድ ከለከለችኝ፤ በቁስም አስገዘተችኝ። አሁንም ይኸውልዎ ጌታዬ ከዚህ ያደረሰኝ የሰው ሎሌነት ያሰኘኝ ይኸ ነው ነገሩ፤ አይፍረዱብኝ” ሲል ነገሩን ጨረሰ።

ሀብታሙ ነጋዴም እያዘነ የዋሕድን ታሪክ አስተውሎ አዳመጠና ሲጨርስ “እኔ ጉዳይ አለብኝና ወደ ድንኳኔ እመለሳለሁ፤ አንተም ወደ ቤትህ ተመለስ፣ እግዚአብሔር ይሁንህ” አለና፣ ነጋዴ መቼም ለምናልባት ገንዘብ ከእጁ አይለይምና ይዞት የነበረውን ገንዘብ እስከ ከረጢቱ ተጁ ጣለለት። ሳይለያዩ በፊት ግን ያው ሀብታም ዋሕድን “ያባትህ ስም ማነው? የገዛውስ አረመኔ ስም ማን ይባላል? ያለበት አገርስ ወዴት ነው?” ብሎ ጠየቀ። ዋሕድም ያንን ከረጢት ወርቅ እንደሞላበት፣ በእጁ እንደያዘ ደስ ብሎት ከንፈሩም እየተንቀጠቀጠ አንደበቱም እየተርበተበተ ያባቱን ስም እስከቦታውና እስከ ምልክቱ ነገረውና፣ ሁለቱም ተለያይተው እየሰፈራቸው ሄዱ።

ዋሕድ ግን ያላሰበውን ሲሳይ ድንገት በማግኘቱ እጅግ ደስ አለውና እንኳን የዚያን የለጋስ ስምና አገር ለመጠየቅ “እግዚአብሔር ይስጥህ” ለማለት አላደረሰውም፤ እንዲያው ወደ ቤቱ ከነፈ።

ነገር ግን ከዚያ ለጋሥ ሰው ፊት የተቀበለውን ለማየትና ለመቁጠር አፍሮ አላየውም ነበርና ወዲያው እንደተለያዩ አንድ የሚሸሽግበት ቁጥቋጦ መሳይ ባየ ጊዜ ዋሕድ የከረጢቱን ወርቅ ቶሎ ከሸማው ላይ ዘረገፈና ቢቆጥር ፵ ወቄት አገኘበት። በዚህ ጊዜ ይልቁንም በደስታው ላይ ደስታ ተጨመረለትና እየፈነደቀ ሲሮጥ ከቤቱ ገባና ለናቱና ለእኅቱ ወርቁን ሆጭ አደረገላቸው፤ ነገሩንም ነገራቸው።

እናቱም እኅቱም ነገሩን ሰምተው የነጋዴውን ደግነትና የተሸጠውን ሰዋቸውንም መለቀቅ ባሰቡ ጊዜ በደስታም ይሁን በሀዘን በንባ ይታነቁ ጀመር። ሀብታሙ ነጋዴ ጥንቱንም ዋሕድን “በቅሎዬን ጫኝልኝና ተከተለኝ ማለቱ ድንገት የሚረጥቡት ሰው እንደሆነ ለመርጠብ ምክንያት እንዲሆነው፤ ለተቀባዩም

ሳያገለግል አለሰበብ መቀበሉ ውርደት እንዳይሆንበት ብሎ ነበር። ሁሉም ይኸው የተገኘው ገንዘብ ያ አረመኔ ለመልቀቂያ አምጣ ታለው ወርቅ አይደርስምና በጎደለው ለመሙላት እናቲቱም ጦቢያም ዋሕድም እንደፊተኛው እያሳባቸው ገቡ። ሁሉም እየተግበራቸው ይውሉና ማታ ማታ ያን ቅጠላቅጠላቸውን ለመብላት ይሰበሰባሉ።

አንድ ቀን ግን ማታ ምድር፣ ጦቢያ ቅጠሉን አብስላ ሰባብቃ ከምንቸቱ ወደ ቆሬው ዘርግፋ እንደልማዳቸው ሶስቱም ቀርበው ሲበላሉ የዚያን ነጋዴ ነገር እያደነቁ ወዲያውም “ይኸ ገንዘብ መቼ ተጠራቅሞልን፤ መቼ ገንዘቡን ሰድደን መቼ ተፈትቶ ካባታችን ጋር ዓይን ላይን እንተያይ ይሆን! ገና ነውና ነገሩ!» እያሉ እየናፈቁ በየጊዜው ምግባቸውን እያቋረጡ ሲነጋገሩ፤ ከየት መጣ ሳይባል የተገደበውን መዝጊያ ገፋ አድርጎ ገብቶ አንድ ሰው ተፊታቸው ቀጥ አለ። ሦስቱም ደነገጡና ቀና ብለው ቢያዩ፣ ያው የሚመኙት ተሸጦ የነበረው ሰዋቸው ሆነ፣ ነገር ግን ሕልም መሰላቸው እንጂ በውናቸው የሚያዩት አልመሰላቸውም። እርሱም እንደገና ሚስቱንም ልጆቹንም አንድነት ባየ ጊዜ በናፍቆትና በነዚያው ፍቅር ስስት ፈዘዘና እንባ እያነቀው መናገር ተሳነው። እነርሱም መብረክረክ እንዲያው መፋዘዝ እንጂ ለጊዜው ለመነሣትም ለመነጋገርም አልሆነላቸውም። ቆይተው ቆይተው ግን ሕልምነቱ ቀርቶ በውነት እርሱ አባታቸው መሆኑን ዐወቁና ነፍስ ገዝተው ሚስቱም ልጆቹም አንድነት ተነሥተው እየተላቀሱ ይረባረቡበት ጀመር። ተነዚያው ተሦስቱ ተወገቡም የተጠመጠመ፣ ታንገቱም የተንጠለጠለ፣ ጉልበቱንም ያቀፈ አለ። የዚያን ጊዜ ላያቸው ሰው፣ እንኳን ለተወለዳቸው ላልተዛመዳቸው ለጠላታቸውም ቢሆን ያሳዝኑና ያስለቅሱ ነበር። አባትዮውም በዚህ ጊዜ ቃሉን እንባ እያቋረጠው በተራ በየራሳቸው አቅፎ እየያዘ፤” እንዴት ናችሁ? እንደምን ናችሁ?” ይላቸው ጀመር። ቀጥሎም ፊቱን ወደ ሦስቱም አድርጎ እንባውን በመሀረሙ እየጠራረገ ያን ያህል ወርቅ ከወዴት አገኛችሁ እና ሰዳችሁ ለባርነት ከተሸጥሁበት አስለቀቃችሁኝ? እኔ እንኳ ገንዘብ ማጠራቀም አላውቅም ነበር፤ ከወዴት አገኛችሁት?” ሲል ጠየቃቸው። እነእርሱ ግን ለገናው ገንዘቡን ቢሆንላቸውም አጠራቅመው ሰደው ለማስለቀቅ እንጂ ከዚያ በፊት አለመሰደዳቸውን ዐውቀው ነገሩ ረቀቀባቸውና የሚመልሱት ቃል አጡ። ብቻ እርስ በርሳቸው ይተያዩ ጀመር። በዚሁ መካከል አንድ ቃል የሚመልስለት ባጣ ጊዜ አባትዮው ወደ ዋሕድ ዞረና “አንተ ትሆን ልጄ? ከወዴት አገኘኸው?” አለና ጠየቀው። በዚህ ጊዜ ዋሕድ ምን ይመልስ? እርሱ እንዳልሰደደ ያውቃል። በኋላ ግን ገና አባትዮው ዓይን ዓይኑን እየተመለከተ መልስ ሲጠብቅ ለዋሕድ የዚያ የሊጋሥ ሰው ነገር ትዝ አለውና፣ “አሁንስ ገንዘብ የሰደደውንና አንተን

ያስለቀቀህን ሰው ዐወቅሁት። አባዬ እኔ አልምሰልህ።” አለና፣ የዚያን የለጋሥ ነጋዴ ነገር፣ ለእርሱም ገንዘብ መስጠቱን ኋላም ያባቱንና የገዛውን ያረመኔ ስም፣ ያለበትንም ያገሩን ስም መጠየቁን ተረከለት።

አባትዬውም ነገሩን ሁሉ በሰማ ጊዜ እጅግ ደነቀውና ከላይም ክርስቶስን ከታችም ያንን ለጋሥ ያመሰግንና ይመርቅ ጀመር። ከዚህ ቀጥሎም ይኸው የጥንት ደጃዝማች ዋሕድን “ልጄ ያ ለጋሥ እኔን ሳያውቅ ሳይጠይቅ ሳይዛመደኝ ያን ያህል ገንዘቡን አውጥቶ ለገዛኝ አረመኔ ከፍሎ አስለቅቆ ወዳገሬ ስመለስ እንዳልደክም ጮሌውን ፈረስ አድርጎ፤ እንዳልራብ ስንቁን ጨምሮ ሰዶ ይኸው ላገሬ፣ ለወንዜ፣ ለቤቴ፣ ለሚስቴና ለልጆቼ አበቃኝ፤ ደስታዬንና ዓለሜን አሳየኝ። ስለዚህ እኔም አሁን ምንም ትልቅ ወረታ ባልመልስለት ባይሆን እንኳ ካለበት ድረስ ሄጄ “እግዚአብሔር ይስጥህ” እንድለው፣ ምናልባት ወደ ንግዱ አልሄደ እንደሆነ እባክህ ወዳለበት ውሰደኝ” ሲል ለመነው።

ዋሕድ ግን ተመልኩ በቀር የዚያን ሀብታም ነጋዴ እንኳን ስሙን አገሩንም ለይቶ አላወቀም፤ አልጠየቀም ነበርና ተጨነቀ። “እንግዲህ ያን ደግ ሰው፣ ያን መሳይ ለጋስ ሰው፣ ያባቴን ታዳጊ፣ የእናቴን፣ የእኅቴንና የኔን እንባ አድራቂ ወዴቱን መልሼ /የትኛውን አቅጣጫ ይገፄ/ ብሄድ አገኘዋለሁ? እርሱን ለማግኘት ምን ባደርግ ይሻለኛል?” እያለ ተጨነቀ። በመጨረሻ “እርሱን ታላገኘሁና ያባቴን በደኅና መግባት የኛን ደስታ የኛን ዓለም ታልነገርሁት እግሬ እስቲነቃ፣ እስትሞትም ቢሆን ዓለሙን እየዞርሁ እፈልገዋለሁ እንጂ ተቤቴ አልቀመጥም” ብሎ ሲያቆም ዋሕድ ስንቁን ቋጥሮ ዘንጉን ይዞ በማግስቱ ከዘመዶቹ ተላቅሶ ተሰነባበተና ለመፈለግ ተነሳ።

ዋሕድ ከቤቱ እንደተነሣ መንገዱን አወዛወዘው፣ ያን ሀብታም ነጋዴ ታንድ ትልቅ ከተማ ዳር ሰፍሮ ነበርና ያገኘው ወደዚያው ከተማ አቀና። ከዚያም በደረሰ ጊዜ ተከተማው ሳይገባ፣ በፊት ዓይኑን ያቀና፣ የዚያ ነጋዴ መደብር ወደ ነበረበት መስክ ነው። የመደብሩን ሥፍራ እያየና ያን ደግ አድራጊ ሰው እያሰበ ዋለለና ተብረከረከ። እንባውም ባይኑ ተንቸረፈፈበትና ተቆመበት ላይ ቁጭ አለ። ከዚያው አለቃቀሰና ሲነሳ ያን አሮጌ መደብር አጉድኖ እያየ አንገቱን እየጣመነው እግሩንም እንቅፋት እያከሰለው፣ ሁሉንም ቁም ነገር ሳይል ፊቱን ወደዚያ አሮጌ ሰፈር እንዳዞረ ተከተማው ገባ። ነገር ግን ከተማ ገብቶ ምን ያድርግ? የዚያን ሰው ስም አያውቅ፣ እገሌ ብሎ አይጠይቅ። ቤቱን አያውቅ፣ ወደቤቱ አይሄድ። ምን ያድርግ? ድሮ አሳቡ ሁሉ ተልከሰከሰበት። እንዲያው እንደሞኝ፣ እንደንከ፤ ታውራ መንገድ መካከል

ቆመና የሚሄድበትን ሳያውቅ ይዋልል ጀመር። የቤት ልጅ ነው፤ መከራ ከጥቂት ጊዜ በቀር አይቶት አያውቅ። በዚህ ጊዜ ውኃ ጥም ታከለበት፤ ራብም ይመተልገው ጀመር። ቶሎ ቶሎም ያንቧቅስ፤ ዓይኑም እንባ ይቋጥር ጀመር። ይኸ ሁሉ ሲሆን ዋሕድ ባደረገው ነገር አይጠጠትበትም ነበር። ያን ደግ ሰው ከመፈለግ፣ ዕድሜውንም ልክ ቢሆን እንዳይገበዝ አንድ ጊዜ በልቡ ቆርጦ ፎክሮ ተነስቷል።

ራቡና ጥሙ ሲበረታበት ጊዜ ዋሕድ ምንጭ ፈልጎ ከዚያ ምንጭ አጠገብ በመቁነን ተስንቁ በላና ከምንጩ አጎንብሶ ጠጥቶ "ተመስገን ጌታዬ" ብሎ ፍለጋውን ለመቀጠል ተነሳ። ከዚያ ወዲያ ያን ነጋዴ ለማግኘት ዋሕድ በያደባባዩም፣ በየገበያውም በየጎዳናውም በየደጀሰላሙም በየቤቱም በየበሩም በየመጋቢያውም በየቤተክርስቲያኑም እየገባ እየዞረ ቢፈልግ አጣው፤ የማይሆንለት ሆነ። ዋሕድ ተስፋውን ቆረጠ። ከዚያ ከተማ መፈለግ ተጀመረ አስራ አምስት ቀኑ ሆነ። ይህን አስራ አምስት ቀን ሙሉ ዋሕድ ቀን ቀኑን ሲፈልግ እየዋለ ማታ ማታውን ጅብ እንዳይበላው ከየቤተክርስቲያኑ ዛኒጋባ ነበር ያሚያድር። ያ ሀብታም ነጋዴ ከዚያ ከተማ አለመኖሩን በእርግጥ ተረዳና፣ "እንግዲህ ወዴት ሄጄ ልፈልገው" ሲል አሳብ ገባው። አስቦ አስቦ የተሻለ ነገር ያገኘው ወደ የነጋዴው መደብር፣ ወደ የነጋዴው ጉዞ እየሄደና እየዞረ መፈለግ ብቻ ሆነ። የዋሕድ አሳብ በዚህ ቆመ።

ይኸን በመከረ በማግስቱ ዋሕድ ከዚያ ከተማ ወጣና በየትም ሳይል አንዱን መንገድ ይዞ መደብር ፍለጋ ይጓዝ ጀመር። ይሄድ ይሄድና ከጉብታ ላይ ወጥቶ ባገሩ ዙሪያ ወይ መደብር ወይም ነጋዴ ጉዞ ለማየት ይመለከታል። ሰውም ተመንገድ ሲገጥመው መደብርና ነጋዴ ብቻ ነው የሚጠይቅ። "ነጋዴ በዚህ አለፈ፣ ከዚህ ሠፈረ" ያሉት እንደሆነ ወደዚያው ሲሮጥ እየሄደ ከነጋዴው መካከል ያን ደግ አድራጊ ነጋዴ ይፈልጋል። መልኩን ካላየው በቀር ስሙን አያውቅምና የሚፈልገውን ሰው ተነጋዴዎቹ አንዱን "እገሌ ወዴት ነው? ወዴትስ ደረሰ?" ብሎ መጠየቅ አይሆንለትም ነበር። ከዚያ መደብር ሲያጣው ወደ ሌላው መደብር ሲሄድ ሲሄድ፣ ተመሸበት ሲያድር፤ ዋሕድ ሆየ አንድ ቀን ሲጓዝ ውሎ መንደር ተሌለበት ከምድረ በዳ ደረሰ። ከዚያው ምድረ በዳ መካከል በሩቅ ትልቅ የነጋዴ ሠፈር አየ። ነጋዴ መሆኑንም በመደብሩ ለየው። ዋሕድ ያንን መደብር ባየ ጊዜ አደባበሩም መጠኑም ያን ሃብታም ባየ ጊዜ ያየውን መደብር መሰለውና ለጊዜው ደስ አለው። ተዚያ ሠፈር ለመድረስ አስቦ ይባክንና ይሮጥ ጀመር። ወንዛወንዝ የበዛበት ሜዳ ነበረና ቢለው ቢለው ርቀቱ ያው ነው። መደብሩ በመጫኛ አስሮ ወደኋላ እንደጎተቱት ሁሉ ወደ ኋላ የሚርቅ እንጂ የሚቀርብ አልመሰል አለው። መንገዱ ቢሄደው ቢሄደው

አልገፋህ አለው። ጊዜው ግን ተማሸ፤ ፀሀዩቱም ተቆለቆለች፤ ዋሕድ ግን ከመደብሩ ሳይደርስ በፊት ምድር መሸበት። በማኸል ቤት ጀንበር ጠለቀችና ድንግዝግዝ አለ። ቀጥሎም ጨለመና ላይን ነካ። በወፎች ጫጫታ ሥፍራ የፈንጣው ድምጥና በያረንቋው፣ በየረግረጉ ያለው ጉርጥና ጓጉንቸር ዋካታ ተተካበት። ይልቁንም በዚሁ መካከል ባንድ ወገን ተኩላው ባንድ ወገን ቀበሮው ሲጫጫሁ ሳለ ባንድ ወገን ደግሞ ጅቡ እሙኝ ይል፣ ነምሩ ይጓጉር አንበሳው ይገሰል ጀመር። ይኸ ሁሉ ሲሆን ዋሕድ ብቻውን ከምድረ በዳው መካከል ሆኖ በፍርሀት እየተንቀጠቀጠ ይጓዛል። ወደ ምሽቱ አቅራቢያ የወፎች ጫጫታ እንደ ባልንጀራ ሆኖት ነበር። ኋላ ግን ያራዊት ድምጥ በቀኝና በግራ ከበበው፤ ስለዚህ ተጨነቀ። ከዚያው እንዳያነጋ ቤት የለ፣ ተምን ይጠጋና ይደር? ተሜዳው ላይ እንዳያድር አራዊት ሊናጠቁት ሆነ። ዋሕድ በዚህ ጊዜ ምን ያድርግ? ከዚያው ተኝቶ አውሬ ቢበላውስ፣ ቢሆንለት በቁሙ እየተከላከለ መጓዙን መረጠና “ምንም ቢሆን ታየሁት መደብር ሳልደርስ አላድርም” ብሎ ሲሄድ ሲሄድ ጨለማው እያደረ ባሰ። ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ሆነበትና መንገዱም ጠፋው፣ ልቡም መባባት ጀመረ። በቀኝም በግራም በፊትም በኋላም ቢያይ ሁሉም ጅብ፣ ሁሉም ነምር፣ ሁሉም አንበሳ ሆኑበት። “ከአሁን አሁን ጅቡ ሳላየው መጥቶ ጎኔን ይዘበትረኛል፤ ነምሩም ዘሎ ያንቀኛል ወይም አንበሳው ይሰብረኛል ወይኔ ሆዬ! ዛሬ ታንዱ ባመልጥ መቼም ታንዱ አላመልጥ” እያለ ነፍሱን ብንን ብንን ማድረግ ብቻ ሆነ ሥራው። ምን ያድርግ፣ ዋሕድ ፍርዱ ነው፤ ደግሞም ገና ጮርቃ ልጅ ነው። ዋሕድ ይኸ ሁሉ ሲሆን ያንን መደብር ያየበትን አንጣር ይዞ ቀስ በቀስ እያለ መጓዙን አልተወም። አንድ ጊዜ ግን በጨለማው አሻግሮ አንድ ቁጥቋጦ አየና አራት እግር ያለው የውነተኛው አንበሳ መሰለውና ነፍስና ስጋው ተለያየበት። ጉልበቱ እየተብረከረከ ትክ ብሎ ሲያየው ጊዜ ያው በፍርሀት የተፈጠረ አንበሳ የሚንቀሳቀስ፣ ዘሎም ሊይዘው ልበልን ልተው የሚል መሰለው፤ በዚህን ጊዜ ዋሕድ ብልኀት ያገኘ መስሎት፣ ለዚያ አንበሳ ብዙ ሰው የመጣበት እንዲመስለው ብሎ ድምጡን ባስራ አምስት አይነት እያረገ፤ አንድ ጊዜ ቀጭን፣ አንድ ጊዜ ጎርናና እያደረገ አንዳንድ መንጋ ሰው እየጮኸ “ከበብ፣ አያምልጥህ አይዞህ፣ በዚያ እለፍ” እያለ ድምጡን አንዱን በአንዱ ላይ እያነባበረ ይጫጫህ ገባ። ዋሕድ ግን ብቻውን አንድ ፍጥሩን ነበር። ከጨለማው ጋር እየተደባለቀ ይሳከር ተነበረው ተገዛ ጥላው በቀር የዚያን ጊዜ ምንም ባልንጀራ አብሮት አልነበረም። ያ በከንቱ የታማ ቁጥቋጦ ምንም ባልንጀራ በአንበሳ ስም ቢጠራ፣ ነፍስ የለውምና አልሸሸለት ሲል ጊዜ ዋሕድ መንገድ ሰብሮ ይሄድ ጀመር። ዙሮ ባየው ጊዜ ግን ያው በገዛ ፍርሀቱ የፈጠረው የቁጥቋጦ አንበሳ የሚከተለው መሰለው። ዋሕድ ሆዬ ጉልበቱም በፍርሀት

እየተብረከረከበት መሄድ ተሣነው። ከዛፍ ላይ ወጥቶም እንዳያመልጥ ከዚያ ምድረ በዳ እንዳጋጣሚ ሁሉ እንኳን ትልቅ ዛፍ የምጣድ መሰቅሰቂያ የሚሆን እንጨትም አልነበረም።

ተዚህማ ወዲያ ዋሕድ ተጨነቀ፣ ፍርሀቱም እያደረ ነገሠበት፣ የሚያየውም ጥቁር ነገር ሁሉ አውሬ ብቻ መሰለው።፡ ከፍና ዝቅ እያለ በዳባቱ እያየ መንገዱን እየለወጠ ሲሄድ በግራው አንድ ትንሽ ዋሻ መሳይ ደርሶ ገች አለበትና የዋሕድ መብረክረክ ባሰ በድንጋጤ ቀጭን ላብ መጣና በገላውም በፊቱም ተሰራጨበት። "ታንዱ አንበሳ ባመልጥ ከሁለተኛው ደግሜ ደረስሁ። አሁንስ ቁርጥ ነው ኣላመልጥም" እያለ ዋሕድ ይጨነቅ ጀመር። ቁሞ እንደ ቄጠማ እያረገረገ ድምጡን እንደፊተኛው በያይነቱ ከፍና ዝቅ እያደረገ በውኃ ጥማት የከረረው ጉሮሮው እስቲነቃና እስቲሰነጠቅ ድረስ "ከበብ፣ ኣያምልጥህ" እያለ ይጮህ ጀመር። ነገር ግን ሲያየው ጊዜ ምንም አይሸሽለትም። የናቀው መሰለውና እንደገና አጥብቆ ተንጠራርቶ ሲጮህ ጊዜ ያው ነው። ኋላ ግን ድምጡም ሰለለበት ጉሮሮውም የባሰውን ተዘጋበት። ከዚያ ታስራ አምስት ዓይነት ድምጡ አንዱንም ዓይነት ለመጮህ ቸገረው። ያው የውሸት አንበሳም ንቆት ዝም ያለው መሰለው። ዋሕድ ከዚህ በኋላ መጠርጠር ጀመረ። "ድንገት ሌላ ነፍስ የሌለው ጥቁር ነገር ይሆናል" ማለት ጀመረ። ቀጥሎም በውል ለማስተዋል በጉልበቱ ተንበረከከና ትክ ብሎ "ከአሁን አሁን ይንቀሳቀስ ይሆን" እያለ ሲመለከት፣ እንደገናም "ጥቂት ጥቂት የሚንቀሳቀስ ይሆን" እያለ ሲመለከት ጥቂት ጥቂት የሚንቀሳቀስ መሰለው። ዓይኑን ሳያጥፍ አተኩሮ እንደገና ባስተዋለ ጊዜ፣ ይልቁንም ከመንቀሳቀሱ ወደ እርሱ መራመድ የጀመረ መሰለው። አተኩሮ ከማየቱ የተነሳ በዓይኑ እንባ ሞላበት። ዋሕድ ግን ጊዜ ያጠፋሁ መስሎት እንባውን መጥመቅ ትቶ ባየ ጊዜ፣ ይልቁንም ያው እንባው እያደናገረው የዚያን አውሬ ርምጃ ወደ እርሱ የተፋጠነ አስመሰለው፤ በመጨረሻ ግን ዋሕድ ዓይኑን ከዚያው አውሬ ላይ እንደተከለ ባባና ተተንበረከከበት ጠጠር አፍሶ ወደፊቱ ብትን አደረገ። ለመከራ ኣጋዥ አይታጣምና ዋሕድ ላደረገው ሁሉ ነገር ምስክር ሆና ተሸሽጋ ስታይ የነበረች አንድ ድርጭት "ተተሸሸግሁበት ተገለጥሁ" ብላም እንደሆነ አይታወቅ ሳር ቅጠሉን በክንፏ አሰሽብራ ተነስታ በረረች። ዋሕድም ያው አውሬ ደርሶ አነቀኝ መስሎት ትንፋሹን አቋርጦ እንደሞተ ታለበት ተንዘራጋና መንቀሳቀሱም ቀረ። ቆይቶ ቆይቶ ግን "ነፍሴ አለች ወይስ ሙቻለሁ" ብሎ አሰበ። ቀጥሎም በአውሬው መነከሱንና አለመነከሱን ለማወቅና ለመረዳት በጆሮው ቢያንቋቋም ምንም አልሰማህ አለው። ዓይኑን ግን አውሬ ሲነክሰው ጨክኖ ማየቱን ቢፈራ ጨፍኖት ነበርና ሲፈራ ሲቸገር ገርበብ

አድርጎ ቢያይ ተፊቱ እንኳን አንበሳ ምንም ጥንቸል አልነበረም። ዋሕድ ከዚያ ወዲያ ነፍስ አጋባና ጫን ተንፍሶ ተነሳ። አሻግሮ ባየ ጊዜ ያ አውሬ ጥንት ተነበረበቱ አይንቀሳቀስ፣ ምን አይል፣ ዝም ብሎ አየው። ዋሕድ ከዚያ ወዲህ ትልቅ አሳብ ገባውና “ወይስ ምንም አውሬ አልመጣም ኑሯል፣ ወይስ አውሬም አይደል ኑሯል? ይሁንና ሲመጣ ባይኔ አይቼዋለሁ፤ ወይስ ነካክሶ ጥሎኝ ሄደ” እያለ ገላውን ቢዳስስ አልተነካም። “ምንም ይሆን በገዛ ፍርሃቴ ባብቼ ኑሯል መውደቄ፣ እንኳን ሰው አላየኝ፣ በገዛ ፍርሃቱ ወንድ ልጅ ሆኖ እንዴት ይወድቃል” እያለ እየተደመመ እንደገና ጉዞውን ያዘ።

ዋሕድ እንደገና በረታ፣ ከዚያ መደብር ሳይነጋ በፊት ለመድረስ ተመኘ። ጊዜው ግን ተዋርዷል፤ ተመንፈቀ ሌሊት ዝቅ ብሏል። ዋሕድ እንደ ባልንጀራ አድርጎ ሲወዳቸው የነበሩት እነስድስቱም ጠፉ። ጨለማውም እጅግ በረታ ። ነገር ግን አንድ ጊዜ ተመንገዱ ሲወጣ አንድ ጊዜም ጥቃሽ ሲያገኝ፣ ሲሄድ ሲሄድ የመደብሩ እሳት ይታየው ጀመርና ደስ ብሎት እየተበራታ ሲጓዝ ታንድ ወንዝ ቁልቁለት ደረሰ። ጥቂት ዝቅ እንዳለ የሠፈሩም እሳት ላይኑ በሸጡ ጀርባ ተሠወረው። ጨረቃ የለ የንጋት ኮከብ እንኳን ገና አልወጣች ምንም ሌቱ ቢዋገድ ጨለማው ይልቁን ባሰ እንጂ አልተሻለም። በዚያው ላይ ደግሞ የግራው የቀኙ ወንዛወንዙ ገረገንብ ጥላ ታከለበትና ጨለማው ዓይን ቢወጉ አይታይ ሆነ። ዋሕድ በዚህ ጊዜ ቁልቁለቱን ተዳፋ። መንገዱ ግን ጠፋው፤ ምን ይሁን? ሳልደርስ አልቀርም ብሏልና ከፎከረበት የነጋዴ ሠፈር ለመድረስ በዚያ ጥቅጥቅ ድንጉር ጨለማ ቁልቁለቱን በእጅና በእግሩ እየተተማተመ በቅምጡ ሲንኳተት በንብርኩም ሲድህ አንዳንድ ጊዜም አልሆንለት ሲል ፊቱን ወደመጣበት አዞሮ እግሩን ወደሚሄድበት አስረዝሞ ማጭድ እረስቶ እንደመጣ ለጓሚ በጁ ሣር ቅጠሉን እየጨበጠና እየሚጠጠ እየጓጠጠም እሾም አይቀረው እንደ ሐር ጎፍላ እየጨባበጠ በደረቱ ሲሳብ ሲጋፍና ሲጎተት ተወራጁ ወንዝ ደረሰ።

ያ ወራጅ ውኃ ለዋሕድ ጥሩም ይሁን ድፍርስ አልታወቀውም። ገና በጥማት ልሳኑ ታስሮ ነበርና ተጎንብሶ እንደ ገልዳ ጠጅና እንደ ገፈታማ ጠላ ለስም ያህል ተላይ ያሰፈፈውን አረንጓዴና ስልባቦት እፍ እፍ እያለ በትንፋሹ ገፈፈና የተቻለውን ያህል አንስቶ ጥማቱ እንዳለፈ፣ “ተመስገን ጌታዬ” አለና ተሹል ደንጊያ ላይ ቁጭ ብሎ የመሻገሪያውን መልካ ያይ ጀመር። ቢመለከት ሁሉም ጥልቅ መሰለው። ቋሚ ይሁን ጠሊቅ ውኃው አልታወቅ አለው። መሻገሪያውም በላይ ይሁን በታች አልታወቅህ አለው። ዝም ብሎ እንዳይገባ ዋሕድ የዋና ነገር አያውቅም ነበረና ፈራ።

ይልቁንም ያ ወንዝ ፏፏቴ አልነበረውም "ዝም ያለ ወራጅ ውኃ ሙሉ ነው" ሲሉት ሰምቶ ነበርና ፈራ "ምን ላድርግ" እያለ ገና በልቡ ሲያመናምን እንዳጋጣሚ እንደእርሱ ውኃ ጥም የተባሰች በቅሎ ከመደብር ችካሏን ነቅላ አምልጣ ደረሰች። ዋሕድ "አውሬን ይሆን" ብሎ ሲደናገጥ አፍንጫዋንና ከንፈሯን ስታማታ በቅሎነቷን አውቆ ሲረጋጋ፣ ያችው በቅሎ ገስግሳ ከውኃው እስተንቢያዋ ገብታ ተነከራ ተዚያ ውኃ ትግፍለት ጀመር። በዚህ ጊዜ ዋሕድ በዚያች በቅሎ ምክንያት የውኃውን ግልብነትና ቁምነት አውቆ አስረገጠና "ቶሎ በቅሎዪቱ ጠጥታ የጠገበች እንደሆነ አትያዘኝም ታመልጠኛለ" ሲል ወደ በቅሎዪቱ አንጣር አድርጎ ውኃውን በዘንጉ እየለካ ተሻገረና ተማዶው ደረሰ። የዚያን ጊዜ በቅሎዪቱ አንድ አፍታ ተዚያው ውኃ ግፋለት አንገቷን አቅንታ ጆሮዋን እያርገበገበች ለሁለተኛው ገና "ልበልን ልተው፣ ይብቃኝ አይብቃኝ" ስትል ዋሕድ ቶሎ ብሎ "እንቺ፣ እንቺ" እያለ እያባባለ ቀረበና ያዛት። እርሷም ገራም ነበረች። ትራገጥ መስሎት አስቀድሞ በእጁ ይዳስሳት ጀመር። በቅሎዪቱ ግን መድከሙን አውቃ "ይረፍብኝ" ብላ ያዘነች መስላ ዝም አለችው። መገረሟን አስረገጠና ዋሕድ ወደ ትልቅ ደንጊያ ስቦ አቀረበና ተቀመጠባት። ቀጥሎም ወደ መጣችበትም ወገን አቃንቶ "እንግዲህ ወደ ሠፈርሽ ውሰጂኝ" አለና አሳቡን እርስዋ ላይ ጣለው። በቅሎዪቱም ዋሕድ የሚለው ነገር እንደገባት ሁሉ የመደብሩን መንገድ ይዛ ሳትነቀንቅ ይዛው ትጓዝ ጀመር። ብቻ አንዳንድ ጊዜ ለምለም ሣር ባየች ጊዜ ቆማ ትነቻቸፍና እርሷ በጠዳት ጊዜ እንደገና ተባልንጀሮቿ ለመደባለቅ መንገዱን ትይዛለች። ዋሕድ ግን ቀስ አድርጎ እንዳይወድቅ ብቻ ጋማዋን ተመጨበጥ በቀር አልኰለኰላትም፤ "ሂጂ መጭ" አላላትም፤ እንዲያው እርስዋ እንዳለች ተዋት። ስለምን እርሷ በፈቃዷ ነውና የተያዘችለት መጭ እያለ በግሩ መጎሳሰም ወረታዋን ማጥፋት መሰለው። "አሁንስ ቢሆን የማን እንግዳ በተቀባይ ቤት ገብቶ ያዝዛል?" እያለ ያስብ ነበር ። ያች የዋሕድ በቅሎ ግን ተሁሉም ሳትደርስ እያዘገመች ስትወስደውና ከሠፈሩ ሊደርሱ ጥቂት ሲቀራቸው ያችኑ በቅሎ ሲፈልጉ የነበሩ ጎረዳማኖች ዱካ ሰምተው ሲሮጡ ደረሱ። በዚህ ጊዜ ዋሕድ አለመገንዘቡ በሰው በቅሎ መቀመጡን ያውቃልና ፈርቶ ተበቅሎዪቱ ወረደና ለመሸሽግ አሰበ። ነገር ግን ጎረዶማኖቹ በቅሎዪቱን ከበው በመጫኛ ሲይዙ እርሱም በዚያው ተገኘና ተያዘ። እንዳያመልጥ እግሩ በጣሙን ተሳስሮ ነበርና ቸገረው። ጎርዶማኖቹ ግን ተበቅሎዪቱ አጠገብ ባገኙት ጊዜ፣ እርሷን ከችካል አውልቆ ሰርቆ ሊሄድ ሳለ የደረስንበት መስሏቸው "አንተ ሌባ የታባትህ" እያሉ በቆመጣቸው ይቸበችቡት፣ ፍዳውን ያሳዩትና ይሰድቡት ጀመር። ዋሕድ ግን "እባካችሁ እንድ ጊዜ ስሙኝ፣ ሌባም አይደለሁ" እያለ ቢጮህ ቢቀባጥር ማን ይስማው፤ ምላሹ

“አንተ ሌባ፣ አንተ ቀጣፊ፣ ስትሰርቅ ደርሰንብህ ሌባም አይደለሁ ትል ጀመር” ብቻ ሆነ። ከዚህ ወዲያማ እየገፋፉ ወደ መደብሩ አደረሱና ገሚሶቹ በቅሎዪቱን በካስማ ሲያስሩ፣ ገሚሶቹ ዋሕድን ገለበጡና አሰሩ። ያን የመሰለ ቀንበጥ ለጋ ልጅ የፊጥኝ ተገልብጦ ምን ይቻል? መተንፈስም አቃተው። ትንፋሹም ባጭር ባጭሩ ሆነ፣ ቅትት ቅትት የሚል ሆነበት። የዚያን ጊዜ ላየው ሰው ዋሕድ እጅግ ያስለቅስ ነበር። የፊጥኝ ባሏለበት ነገር ተገልብጦ እንደሚታረድ ፍየል እጅና እግሩን ተኮድኩዶ ተጋድሞ በቅሎች አንዳንድ እግራቸውን ብቻ በገመድ ታስረው ጥሬ ተዘርግፎላቸው ሲበሉ ዋሕድ ተተጋደመበት እንደ ሆነ አየና “ምነው ባይሆን እንኳ እንደናንተ እግሬን ብቻ ባሰሩና እንደናንተ ትንፋሼን በሙሉ በተነፈስሁ” እያለ በበቅሎቹ ሳይቀር ይቀና ጀመር። መተንፈስ ግን የማይሆንለት ሆኖ ሊፈነዳ ደረሰ። ያን የንጋት ኮከብ የመሰለ ዓይኑን እያንከባለለ ዙሪያውን ሰው ቢፈቅድ ማን ይገላግለው? ማን ያማልደው? ማን ጥቂት እንኳ ገመዱን ያላላለት? በከንቱ ነው። መከራው ሥቃዩ ተገድላቸው ሲነበብ እንደሚሰማው እንደ ሰማእታት ሥቃይ ሆነ እንጂ ተዚያም አያንስ፤ ያ ወደል ወደል ነጋዴ ሁሉ በክርንም በጡጫም በርግጫም ሲተካከዝበት እንዳይነጋ የለምና ለዋሕድ ነጋለት። ሲነጋ ተኝቶ የነበር ነጋዴ ሁሉ እየተነሳ እየመጣ ያን በከንቱ የታማ ሌባ እንደ ቀረመት ፍሪዳ በዙሪያው ከቦ ሲያይ ፀሐይ ብልጭ አለችና ሌሊቱን ሁሉ በእሾና በጋሬጣ የቆሰለውን ገላውን በደም የተበከለ ጋቢው፤ ቁልቁለቱን ሲወጣ ሲወርድ የተገጣጠበውን ጉልበቱን፤ ደረቱን፣ ጀርባውን አዩና እርግጥ በሌባነቱ አቆሙት። “ተሌላም ሥፍራ እንደዚሁ ሲሰርቅ ተገኝቶ ገርፈው ለቀውታል” አሉ። እነዚያው ሰዎች እኩሉም “አስረን ተኝው ጋር እናጉዘው” አሉ። ዋሕድ ግን ዓይኑን መክፈት እስኪሳነው ድረስ ደክሞ መተንፈስ አቅቶታል። እንኳን ቁሞ ከእነእርሱ ጋር ይጓዝ እውነትም በቅቶታል፤ በዚያን ጊዜ ገሚሱ ነጋዴ “ለአገሩ ሹም እናስረክብረው ወይ አስረን ተበቅሎ ጋር እንንዳው” እያሉ ሲከራከሩ፣ እኩሌቶቹ በእግራቸው እየጎሰሙ “ማን ትባላለህ፤ ከወዴት መጣህ” እያሉ ቢጠይቁት እንኳን መመለስ ይሆንለት፤ ያን ያህል ሲረግጡትም ስቅቅ አይለውም ሆነ። እንደበድን ወዲህና ወዲያም ሲያገላብጡትና ሲያንከባልሉት እንደሬሳ ሆነ። በዚህ ጊዜ አብዛኞቹ፣ “ተዉ እንፍታና እንተወው፣ የሞተ እንደሆነ ሰበቡ በእኛ ይሆናል” አሉ። ወዲህም ረፈደባቸውና ከብት ማዋዛት ጀመሩ። ወዲያውም ጫጫኑና ለሹም ማስተላለፉ ስለረፈደ አላደርሳቸው ብሎ ዋሕድን ተፍተው ተዚያው እንደተጋደመ ትተውት ተጓዙ። ከመደብሩ ላይ አጋሰስ ታረከሰው ሳርና ከእርሱ በቀር ምንም አልቀረም።

ከዚያው ላይ ያው ያልታደለ ዋሕድ፣ አለስንቅ፣ አለውኃ፣ አለዘመድና አለደጋፊ ወድቆ ቀረ። ሌሊቱን ሁሉ ውርጭና አመዳይ አድሮበት በዚያው ሥፍራ ደረቅ ፀሐይ ተተከቶ ልብ ልቡን፣ ግንባር ግንባሩን ያከሰለው ጀመር። ተነስቶ ወደ ጥላ እንዳይጠጋ በምን ጉልበቱ፣ በምን ዐቅሙ። ቀን ተሌት መንገድ መትቶታል፤ ቀጥሎም የጎረዶማኖቹ እርግጫ፣ ጥፊ፣ ጡጫ፣ መንዶ፣ ጎመድና ግፊ ሰልቆ አደንዝዞታል፤ ከዚያም በላይ የእስራቱ መከራ ተጨምሮበታል። እህል ተቀመሰ ሁለት ቀኑ ነው፤ ከዚያ ሁሉ በኋላ እንደምን መንቀሳቀስ ይቻለው! እንዲያው ዝም ብሎ ፀሐይ እያቀረናው ውኃ ጥማት እያከረረው በሞቱ ቆርጦ ተዘረረ። ክርስቶስ አትሙት ያለው ሰው መቼም አለቀኑ አይሞትምና እንዳጋጣሚ ሁሉ አንዲት ኩበት ለቃሚ ባልቴት ተሩቅ ተጋድሞ አየችው። ተመጀመሪያው ነጋዴ ተመደብር የረሳው እቃ መሰላት። እያደረች ስትቀርብ፣ ስትቀርብ የሰው አካል መሰላት። በጥፍሯ ቁማ ስታስተውል በሩቅ የተጋደመ ሬሳ መሰላትና መቅረቡን ፈራች። ወደኋላም እንዳትመለስ እርግጡን ነገር ሳታይ መሄድዋን ጠላች። በዚህ ጊዜ ስትፈራ ስትቸር ቀስ እያለች እያጠቀሰች ትቀርብ ጀመር። ምንም አተኩራ ብታይ ሲንቀሳቀስ አላየችውም ነበርና ሬሳ ነው ብላ ጠረጠረች። ከዚህ ወዲያ ግን ያደረ የዋለ ሬሳ እንደሆነ ፈርታ አፍንጫዋንና አፍዋን በጨርቋ አፍና ይዛ በጣም እየቀረበች "ምን ሰው ነህ? ምን የሆንህ ሰው ነህ?" እያለች ብትጠራው አይናገር አይጋገር፤ ዝም ብሎ አየችው። እርሷ ግን ድንገት የማውቀው ሰው ሙቶ እንደሆነ ብላ ለማወቅ ቀረበችና ብታይ የዋሕድ ዓይን ጥቂት ገርበብ ብሎ ነበርና "አይዞሽ ገና ነፍሴ አልወጣችምና ቀርበሽ ብስቴን እይልኝ፣ ቢቻልሽ አግዢኝ" የሚል መስሎ ታያትና ጥቂት መንቀሳቀሱን ባየች ጊዜ ቀስ ብላ "ምን ሆነሃል ወንድሜ" ስትል ጠየቀችው። እንዳልመለሰላት ባየች ጊዜ ደረቷን እየደቃቃችና እያለቀሰች ስትሮጥ ሄደችና ተቤቷ ባንድ እጅዋ ወተት ባንዱ እጅዋ ውኃ ይዛ ያች ደግ ባልቴት ደረሰች። የወተቱን ቋጫ አኖረችና ባንድ እጅዋ አንገቱን ቀና አድርጋ ከደረቷ ላይ አስጠግታ "ጉሮሮህን እስቲ አርጥበው ልጄ" አለችና ውኃውን ተከንፈሩ ለገተችለት። ዋሕድም በዚያ ውኃ ከንፈሩን እንደ መነካከር እደረገ እንጂ ለጊዜው መሳብ አልሆነለትም። የተሰነጣጠቀው ከንፈሩ እንደራሰለት አይታ የቋጫውን ወተት ለገተችለት። ወተቱን አንድ ሁለት ጊዜ ጉርጉጭ እንዳደረገ ዓይኑን መግለጥና እንደልቡ መተንፈስ ጀመረ። ያች ደግ ሴት ነፍሱ እንደገባለት ዐወቀችና ለኩበት መልቀሚያ ያመጣችውን እንቅብ ደፍታ አንተራሰችው። ራቅ ብላ ከፍታለ ዲብ ላይ ወጥታ በቅርብ ጠምዶ ሲያርስ የነበረውን ባሏን ጠርታ "ወዲህ ና፤ የምታግዘኝ ስራ አለ" አለችው። ባሏም ጥማዱን አቁሞ ሲሮጥ ደረሰና "ነገሩ ምንድር ነው?" ብሎ እስቲጠይቃትም አላቆየችውም

ብቻ “እባክህ ይህን ኀበዝ ተጋግዘን ተቤታችን እንውሰደውና እናስታመው” አለችው። እነርሱም እየተጋገዙ ወስደው ተገዛ አልጋቸው አስተኙና እንደናትና እንዳባት ያማረውን ሁሉ ሳያሳጡ እነርሱ ከመሬት እየተኙ አስታመው አዳኑት። ዋሕድም የነዚህን ባልና ሚስት ደግነትና የጎረዶማኖቹን ጨካኝነት እያመዛዘነ “ከዚህ ዓለም ስንት ክፉ፣ ስንትስ በጎ ሰው አለበት” እያለ ለብቻው ተደመመና “እግዚአብሔር ካሣችሁን አያስቀርባችሁ፣ ተምስጋና በቀር እኔ የማደርግላችሁ ነገር የለኝም፤ አሁንም ይኸው ጉልበቴ በናንተ ቸርነት ጠነከረልኝ፣ እንግዲህ ልሂድ” አላቸው። እነእርሱም ስንቁን ሰንቀው መንገዱን አሳይተው ሸኝተው ሲጨርሱ “ተዛሬ በፊት ያገኘህን መከራ አትርሳ፣ ሰው ክፉ ነው፤ ከእንግዲህ ወዲህ ተጠንቀቅ፣ ብቻህን አትሂድ። ለኛ በቁሙ በወርዱ፣ አንድ ልጅ ብቻ ነበረን። ይኸንኑ ልጃችንን አንድ ብቻውን ተመንገድ አግኝተውት፣ እስላሞች ነጋዴዎች አፍነው ይዘው ሸጡት፤ እኛም ይኸው ደጋፊ፣፣ጧሪ፣ ወራሽ፣ ቆራሽ አጥተን ቀረን። አንተም ገና ያልባለቅህ ልጅ በሰው እጅ እንዳትወድቅና እንዳትሸጥ ተጠንቀቅ” ብለው መክረውት ተሰነባበቱ። ዋሕድም ከዚያው ላይ ሲሰነባበቱ የሁለቱንም ስም፣ የተሸጠውን ልጃቸውንም ስም፣ ያገራቸውንም ስም አስተውሎ ጠይቆ አጥንቶ ይጓዝ ጀመር። እጅግ እየራቀ ሄደ። ዋሕድ የሚሄድበትን ስፍራና የሚሄድበትን አገር ቆላማ ይሁን ደጋ አያውቅም ነበር። ብቻ የነጋዴ ወሬ እየጠየቀ “በዚህ አለፈ፣ ከዚህ ሠፈረ” ሲሉት ያን ያሉትን መንገድ ይዞ ይጓዝ ነበር። እንዲህ እንዲህ ሲል ሳያውቀው የክርስቲያኑን ድንበር ዘሎ የሚፈልገውን ያን ሀብታም ነጋዴ ሳያገኝ ታረመኔው አገር ገባ። ሰውን አስቀድሞ ባየ ጊዜ ቋንቋውም ልብሱም ስራቱም ምኑም ተለየበት። ዋሕድ መጨነቅ ጀመረ። ወደ ኋላውም እንዳይመለስ እንዴት ብሎ። እግሩ እንደመራው ነበርና የሚጓዘው የመጣበትን ስፍራ ቢያይም አገር ምድሩ ዞረበት ። የፀሐዩ መግቢያና መውጫ አንድ ሆነበት። በእዚህ ቅጡ ጠፍቶበት ሲጨነቅ ምድር መሸበትና “በቁሜ አውሬ ከሚበላኝ ባይን ሰው እንዳደረገ ያድርገኝ” አለና ተመንገዱ ዳር ታለው ተማንላቸውም ቤት ሄደና፣ “እባካችሁ አሳድሩኝ” ብሎ ለመነ። ዋሕድ የተናገረው ነገር አልገባቸውም። ነገር ግን በመላ አሳድሩኝ ማለቱን ዐወቁና ደስ ብሏቸው በግራና በቀኝ ሆነው ከሩቅ ዘመቻ እንደተመለሰ ዘመዳቸው እጁን ይዘው እየደጋገፉ ከቤቱ አስገቡት። ምግቡንም አሳመሩና ከስቶ እንዳያድርና ዋጋ እንዳያፋርስባቸው አበሉት፣ አጠጡት። ዋሕድ በደግነት የእግዚአብሔርን እንግዳ ለማክበርና ለማስተናገድ ያደረጉት መስሎት ይመርቃቸው ጀመር። እነርሱ ግን ወዲያው በልቶ እንደጨረሰ ያን በጨለማ ሲሄድ ያደረ ዕለት የተላላጠውንና ከነጋዴ መደብር የተደበቀውን ሰውነቱን ቆስሎ ሽሮ ባዩ ጊዜ ዙሪያውን ከበው እየዳሰሱ

ያስተውሉት ጀመር። ድሮ እነርሱ "ዋጋ ያወርድብናል አያወርድብንም" እያሉ ለነገው ገበያ ማሰናዳታቸው ኑሯል። ዋሕድ ግን ይኸን ሁሉ አላወቀ በቅን ልቦናው የዳነውን ቁስሉን ድፍጥጥ ድፍጥጥ እያደረጉ፣ እየተመለከቱ ሲነጋገሩ ሲያያቸው ጊዜ ያዘኑለት እየመሰለው "አሁንስ ድኛለሁ፣ አያመኝም" ይላቸዋል። እነርሱ ግን የሚለውን አይሰሙ፣ አያውቁ ዝም ብለው የነገውን ገበያቸውን "ምን ያህል ብለን እንሸጠው" እያሉ ያሰናዳሉ። አስተኝተው እንዳይሾልክና እንዳይጠፋባቸው ሲጠብቁ አሳደሩና እጅግ ማልደው ተነስተው ገንፎ አገንፍተው፤ ከሚጣፍጥ እንቅልፉ ዋሕድን ቀሰቀሱና ያበሉት ጀመር። በልቶ እንደጠገበ ወዲያው ሁለንተናውን በቅልጥም ያሻሹት ገቡ። ዋሕድ ግን ምንም ቢሆን የጌታ ልጅ ነበርና ባይን እንኳ በሰንደል ንጥር የጣፈጠ ቅቤ ነው እንጂ፤ ሰው እንዳሮጌ መጫኛና እንደገረረ ጀንዲ በቅልጥምና በሞራ ሲጨማለቅ አይቶ አያወቅም ነበር። ስለዚህ "አይሆንም አታስነኩኝ" እያለ ተናገረ። እነእርሱም ምንም ቋንቋውን ባያውቁ ባኳኋኑና ባተያዩ መጠየፋንና አለመውደዱን አውቀውበታል። ነገር ግን አወዛዝተውና ሆዱን በገንፎ ነርተው ለገዢ ሳያሳዩት ብዙ ገንዘብ እንዲያስነችፋቸው ያውቃሉና እያደናቆሩ፣ ምንም ቢል በዚያ በሚገማ ስብ ሁለንተናውን በካከሉት። ዋሕድ ግን እንደማይተዉት ባወቀ ጊዜ ተረታና ዝም አላቸው። ደግሞም ጣመኑ እንዲለቀውና ያ የተገጣጠበው በውል እንዲድን ብለው ለሱ ደግ ውለታ መዋላቸው መስሎታል። «ወይ ግሩም! ወይ ግሩም! » እንዴት የእግዚአብሔር እንግዳ የተወደደበት አገር ነው" እያለ አገር ይመርቃል። ወይ አለመተዋወቅ!!

እነዚሁ ያሳደሩት ሰዎች ወደ ደረቅ ረፋዱ ሲሆን ዋሕድን ባይን ጥቅሻ "ተነስ ተከተለን" አሉትና ታጥቀው ወጡ። እሱም እንደ መልካም ሽርሽር "እሺ" ብሎ በመካከላቸው አድርገውት ሲሄዱ ሲሄዱ ካንድ ትልቅ መንደር ደረሱ። ያ መንደር በትልቅ እርድ እንደ አንድ ምሽግ ተከልሏል (ታጥሯል)። በዚያ እርድ ውስጥ ትልቅ የደንጊያ ቅጥር ተክቦበታል። በዚያም እድሞ ላይ የአጋምና የግራር እሾህ ሰው እንዳይዘለው ተመስጎበታል። ከዚያ መካከል ትልልቅ ሰቀላ ቤትና ሁለት ትልልቅ ቤተ ንጉሥ አዳራሽ ተገጥግጦበታል። የዚያ ቅጥር በር ሁለት ብቻ ነው። ከሁለቱ በር አንዱ ጠባብ ነው። አንደኛው በፈረስ ተዛንቶ ለመግባት የተመቸ ነው።

ከዚያው ካውራው በር አንድ ጥብልያኮስን የመሰለ ሻንቅላ ደረቱ በክንድ የሚሠፈር የመሰለ፣ ቁመቱ ዐምድ የመሰለ፣ ዓይኑ እንሶስላ የሞቀ የመሰለ፣ አፍንጫው መርግ የተንከባለለበት የመሰለ፣ የመዳብና የቆርቆሮ አንባሩን፣ የዝሆን መዳፍ በመሰለ ክንዱ ላይ ደርድሮ፣ ባራት ማእዘን የተሳለ ጉዶውን የመስከረምን

ዘተር ዱባ በመሰለ፣ በራቁት ሆዱ ላይ አሽንጦ በቀኝ እጁ ጎመዱን አጠንክሮ ይዞ ያልተፈቀደለትን ሰው ለመከልከል ተገትሮ ነበር። ዋሕድ ይኸን አይቶ "ያገሩ ገኸ ያለበት ይሆናል" እያለ ሲያስብ፣ እነዚያ ይዘውት የመጡት ሰዎች ለባለቤቱ ልከው ኖሮ ግቡ ተባሉ። በመካከል አድርገውት ተቅጥሩ እንደገቡ በዚያም እንደእርሱ ለመሸጥ የመጡትን፣ የሚያለቅሱም የሚተክዙም ሰዎች ነበሩባቸውና በሰዎች እየተከበቡ እንደእርሱ ሲገቡ ዋሕድ አየ። ከዚህ ወዲያ ግን ሰውነቱ ጠረጠረበት። ያ ሁሉ መከብከቡ ለቅንነት አለመሆኑን ዐወቀው። ነገር ግን መጨረሻውን ለማየት ዝም ብሎ ይከተል ጀመር። መሆንማ ነገሩንስ ቢያውቅ ብቻውን ታረመኔ መካከል ሆኖ ምን ሊያደረግ ይችላል? ባረመኔ እጅ ተይዞ ቋንቋቸውን እንኳ አያውቅ። እንደ ፋሲካ በግ ባይኑ ዝም ብሎ መቀላወጥ ብቻ ሆነ። ያው ትልቅ ቅጥር፣ ያው ሁሉ ምሽግ፣ ያው ሁሉ የአጋም እሾህ፣ ያ ሁሉ ጥንካሬ ያንድ የትልቅ የባሪያ ነጋዴ ቤት ኑሯል። ያ እየተያዘ የሚመጣው ባሪያ እየዘለለ በሌትም ሆነ በቀን እንዳይጠፋና እንዳያመልጥ ኖሯል የታጠረው።

ያ ዋናው የባሪያ ነጋዴ ታዳራሹ ወጣና ለመሸጥ ከተሰበሰበው ሰው ዋሕድም ታለበት መካከል ሆነና እየዞረ ያይ ዋጋውንም ይጠይቅ ጀመር። እንዲህ እንዲህ ሲል ተዋሕድ ደረሰ። እንደ መልካም ወጌሻ እያገላበጠ ክንዱንም እግሩንም እንደ ልጅ ጥርስ እያነቃነቀ ያይ ጀመር። ካመጡት ሰዎች ጋር የዋጋውን ነገር ጨርሶ ብር ቆጥሮ ሲሰጥና ሲቀባበሉ ዋሕድ እንደ እማኝ ሆኖ ሲያስተውል ዋለና መሸጡንና ባሪያነቱን ዐወቀ። እነዚያ የእግዜር እንግዳ አክባሪዎችም ወርቅና ብራቸውን በዋሕድ ጫንቃ ያፈሩትን እያሆንጫሆጩ ወደ ቤታቸው ተመለሱ። ዋሕድም ከአዲሱ ጌታው ጋር ቀረ። አዲሱ ጌታው ግን እንደ እውነቱ ለዋሕድ ክፉ ሰውም አልሆነበትም፤ ይልቁንም በውቃቢውና በመልኩ በጠባዩ በለጋነቱም ወደደውና አልነግድበትም ብሎ ተገዛ ልጆቹ ጋር እንደ ቤት ልጅ እንዲቀመጥና ሥራ እንዳይሰራ ፈቀደ።

ዋሕድም ምንም በሰው እጅ ቢሆን "ዘመዶቼንና ያን ደግ አድራጊዬን ነጋዴ ሳላይ እንደምን ክርስቶስ ታረመኔ ቤት ያስቀረኝ" እያለ ያስብ ነበር። ሲኖር ሲኖር ግን ከዚያው ቤት ብዙ ክርስቲያኖች ተሽጠው ባሪያ ሁነው ያለበቱን ጌታ እያገለገሉ ሲኖሩ በቋንቋቸው ዐወቃቸውና ይቀርባቸው ጀመር። አዩኝ አላዩኝ እያለ እየፈራ የተሸጡበትን ጊዜና አገራቸውን ስማቸውንም ጠይቆ አወቀ።

ተነዚያው መካከል እንዳጋጣሚ ሁሉ የእነዚያን ነጋዴ ደብድቦ ጥሎት ተሄደበት ስፍራ አንስተው ያዳኑትን ሰዎች ልጅ እንደ እርሱው መሸጡንና ስሙን ነግረውት ነበርና፤ እርሱ በገዛ አንደበቱ ስሙንም አገሩንም አሻሻጡንም ቢነግረው ዐወቀው።

እጅግም ደስ አለው። ተዚህ በኋላ ዋሕድም ተቤቱ ታሞ መዳኑን የናት አባቱንም ወሬ በእርሱ ነገር ዘወትር መላቀሳቸውን ነገረው። ከዚያ ወዲያ ግን ሁለቱ በፍቅር ተጠመዱ፣ አንድ አካል አንድ አምሳል ሆኑ። ምሥጢራቸውም ተስፋቸውም አንድ ሆነ፣ ወዳገራቸውም ለመግባት አርቀው እያሰቡ በተስፋ ይኖሩ ጀመር።

ዋሕድ ከቤቱ ከወጣ ዓመት ሆኖት ነበርና እናትና አባቱ፣ እኅቱም ወዴት እንደሄደ ባለማወቃቸው “ደብዛው ጠፋ” ብለው ገምተዋል። ስለዚህ ሲላቀሱ ባጁ ከረሙ። በኋላ ግን የዋሕድ አባት “ልጄ ጠፍቶ ሲቀር ዝም ብዬ ከሞቀ ቤቴ እቀመጣለሁ፤ ሄጄ በየትም ብዬ ልፈልገው እንጂ” አለና ያ ደግ ነጋዴ ከተሸጠበት ባርነት ባወጣው ጊዜ ላገሩ መመለሻ የሰደደለትን ፈረስ ጭኖ ስንቁንም ከደኅራዩ ወድሎ ተነሣ። ነገር ግን አንድ የሚከተለው ሰው አልነበረም። በጦርነቱ ከአሽከሮቹ እኩሌቶቹ ተፈቱ እየተጣበሱ አለቁ፣ እኩሌቶቹም እንደእርሱ ተማርከው ተሸጠዋል። እርሱም አገሩን ቢመለስ ሰዉ አልቆ ንጉሡ ሙቶ ከብቱ ተነድቶ መሬቱ ጠፍ ሆኖ ቆይቶ በድኅነት ላይ ወድቋል። ሴት ልጁ ጦቢያ ብቻውን ለመሄድ እንደተነሣ ባየች ጊዜ በወጣበት ጠፍቶ እንደ ወንድሟ እንደ ዋሕድ እንዳይቀርባት ፈርታ ታለቅስ ጀመር፤ ቀጥላም “አባየዋ፣ አንተ በጌትነት የኖርህ እንዴት አላንድ ሰው ብቻህን ለመሄድ ይቻልሃል? ፈረስህንስ ማን ሣር አጭዶ ያበላልሃል? ውኃ ማን በጊዜው ያጠጣልሃል? አሁንም እባክህ ልከተልህ ትተኸኝ አትሂድ፣ ባይሆን እንኳ አፍህን አካፍትሃለሁ፤ ፈረሱንም በለኮው ይዤ ተመስክ ላይ አግጥልሀለሁ፤ ምንም ቢሆን ጥለኸኝ አትሂድ” እያለች አልቅሳ ነገረችው። እርሱ ግን የእርሷን ጭንቀት፣ የእርሷን ጥበት ባየ ጊዜ እጅግ አዘነና እንደእርስዋው እያለቀሰ “ልጄ ሐሳብሽ የማይሳካ የማይወጠን ነው፤ አንቺ ሴት ልጅ ገና ጮርቃ ነሽ፤ አንቺን ፀሐይና ብርድ አግኝቶሽ፣ መንገድ መትቶሽ፣ ውኃ ጥማትና ርኀብ ተጨምሮብሽ እንዴት ችለሽ ከእኔ ጋር አገር ላገር መዞር ይሆንልሻል? አይሆንም አትምጪ” አለና ከለከላት። ጦቢያ ግን “አይሆንም አልቀርም” እያለች እያለቀሰች ለመነችው። አባትዬው ግን ነገሩን አይቶ ጠንክሮ እንቢ በማለት “እንኳን ታግዢኝ ይልቁንም ትደክሚና ተመንገድ ወንድምሽን ዋሕድን እንዳልፈልግ ታደክሚኛለሽ” አላት። ደግሞም “ጦቢያ ገና አንቺ ለጋ ቀምበጥ ልጅ ነሽ ተከብክበሽ፣ በጌትነት ጠጁ ተጉሮሮሽ፣ ብርሌው ከጅሽ ሳይለይ ያደግሽ ነሽ። አሁን ጠጁ ቢቀር ውኃ አጥተሽ፣ ስጋጃና ወላንሳ በረገጥሽበት እግርሽ እሾህ አሜከላ አቃቅማ የፀሐይ ረሞጫ ረግጠሽበት እንዴት ትችይና ትመጫለሽ? አሁንም ዐርፈሽ ተናትሽ ጋር ቅሪ” ብሏት ሊስማትና ሊነሳ በሆነ ጊዜ ጦቢያ ይልቁንም ከንዱን ተጠማጥማ ይዛ እያለቀሰች “አባዬ ለእኔ አታስብ እንኳን ድህነት ጌትነት ይለመዳል፤ ሁሉንም ልጅ ነኝና

እለምዳለሁ፤ ደግሞም ባለጌ ጌታ ሲሆን አያውቅበትም እንጂ፣ ሀብታም የጨዋ ልጅ ቢያጣም ድህነትና መከራም አይከፋበትም፤ ቶሎ ይለምደዋል። እኔም ቶሎ ለመልመድ አይሳነኝምና ውሰደኝ ደግሞም ለእኔ ከዚህ ቀርቼ ባንተ በደጉ አባቴና በምወደው ወንድሜ አሳብ ተመጨነቅ ካንተ ጋር አገር ላገር እየዞርሁ የሆንሁትን ብሆን ይሻለኛል" አለችው። በዚህ ጊዜ አባትዮው "እኔስ እስኪ አንቺ እንዳልሽው እሺ ብዬ ልውሰድሽ፤ ኧረ ላንቺ ምን ይመስልሻል? እናትሽን ለብቻዋ ከአንድ ቤት ዘግተንባት ስንሄድ? ይኸን ነገር ብናደርግ ለሰውስ ምን ይመስለዋል?" ብሎ በተናገረ ጊዜ እናቲቱ ቀጠል አድርጋ "ሰዉም ያለውን ይበል፣ ለእኔ አታስብ፤ ደግሞም የምታስተዳድረኝ አንዲት ባልቴት መሳይ አላጣም፤ ብቻ እኔ የምፈራው ልጅቱ ካንተ ጋር መገሥገሥ ያልተቻላት እንደሆነ ነው እንጂ፤ እርሷ ተተቻላት ነው ለእኔ መታሰቡ፤ ለእኔ የሚያሳስብ ነገር የለም አታስብ።" አለችና ወደ ልጅዋ ዞራ "እውነት አሁን ልጄ እርግጥ ጉልበትሽን ትተማመኝዋለሽን?" ስትል ጠየቀቻት። ጦቢያም ቶሎ ብላ "አዎን እናቴ አንቺ ተፈቀድሽልኝ፤ አንቺ ለብቻሽ መሆን ታልሠጋሽ መሄድ ይሆንልኛል፤ አባቴን ብቻ እሺ እንዲለኝ አግዢኝ" አለቻት። ገና አባቷ "ይሁን አይሁን" ብሎ ሳይመልስላት፤ ጦቢያ አሳቡን አቋረጠችና "አባቴ አንድ ነገር ብቻ" አለችና ልትናገረው አፍራ ሳትጨርሰው እንደመዳዳት አለች። በዚህ ጊዜ ማፈሯን አባቷ ዐወቀና "ምን ሆንሽ ልጄ እስኪ ንገሪኝ" አለ። ጦቢያ አነሣችና "አባዬ ካንድ ሁለት ይሻላል፤ የሰው ጠላት አንበሳ እንኳ ሁለት ሰው ሲያይ ያከብራል፣ አይናካም። ነገር ግን ሁለቱም ሰዎች ወንድ ቢሆኑ ነው የሚፈሩ እንጂ ጠላት ሴትን ከቁም ነገር አይጥፋትም። ስለዚህ አንተን ስከተል የሴት ልብስ ቀርቶብኝ እንደ እንደ ብለብስ ይሻል ነበር" እያለች የምትለውን ለመጨረስ አፈረችና አንገቷን ወደ ምድር አዘነበለች። አባቷ አወቀባትና "እንደ እንደ የምትይው እንደ ወንድ ልልበስና ልከተልህ ማለትሽ ይሆን?" ሲል ጠየቃት። ጦቢያም አፍራ ይልቁንም በሁለት እጆቿ ፊቷን ጋርዳ ቃሏን አቅጥና "ይሻል መስሎኝ ነዋ አባቴ" አለች። አባትዮውም እርሷ እርግጥ በመነሣቷ እንደ ቆረጠች አየና "እሺ ተወደድሽው ምን ይደረጋል? ተሰናጂና ቶሎ እንነሳ" አለ። ጦቢያ ደስ አላትና የሐር ነዶ የመሰለ ሳዱላዋን እንደ ወንድ ተቆርጣ የወንድ ሙሉ ልብስ ለበሰችና እናቷን አይዞሽ ብላ አረጋግታ ሁሉም ተሰነባብተው ተለያዩ።

እንግዲህ አባትና ልጁ እርስ በርሳቸው እየተደጋገፉና እየተበረታቱ ሲሄዱ ሲሄዱ፣ ተመሸባቸው ሲያድሩ፣ ሲጓዙ ሲጓዙ ተመሸባቸው ሲያድሩ፣ ዋሕድ ሲነሳ እሄድበታለሁ ብሎ ካመለከታቸው ከተማ ደረሱ። ከዚያው እንደ ደረሱ ግን ማንን ይጠይቁ? ብቻ በያደባባዩም በየገበያውም እየዞሩ ቢፈልጉ ዋሕድ ወዴት ይገኝ

እንዲያው ተረት ሆነባቸው። በኋላ ግን “ዋሕድ ያንን ደግ ሀብታም ነጋዴ ለመፈለግ ነውና የሄደው ያገሩ ሁሉ ነጋዴ ወደሲናር ከሚያልፍበት በር እንቀመጥና የሚወጣ የሚወርደውን ነጋዴ ሁሉ እንመልከት፤ ዋሕድ ወይ ያን ነጋዴ አግኝቶት አብሮ ከምስር ሲመለስ እናየዋለን” አሉና ይኸን ተስፋ አድርገው ወደዚያ ትልቅ በር እየጠየቁ ሲሄዱ መንገዱ ጠልፎ ወዳላሰቡበት ወሰዳቸው። አንድ አዳ መንገድ ይዞ ሲያሳስብ አርቆ ከወይና ደጋው ወደ ቆላው ሲል ከማያውቁት አገር አግብቶ ደነጎራቸው። “ከዚህ በየት በወጣነ” እያሉ ሲዳከሩ ሲዳከሩ ከአንድ ለም ደጋ ደረሱ፣ ያንም ደጋ አሻግረው ሲያዩት እጅግ አምሮ ለምቶ ልብ ያስፈነድቅ ነበር። ጊዜው መኸር ነው። ባንድ ወገን ክምሩ፣ ባንድ ወገን አጨዳው፣ ባንድ ወገን እሸቱ፣ ባንድ ወገን ዝርዝሩ፣ ባንድ ወገን ቡቃያው፣ ባንድ ወገን የበልጉ ዘር እየሆነ አቀማመጡን ሲያዩት ሳይበሉ የሚያጠግብ ይመስል ነበር። ጦቢያ ያንን ሁሉ ባየች ጊዜ እንደገና ጠነከረች። አባቷም ደስ እያለው ጥንካሬዋን ባየ ጊዜ መቼም ገና ከቤትዋ ስትነሳ ጦቢያ የሴት ልብሷን አውልቃ ጥላ የወንድ ሱሪ አጥልቃ የወንድ እጀጠባብና ኩራቢዋን ለብሳ፣ በዚያው ላይ በባሕር ዐረብ የተዘመዘመ ማለፊያ የዳንግሌ በግ አጎዛ ደርባ አሸከፋ ነውና የወጣች “ምን ልብስሽ ብቻ ልጄ ጉልበትሽም የወንዶችን ሆነ እንጂ” እያለ ይተርትባታል። እንደውነቱም ጦቢያ እጅግ በርትታ አንድ ጊዜም ደከመኝ አትል ነበር። ከዚያው ቆላ አፋፍ ብቅ ብለው ተደጋው መጀመሪያ ተቀምጠው የደጋው አብራጃ በፊታቸው ላይ ሽው ሽው እያለባቸው የዚያን አገር አዝመራ ልማትና ማማር እያዩ ሲያደንቁ ጀንበር ተቆለቆለችባቸውና ወደ መንደር ተጠግተው ለማደር ተነስተው ሄዱ። “ከመንደር አርፈን አድረን ወደ ስናርም ወደ ምስርም ወደ ባሕርም የሚሄዱ ነጋዴ ሁሉ የሚሰፍርበት ዋና አንድ በር አለና ከዚያ የሚያደርሰንን መንገድ በውል ስንጠይቅ አድረን ተነግሁ ቀደም ብለን ተነስተን እንጓዛለን» ነበር ሐሳባቸው። ምክራቸውንም በዚህ አቁመው ታንዱ መንደር ገቡና ከአንደኛው ቤት ቀርበው “እባካችሁ አሳድሩን ፈረሳችንንም ወደ ጋጥ አስጠጉልን” ብለው ለመኑ። አንድ ስታለቅስ የነበረች ሴት ፈጠን አለችና እንባዋን ጥርግርግ እያደረገች ብቅ አለች። ወዲያውም ተቻኩላ “ተወዴት መጣችሁ? ምን ወሬ አለ?” አለችና ጠየቀች። እርሷም የቤቱ ባለቤት ኑራለች። “የጦቢያ አባትም ምንም ወሬ አልሰማን፣ የመጣንበትም በዚሁ በኩል ነው” አለ በጁ የመጡበትን እየጠነቆለና እያሳየ። ያችው ባለቤት እንደገና እያለቀሰች “ምን ከፋ ግቡና ዕረፉ ፈረሱም ተኞቹ ጋር ሲበላ ያድራል እናንተም እኛ እንደሆነ ሆናችሁ ታድራላችሁ፤ ደግሞም እኛው በቤታችን እስትናዝበት ድረስ የእግዚአብሔር እንግዳ እንደልቡ ቢያድርበት ይቻለዋል፤ ተነገ ተሠልስት ወዲያ ግን ማን ያውቃል? ወይ እስከኛውም

አናዝዝበትም ይሆናል፤ የሚመጣው አረመኔ ወይ ያቃጥለዋል ወይ እንደሠራው ገብቶ ይዘጠርበታል። ወይ ቤቴ! ወይ ንብረቴ ሆይ! ደጊቱ ቤቴ እንዳልበላሁብሽ ዓለም እንዳላየሁብሽ ሁሉ" አለችና በመጨረሻ ጧ ብላ አለቀሰች። በዚህ መካከል እንደገና ልብ ስታደርግ ጊዜ እንግዶች የምታለቅስበትን ነገር አለማወቃቸውንና አክብረው ፈርተው ነገሩን እንዳልጠየቋት ዐወቀችና። "ምን ይሉኝ ይሆን እኚህ እንግዶች" አለችና እንባዋን ባይበሉባዋ እየጠራረገች "አይዟችሁ! ነገሩ ወዲህ ነው! እህል ተቀመሳችሁ በኋላ ታውቁታላችሁ ደግሞም ለመልካም ወሬ ነው እንጂ ለክፉ ነገር ቸኩሎ መንገር ደግም አይደል" ብላ አረጋግታቸውና አፅናንታቸው ወደ ስራዋ ተጋባች።

ጦቢያ ይኸ ሁሉ ሲሆን ደንግጣ አባቷን ውስጥ ለውስጥ "ይኸን ቤት ለቀን እንሂድ" ትለው ነበር። በዚህ ጊዜ አንድ ወንድ ጥቂት ከነሱ ራቅ ብሎ ፈዝዞ አሳብ አደንዝዞት አይናገር ምን አይል አገጩን ተጉልበቱ ጥሎ ተብርኩማ ላይ ተቀምጦ በጨንገር መሳይ ምድር እየቆረቆረና እንደጅግራ እየጫጫረ ትቢያውን እያስነሣ ይህ ሁሉ ሲሆን እነዚያን እንግዶች አላነጋገራቸውም ነበር። ኋላ ግን አንድ እንቅብ ትንፋሹን ለቀቀና አንገቱን አቀና፤ ወዲያውም ተነሥቶ ወደ እንግዶቹ ቀረበና "ወንድሞቼ እስካሁን ዝም በማለቴና ሰላምታ ሳልሰጣችሁ በመቆየቴ አትዘኑብኝ። አሳብ ገብቶብኝ ልቤ ተሰቅሎ ነው" አለና ቀጥሎም "ወዴት ለመሄድ ታስባላችሁ? ተወዴትስ መጣችሁ?" ሲል ጠየቃቸው እነርሱም የመጡበትን ጉዳይና የሚሄዱበትን በነገሩት ጊዜ "አረመኔ ሲመጣ ወደዚያው ወደመጣችሁበት እንደመሸሽ ሁሉ እንዴት እየገፋችሁ /ወደፊት/ ወዳረመኔው ትሄዳላችሁ? ዓይናችሁ እያየ ከእሳትና ከጉድጓድ መውደቅ አይሆንባችሁምን?" አላቸው። አባትና ልጁም ደነገጡና "ኧረ ነገሩ ምንድነው? እኛ እኮ ነገሩን አላወቅነውም፤ እባክዎን ጌታው ነገሩን ይንገሩን" አሉና ለመኑት። "እንግዲያው ነገሩን ታላወቃችሁስ ይኸው አንድ አመት ከመንፈቅ ሆነ፣ ያገራችን ሰው ታረመኔ ተዋግቶ ድል ተሆነ። አገሩም ጠፋ ንጉሣችንም በሀዘን ሞተ። ስለዚህ አገራችን ንጉሥ ጠፋበት አውራም አጣ። አንድ አውራ አጣ። አንድ አውራ ተጠፋ ወታደር እንደንብ ነው፤ አላውራ አለንጉሥ አይቆምም። ይኸንን ወሬ በሰማ ጊዜ ያረመኔው ንጉሥ ሰውን አስከትቶ ምሳባሐውን በግመል ጭኖ አገራችንን ለመውረር ክርስቲያኑን ሁሉ በእርሱ ሃይማኖት አስገብቶ ሊያስፈታ ያላመነውንም ሊፈጅ ይኸው ወዳገራችን ይገሰግሳል። ተነገ በስቲያ ተዚያ ሳይደርስ አይቀርም ይባላል። ደግሞም አደጋ ሊጥል አይፈልግም ተዋጊ ተከላካይ አለመኖሩን ዐውቆ "መቼም የሚያመልጠኝ የለ፤ አገሩ ሁሉ በጄ ነው" እያለ እንደገዛ ቤቱ ሊገባ ተዛንቶ ይጓዛል አሉ" ብሎ ይህን አጫወታቸው። ጦቢያም አባቷም ክስል

ብለው ደንግጠው መነጋገር አቃታቸው። ይልቁንም አባትዬው የልጁን የጦቢያን ነገር ለእርሱ ብላ መጥታ ካረመኔ እጅ መውደቋን ባሰበ ጊዜ እንባ እያነቀው ንግግሩን ተወው። ለዚያው ለቤቱ ባለቤትም ከጦርነቱ መኖሩን ተማርኮ መሸጡንና እንደገና አገሩ መግባቱን ለማጫወት ቢቃጣ እንባው እያቋረጠው የማይሆንለት ሆነ።

ባለቤቲቱ መጣችና ባሏ ተንግዶች ጋራ እንዲገባ ለራት ጠራችና ተያይዘው አንድነት ገቡ። ምግባቸውም እጅግ አለመጠን አምሮ አለልክ አቁልቋዩ እስቲሰበር ድረስ እንጀራ ተጥሎ አንፊላው፣ ዝግኑ፣ እምሱ፣ ዓሳው፣ ዶሮው፣ እርጎው፣ እየተነባበረ ተደርድሮ አሳላፊዎችም ተሰልፈው ቆመው ፋናውም በየማዕዘኑ ተተክሎ፣ የሙሽራ ቤት መስሎ ተሰናድቶ ይጠብቃቸው ነበር። ቤተሰቡ ብዙ ነበር። ጠላ ቤቱም፣ ስጋ ቤቱም፣ ወጥ ቤቱም፣ አስታጣቢውም፣ ፋና ወጊውም ሁሉም እየስራው እፍን እፍን ይል ነበር። ጦቢያና አባቷ ይኸን ሁሉ ጌትነት ባዩ ጊዜ ደነቃቸውና ያች ስታለቅስ የነበረችውና ወጥታ የተቀበለቻቸው ሴት ያም ሲያነጋግራቸው ያመሸው ሰው እውነት የዚያ ቤት ባለቤቶች አልመሰሏቸውም። ደግሞም ፊት የማይንቀሳቀስ የነበረው ቤተ ሰብ ሁሉ በየሥራው ተሠማርቶ ኑሮ፣ የግብር ጊዜ ብቻ ከየት መጣ ሳይሉት በዚያም በዚያም ይትመከመክ ጀመር። ያገር ቤት ጎናዴ ተቤቱ ሲገቡ ነው እንጂ ከውጭ ልብሱ አልባሌ ነውና ማንም ይህንኑ ነው የሚመስል፤ እንዲሁም ለእንግዶቹ ተውጭ ሳይመስሏቸው ከቤት ቢገቡ ነገሩ ሁሉ ተለዋወጠባቸውና ተደናገራቸው። ባለቤቶቹ ግን ተፊቱ ፍትፍቱ፤ ተፍትፍቱ ፊቱ እንዲሉ ሁሉ ተምግቡ ጠባያቸው አፈሌነታቸው /ተጨዋችነታቸው/ ትህትናቸው ይበልጥ ነበርና ጦቢያም አባቷም ተዛንተው በሉ ጠጡ።

ይሁንና ሌሊቱን እንቅልፍ እንዴት ብሎ ይውሰዳቸው ያረመኔው አመጣጥ እየታሰባት "እንዴት እናድርግ? ወዴቱንስ መልሰን እንሸሽ?" እየተባባሉ ምንም ቀኑን ሁሉ ሲጓዙ ውለው ቢደክሙ ይኸን ብቻ ሲያስቡ እንቅልፍ ባይናቸው ሳይኩሉ አደሩና ጎሕ እንደመቅደድ ሲል ተነሡ። ፈረሳቸውን አስጫኑና እነዚያ ያደሩባቸው ሰዎች እንጀራውን፣ ዳቦ ቆሎውን ባገልግል፤ ጠጁን በቀንድ አድርገው አሰናድተው ሰጥተዋቸው ተውዲላው ላይ ወደሉና ባለቤቶቹን መራርቀው ሊጓዙ ተነሡ። ነገር ግን ወዴት መልሰው ይሽሹ? ካውራው መንገድ ሆነው "የቱን መልሰን እንሂድ? ወደኋላችን ተመልሰን ወዳንዱ ቆላ እንግባና እንሸሽግ" ሲሉ ገና አንዱን ነገር ሳይቆርጡ በቀኝም በግራም በፊትም በኋላም አገሩን ጢስ እንደ ጉም ያላብሰው ጀመር። አረመኔው ያፋቀ ያፋቀውን ወንድ ባፎቁ (በጎራዴ) እየጎመደ ሴትና ልጁን

እየማረከ፤ ቤትና ከምሩን እያቃጠለ፤ ከብቱን ፈረስ በቅሎውን እያጋፈፈ እየነዳ ዝርዝሩን እየቀጨ ለወገኑ እያበላ፤ የቀረውንም በግሩ እየዳሸ፤ ቤተክርስቲያኑን እያቃጠለ፤ ዱሩን እየመደመደ፤ አታክልቱን እየቆረጠ እየዘነፈጠ፣ ለጎጀው እያደረገ መምጣቱ ኑሯል። ይኸን ምጣት ባየ ጊዜ የጦቢያ አባት ልጁን ጦቢያን እንቅ አድርጎ ከደረቱ አስጠጋ ያዘና “ልጄ አካሌ ወዳጄ! ለእኔ ብለሽ መጣሽና ተመከራ ላይ ወደቅሽብኝ ካረመኔ እጅ ልትገቢብኝ ሆነ፣ እንግዲህ ወዴት ላድርስሽ? እኔስ ተማርኬ ብሸጥ እግዚአብሔር መልሶ በታምሩ አወጣኝ። ደግሞም የገዛኝ አረመኔ ገንዘብ አይቶ ለቀቀኝ። አንችን ያገኘ ሰውማ ያንቺን መልክ አይቶ እንዳንች ያለ ወዘላ በዚህ ዓለም ታይቶ አይታወቅ እንደምን ይለቅልኛል? በቁመቱ ሙሉ ወርቅና ብር፤ አልማዝና ሉል ቢሰጡም አይለቅሽ” እያለ ያለቅስ ጀመር። ጭንቀቱ ደግሞ በሁለት በኩል ሆነበት። ጦቢያ የሴት ልብሷን ጥላ እንደ ወንድ ለብሳ ነውና የተከተለችው አረመኔው ወንድ ወንዱን አይምርም እንደደረሰ በፈንዜ እያረደ ይጥለዋል ተብሏልና፤ ልብሷን አይቶ ወንድ ነው ብሎ እንዳይገድልበት ፈራ። ምንም በዚያን ጊዜ የሴት ልብስ ባያገኝላት የሴት ልብስ እንዳያለብሳት አረመኔ፣ ሴት አይቶ እንዳይለቅ የታወቀ ነውና ይዞ አገሩን እንዳይወስድበትና ከዚያ አረመኔ አገር ለዘለዓለም እንዳትቀርበት ፈራ። አንዱ ችግር ከአንዱ እየባሰ ስለታየው ያለቅስ ጀመር። ጦቢያ ግን ምንም የነገሩን መክበድ ብታውቅ እርሷም እንደርሱ እንዳባቷ ውኃ እየሆነችና እያለቀሰች ታረጋጋው ጀመር። “አባዬዋ፣ እግዚአብሔር ከዚህ ቀደም ተአምር ሰርቶ አንተን ተባርነት አውጥቶ ደስ አሰኘን፤ እግዚአብሔር የማይጨርሰውን ነገር አይጀምርም። አሁንም እርሱ እንደጀመረ በታምሩና በምህረቱ ያድነናል፤ ተክፉ ነገር ይሰውረናል፤ አሁንም አትባባ። አይዞህ! ክርስቶስ አላንድ ጊዜ ተአምር አይሰራም ይመስልሃልን? እርሱ አይደከም፣ አይሰለች፣ አይረሳ፣ አያረጅ፣ አይከሳ፣ አይወፍር፣ መቼም አንድ ነውና ወረት የለበት፣ ተወደደ አይጠላ። አሁንም አይዞህ! አሳባችንን ለእርሱ እንተውለት” አለችና አረጋጋችው። በዚህ ጊዜ ግን ገና እነርሱ የሚሸሹበትን ስፍራ ሳይመርጡና አንድ ነገር ሳይቆርጡ በመካከል ቤት አገሩን የሚያቃጥለው አረመኔ መቃረቡ በጢሱ ይታወቅ ጀመር። ያደሩበት መንደር ሰው ያን ጢስ እያየ ተሸበረና መሸሽ ጀመረ። ጎበዝ ጎበዙ አሮጌ አሮጌውን፣ ባልቴት ባልቴቱን፣ ሩጦ ለማምለጥ የማይቻለውን ሰው በጀርባው እያዘለ መሮጥ የሚቻለውን ልጅ ልጁን በፊቱ እያስቀደመ እየገፋፋ እያስፈራራ፤ ሴት ሴቱ ጨቅላ ጨቅላውን ልጅ በደረቱ ላይ እየጣፈ በጀርባውም እያዘለ፣ በጎንም ቢሆን እያሟቀለ፣ በርታ በርታ ያለው ሽማግሌ መሮጥ ያቃተውን ደቦል ልጅ በጫንቃው አሸኮኮ እያለ መቀዳደም መሮጥ በየገደሉ በየዱሩ በየጉሩ በየጢሻው መግባትና

መሰማራት ሆነ። ጦቢያና አባቷም ይኸን ባዩ ጊዜ “እንዲያው ቁሞ ተመያዝ እስቲደርስብን ድረስ ምንም ባናመልጥ እንሸሽ እንደሰዉ እንምሰል” አሉና የፈረሳቸውን ቅናት አጠባበቁና ለመኮልኮሉ ጦቢያ አልለመደችምና አባትዮው ተኮርቻው ጦቢያ ተጎረዴው ወዲያ ሆኑና አስነስተው ሲጋልቡ ሲገርፉ ሲኮለኩሉ ከትልቅ ሜዳ ላይ ደረሱ። ከዚያ ወረዱና ጥቂት የፈረሳቸውን ልጓም ለቀው አስተነፈሱትና እነርሱም ዐርፈው እንደገና ኋላ ኋላቸውን እየዞሩ እያዩ ይጋልቡ ጀመር። ፈረሱም እያላበው እንደገና ጉልበት ተሰማው። የጌቶቹን ብሶት የጌቶቹን ማፋጠን የጠላታቸውን መድረስ ያወቀ መሰለ። ለራሱ ቀርቶ ለእነርሱ ያሰበ መስሎ ለዘብ አድርገው “ደንገላሳ እንጋልብህ” ቢሉት ልጓም እየገፋ ይግል ጀመር። ሲሉ ሲሉ እየዞሩ ቢመለከቱት ነገሩ እንዳልሰላ አዩት። ሂደው ሂደው የሚደርሱበትን አጡት እንኳን ሌላ የሚሸጡበት አገር ወሬሳ የማይመታው ቆላ ይቅርና አንድ እንኳ ቁጥቋጦ ግንባራቸውን የሚተግኑበት ቅጠል ከዚያ ሜዳ አልነበረም። ከዚያ እፍ ካለ ሜዳ መካከል አንድ ብቻውን እንደ ዐምድ የቆመ ኮረብታ ነበረ። ተላዩ ግን ከሻፎ ከሻፎ ደንጊያ በቀር ምንም ዛፍና ቅጠል አልነበረበትም። እንኳን ሰው ሊደርስበት ሣርና ቅጠል ሊበቅልበት የተጠየፈው ይመስል ነበር፤ ብቻ ከጫፉ በነጭ ኩስ የተጨማለቀ አንድ ብክን ያለ ጎጆ የተውተፈተፈበት አሮጌ ቅራት ነበር። ይህን ላሞራው የማይነቀል እርስት ገዳሙ ኖሯል። ይኸን ኮረብታ ጦቢያ ባየች ጊዜ ላባቷ “አባዬ! ይኸ ወሬሳ የሚመታው ጦር መቼም ሁሉም በከብት ነው እንጂ በግር አይገሠግሥም። ከብት ያለው ሰው ሜዳ ሜዳውን ይጋልባል፤ መንደር መንደሩን ይዘርፋል እንጂ ሰውና ከብት እህል፣ ወርቅና ብር ከሌለበት ኮረብታ ያሞራ ኩስ ሊዘርፍ አይወጣም። ስለዚህ እኛም ከዚያ ወጥተን መዓቱን ብናሳልፈው ይሻላል።” አለችና ነገረችው፤ አባቷም “እውነትሽ ነው ልጄ ያሳድግሽ ይኸም አለና! እውነትሽ ነው፤ እንግዲያውስ ወደዚያው እንጋልብ” አለና ወደዚያው ገረፉ። ተኮረብታው ሥር እንደደረሱ የፈረሱ ነገር ቸገራቸው። ለገንዘብነቱም አይደል፤ እንዲያው ቤቴ ቤቴ ሲል እስቲያልበው ተሸክሞ ከዚያ አድርሷቸው እንደ ከፉ አድራጊ ለጅብ ጥለውት ስለመሄዳቸው ነው እንጂ። ታዲያ ይሁንና ለእርሱ ሲሉ እነርሱ ተመከራና ተሞት ሊወድቁ አይቻልም። እያዘኑ ልጋሙን ለቀው ወደሜዳው ገረፉና “እንደሻህ ሁን እንግዲህ የኛነትህ ቀረ፤ ባይሆን እንኳ ደህና ጌታ ይዘዝልህ” እያሉ አባትና ልጁ አቀበቱን ተያያዙት። አቀበቱ ግን ሰው ረግጦት አያውቅምና ስርጥ መንገድ እንኳ አልነበረበትም። እነርሱን በመሰላቸው አቋራጭ ሲሉ ሲሉ ሙትት ብለው ደክመው ተጫፉ ደረሱ። ከዚያም አርፈው የሚንጠባጠብ ወዛቸውን በልብሳቸው ጫፍ እየጠራረጉ ዙሪያውን ያዩ ጀመር።

መቼም አራቱም ማእዘን ዓይን እስተደረሰበት ድረስ ከዚያ ኮረብታ ጫፍ ሆኖ ቁልጭ ብሎ ይታይ ነበርና ወሬሳ የሚመታው ጦር መታየት ጀመረ። አባትና ልጁም “አቤት! አቤት! አውጣነ! አውጣነ!” እያሉ እግዜርን እየለመኑ ለፀሐዩ ጠዳል እጃቸውን ተግንባራቸው ላይ ጣል አድርገው ሲመለከቱ ሲመለከቱ አንዳንድ ጊዜም እየተነሡ ዓይናቸውን እስቲደክማቸው ሲያዩ ሲያዩ ወራሪው ተቃረበ። ከዚያ ተራራ ሥር የተውት ፈረስ ሣሩን እየነጫጨ ቀና እያለ ሰው ባይኑ ይፈቅዳል። ጌቶቹ ጭራሹን እንደተውት አላወቀም። ታሁን አሁን መጥተው ይወስዱኝ መስሎታል። ጦቢያ እያየችው ታዝናለች። ነገር ግን “ወረራው ሲደርስ ያየው እንደሆነ መሸሽጋችንን ያስታውቅብን ይሆን” እያለች ስታስብ ድሮ የፊታውራሪው ጦር ያሉበትን ኮረብታ ዙሪያውን አለበሰው። ያም ፈረሳቸው ከዚያው መካል ጠለቀና ጠፋ። ያባትና ልጁ ልብ ጭራሹን ይሸበር ደረታቸው ዱብ ዱብ ይል ጀመር። መቀመጣቸውም ቀረና እንዳይታዩ ተጋድመው አንገታቸውን ብቻ እንደ ኤሊ ብቅ ብቅ እያደረጉ ሆነ የሚያዩ። እንዲያው ቢፈሩ ነው እንጂ እነእርሱ ታሉበት አንድ ኮረምቱ ዝሆንም እሰከ ነጭ ጥርሱ ቁሞ እዩኝ ቢል ከሜዳው ላለ ሰው ዝንብ ይመስለው እንደሆነ ነው እንጂ ምንም ከዝንብ ልቆ አይታየውም ነበር። ጦቢያና አባቷ ግን እንሰማለን መስሏቸው ፈርተው ጉንፋናቸውን እንኳ በልብሳቸው አፋቸውን ለጉመው ነበር የሚስሉ። ያ የጥንት ደጃዝማች፣ የጥንት ጀግና የጦቢያው አባት ይኸ ሁሉ ፍርሀቱ ለልጁ ለጦቢያው ነው እንጂ፤ ለራሱ ፈርቶ አልነበረም። የሆነ ሆኖ ከሴት ጋር የዋለ ሴት ነውና የልቡን መሥራት እንደማይሆንለት ዐውቆ ወይኔን ብቻ ይዞ ተቀመጠ። ለዚያ ግንድ ታመድ ለሆነ ሠራዊት የሚመከት ታገሩ አንድም ሰው አልነበረም። ብቻ ወራሪው ዓይኑ የገመገመውን ከብቱ የቻለውን እጁ የመጠነውን ወርቅና ብር እየዘረፈ የቀረውን ቤቱንም እህሉንም ለማይጠግብ፣ በልቶም ምስጋና ለሌለው እሳት መስጠት መለገሥ ማለፍ መሄድ ብቻ ነው የነበር።” አዬ ለጋስነት! እንዲህ ነው መለገስ! የጨካኝ አረመኔ ልገሣ ሰው ያዳሙ ልጅ ሁሉ በራብ ሲያልቅ እህሉን ለእሳት ማብላት ከተራበው ሰው ታፉ እየነጠቁ ላልተራበው እሳት ማጉረስ የታዘዘውን ድኃ እያስወጡ ወደ ውርጭ እየገፉ ብርድ ለማይሰማው እሳት ቤቱን አዳራሹን የሞቀውን እልፍኝ መስጠት እጅግ የተዋበ ልግሥና ነው፤” እያለች ጦቢያ ታዝን ጀመር።

ጦቢያና አባቷ ይኸን ሁሉ ያያሉ ያስተውላሉ። ጦሩ በእዚያ ባሉበት ኮረብታ ጥግ እንደ ውኃ ሙላት እየገጠመ ይደርስና ከኮረብታው ሲደርስ ተሁለት እየተገመሰ ብቻ ያልፋል። ያን ኮረብታ ታለፈም ወዲያ እንደገና ይዋኃድና ይሄዳል ይዘርፋል፣ ይገፋል፣ ይገድላል፣ ይማርካል። ያ ኮረብታ ግን እንደ ትልቅ ደሴት ሆነና ተጎልቶ

አንድ ሰውም አቅንቶ የሚያየው አልነበረም። በኮረብታው ጥግ ያ ሁሉ ሰራዊት ሲሻገር ሲሻገር፣ ሲጓዝ ሲጓዝ፣ ቀኑን ሙሉ ዋለና የሚሻገረው ሰው ጥቂት እየሆነ ሄደ። ጦቢያ ታባቷ ጋ ስትማከር "እንግዲህ ጦሩ ተሻግሮ ማለቁ ነው መሰለኝ። እግዚአብሔር ከዚህ መዓት ሠውሮ ከአዳነን ከዚህ አድረን ስናበቃ ዶሮ ሲጮህ ተነስን ቁልቁለቱን ወርደን ጦሩ ወደመጣበት አቃንተን እንሂድ መቼም ጦሩ ወደፊት እንጂ ወደ ዘረፈው አገር አይመለስም። እውን አባባ" አለች። ገና እንዲህ ብላ እንደጨረሰች ተሩቅ ተሜዳ ጫፍ የሀምሌን ደመና የመሰለ ነገር ተሜዳው ጫፍ ጠቁሮ መታየት ጀመረ። አባትና ልጁ ምን ይሆን ሲሉ ቧሂት ያነሣችው የመሰለ አቧራ ቀጥ እያለ ይታያቸው ጀመር። የፊት አጀብ በፈረሱ ኮቴ የሚያስነሳው ትቢያ ኑሯል ሲል ሲል ይታይ ጀመር። ከሁለት የተከፈለ አጀብ ትልቅ መስሎ ይለይ ጀመር። ያን እያዩ አባትና ልጁ እንደገና አዘንና ድንጋጤ ገባባቸው ተስፋቸው እንደገና ተባነነ። እንደገና ወደ አምላክ ይማለሉ ይሳሉ ጀመር። አጀቡ ግን እያደር ይቀርብ ጀመር። ነጋሪቱና ቀንደ መለኸቱ ከነፋሱ ጋር እየተሳከረ ይሰማቸው ጀመር። በውል ወጀቡ በቀረበ ጊዜ የፈረሱ የበቅሎ መጣምር በነቻው የሰውም ጌጥ ከለቻው ራስ ወርቁ ወርቅ ኩፍታ አቁዳማ ቢተዋው አንፋሮው ወርቅ ለምዱ ጫሜው ጣፋው እንዲህ እንዲህ ያለው ጌጥ ከፀሐዩ ጋር እየተሳደበ ላይን ይገለምጥ ጀመር። ከእዚያ ከሁለት ከተከፈለው አጀብ መካከል ጥቂት ፈንጠር ብሎ ጥቂት ሰው ይታይ ጀመር። ንጉሡ ግራና ቀኝ ባለወርቅ ዝምዝም ባለወርቅ ጉብጉብ አጫዋች ሀር ጥላ ተይዞለት ከእርሱ አካል ይልቅ ወርቁ በከበዳት በቅሎ ተቀምጦ ከጥቂት ባለሟሎቹ ጋር እየተጫወተ ይጓዝ ነበር። በዚህ መካከል ፀሐይ እንደ መቆልቆል ብላ ነበርና ያ እየተቸነነ ይመጣ የነበረ አጀብ እንደተቆጡት ባንድ ጊዜ ቀጥ አለና ቆመ። ያ ይጎሰም የነበረ ነጋሪትና ይከላላ የነበረ መለኸት የጉዞውን ድምጥ ትቶ የሠፈሩን ምልክት ይመታ ጀመር። ቀጥሎም ከፍ ታለው ሥፍራ ንጣቱ ከበረዶ የበለጠ አንድ አጅባር ድንኳን ፍንትው አለና ተተከለ። ከዚያ እየተከታተለ ሌላውም ሁሉ ይተከል ጀመር። ከነዚሁ ድንኳኖች መኻል አንድ ተኮረብታ ዝቅ ታዳራሽ ከፍ ያለ ግምጃ ድንኳን ተተከለ። ያው ድንኳን ባለወርቅ ሻኁራ ባለወርቅ ጉልላት ነበር። ከዚያ ጉልላት ላይ ደግሞ ከነፋስ ጋር የሚታገል የወርቅና የብር ሻኁራ እየተጣለቀ ተደርጎበታል አንድ ትልቅ ሶበድአት በላዩ እስከ ቀስቱ የተጠለፈበት ሰንደቅ ዓላማ ፊጥ ብሎበታል። ይህም የንጉሥ ድንኳን መሆኑን ጦቢያና አባቷ አወቁ። ያም ሶበድአት ያረመኔው ማምለኪያ ምልክት መሆኑንም ዐወቁ።

ይኸ ድንኳን በታየ ያ እንደ ባህር የተጠለለ ጭልጥ ያለ ሜዳ ከመቅፅበተ አይን ድንኳን ፈሰሰበት። ሰዉም ፈረሱም በቅሎውም የተጋፈፈውም ከብት

ተገጠገጠበትና ሎሚ እንኳ ቢወረወር የሚወድቅበት ምድር የማይገኝ መስሎ ታየ። ባራቱም ማእዘን ያለው ዓለምና ፍጥረት በአመ ይመጽእ ጊዜ በቀርነ መለኸት ተጠርቶ የመጣ ይመስል ነበር እንጂ እውነት ባንድ ንጉሥ ቃል የሚያድር ያንድ አገር ጦር ያንድ መንግስት ሰራዊት አይመስልም ነበር። ብዛቱ በሰው ሀይል እንኳን በጦር ተዋግቶ የሚቸነፍ መሆኑ ይቅርና በክርስቶስም መዓት ሙቶ የሚያልቅ ቢሞትም ምድሩ ለመቃብር የሚበቃው አይመስልም ነበር። ይኸ ሁሉ ሲሆን ጦቢያና አባቷ ሁሉንም እያዩ "እግዚአብሔርን ብቻ ሡውረነ አውጣነ" እያሉ ሲለምኑ እስተዚያ እስታሉበት ሥፍራ እንኳን ለመውጣት አሻቅቦ ለማየትም ያሰበ አልነበረም። ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል እንዲሉ ሁሉ አባትና ልጁ ወደ ኮረብታው የሚወጣ ሰው ሳያዩ ጊዜ ለጊዜው ተስፋ አደረጉ። በአሳባቸው በጤና እናድራለን ነገም ማልዶ ይጓዝልናል ብለው አስበው ነበር።

የነገስታቱ ልማድ ሰፈር ሲጀመር ከድንኳናቸው ሳይገቡ በፊት ሠፈሩንም ለማየት ቢሆን በዙሪያውም ጠላት መኖሩንና አለመኖሩን ለመሰለልም ቢሆን ወይም በማግስቱ የሚጓዙበትን አገር የቅርቡን ባይን የሩቁን በመነጠር ለማየት ከፍ ታለ ሥፍራ መርጠው ይወጣሉ። ስለዚሁ ነገር መሥፈር በተጀመረ ጊዜ ንጉሡ ከጥቂት ባለሟሎቹ ጋር ታጅቦ ተነጥሎ በፈረስ ጋለበና ጦቢያ ካባቷ ጋር ከተሸሸገችበት ኮረብታ ሥር ደረሰ። ከዚያው ሲደርስ ወረደና መነጥሩን አሲዞ አቀበቱን ተያያዘው። አሳቡ መቼም አገር ለማየት ነው። ይኸን አይተው እነዚያ አባትና ልጁ ምን ያድርጉ ከዚያ ሸሽተው ወዴት ይድረሱ? እንዲያው ክው ብለው ደረቁ ፈዘዙ። የጦቢያ እንባም በድንጋጤ እንደተቆጡት ልጅ ቀጥ ብሎ ቆመ። ሁለቱም እንግዲህ በሞታቸው ቆረጡ ። አባትዮውም ቀረበና ጦቢያን "ልጄ እንግዲህ ተለያየን፤ እንግዲህ የፈጠረሽ አምላክ እንደ ምህረቱ ያድርግሽ። ለእኔ ስትይ ከዚህ መከራ ወደቅሽ" አለና ግንባሯንም፣ ጉንጯንም፣ ራሷንም ሳሳመና ያለቀሰውን እንባ ፈርቶ ለጠላት ላለመታየት አደራረቀና የሚመጣባቸውን ነገር ይጠብቅ ጀመር። ንጉሡም እስተባለሟሎቹ አቀበቱን ጨረሰና ከጫፉ ብቅ አለ። ገና በሩቅ ከሌሎቹ ሰዎች በፊት ንጉሡ ጦቢያን እስከ አባቷ አየና "ምናምን ከሌለበት ተራራ ከሻፎ ደንጊያ መካከል ምን ሰዎች ቆመዋል?" ብሎ እየደነቀው "ብቻቸውን ከዚህ ምን ያደርጋሉ?" እያለ ግፋን ወደ እነርሱ ሄደ።

እርሱን የተከተሉ ባለሟሎች ካጀብ እየዋሉ ወደ ወሬሳ መሄድ አይሆንላቸውምና የሰው ደም ለማፍሰስ ለግዳይ የዋሙኑ ነበሩ። እነዚያን አባትና ልጅ ቆመው ባዩ ጊዜ ዓይናቸውን በርበሬ እያስመሰሉ ፈንዜያቸውን እየነቀሉ በሻማ

ሊበጫጭቋቸው ሲቻኮሉ ንጉሡ ተፋጥኖ፡ “አትንኳቸው” አለና አስጣላቸው። ቀጥሎም “ተሁሉ በፊት ያየኋቸው እኔ ነኝ፤ እኔ ስተዋቸው እያያችሁ ስለምን ቃጣችሁባቸው? ደግሞ ለነዚህ ሰዎች እንኳን የሚዋጉበት መሣሪያ የሚመክቱበት ጋሻ የላቸውም። መግደል የሚገባው መሣሪያ ይዞ፣ እገድላለሁ አንጂ አልገደልም እያለ የሚከላከለውን ጠላት ነው። መሣሪያ የሌለውን ሰው በመማረክ ፈንታ ቢገድሉት ተግዳይም አይቆጠርም። እኔ እንኳ ገና መራየን ያልወጣሁት የሚያፋጥጠኝ ጠላት ታላገኘኝ እንዲህ ያለውን ግዳይ ነው ብዩ አልገድለውም እማርከዋለሁ እንጂ አልገድለውም አሁንም እነኚህ ካፊሮች የኔ ምርኮኞች ናቸው፤ ተዋቸው! ለካን ሰው ሁሉ ጀግና ነኝ የሚል አለመሳሪያ ዝም ብሎ መማረክ ፈልጎት የቆመውን ሁሉ እየገደለ ነው! ለእንግዲሁ ሥራት እናወጣለን” አለና ቃሉን ጨረሰ።

ይኸ ሁሉ ሲሆን አባትና ልጁ በሞት ቆርጠው ዝም ብለው ቆመው ያያሉ። ክርክራቸውን የመዓት ይሁን የምህረት አላወቁም። ጦቢያም ታባቷ ጀርባ ተጥፋ ዓይኗን ወደ መሬት ሰክካ ትንቀጠቀጣለች። አባቷ ግን ጥንት አብሮት የኖረ ጀግንነት ጥሎት አልሄደምና አተያዩን የኮረምቱ አስመስሎ ያስተውላል። የጦቢያን መንቀጥቀጥ ብቻ ሰውነቱን እያነቃነቀው ልቡ ተሰቅሎ እጁን ወደኋላ አዙሮ እሷን ያጠናናል። ንጉሡ የጦቢያን መንቀጥቀጥ ባየ ጊዜ ምንም ዘሩ ያረመኔ ቢሆን ጥቂት መራራት የማያውቅ ፍጥረት የለምና አዘነ። ቀጥሎም በጣም ቀርቦ “እናንተ ካፊሮች ከዚህ ኮረብታ ለብቻችሁ ምን ታደርጉ መጣችሁ?” አላቸው። “እግዚአብሔር ከዚህ ጦር መዓት ቢያድነን ብለን መሸሻችን ነበረ” ብሎ አባትዬው መለሰ።

ከንጉሡ ጋር አንድ ተራቢ ነበርና ይኸን ቃል በሰማ ጊዜ ለንጉሡና ለባለሟሎቹ “ካፊሮች አምላካችን ከሰማይ ነው ይላሉና ተኮረብታው መውጣታቸው ለሰማዩ እንዲቀርቡና ቶሎ አምላካቸው ልመናቸውን ሰምቶ ከእኛ እንዲያድናቸው ብለው ይሆናል፤” ብሎ ተናገረ። ቀጥሎም ፊቱን ወደ ምርኮኞቹ አዙሮ “አሁን ታዲያ ምነው አምላካችሁ መጥቶ ከእኛ እጅ አያድናችሁ?” እያለ ይዘብትባቸውና ያላግጥባቸው ጀመር። ይኸው ተራቢ ባሣቂነቱ ተወዶ ቀርቦ ነው እንጂ እንኳን ለቤተ መንግሥት ለተራብ ጅብም ያስጠይፍ ነበር።

አስቀድሞ ባቱና አንገቱ የሽመላይ አሞራ ይመስል ነበር። ጉንጭና ጉንጩም በመዶሻ የሆነኝ ብለው ያጣጉት ይመስል ነበር። ሲሥቅማ ቢታይ ጭራሹንም መልኩ ሁሉ ይለዋወጥና የጭላዳውን ዝንጀሮ መልክ ያስመስግናል። ውቃቢ የለውም ላህይ የለውም ውርፍ ያለ ውርፍ ነበር። ነፍሱ መኖሯ በመንቀሳቀሱና

በመነጋገሩ ነው እንጂ መታወቋ በቀረውስ ከላሊበላ ዋሻ ከሚጠራቀመው ሬሳ አንዱ ሥፍራ ታጥቶለት ከውጭ የቀረ ይመስል ነበር።

የዚህን ጅማታም ተረብ በሰማ ጊዜ የጦቢያ አባት በክርስቲያን ሃይማኖት መሣለቁ ነዶት “አንተ የምተሣለቅበት የክርስቲያን አምላክ መዓቱንና ምህረቱን ለማውረድ የተራራው ቅርበት የሜዳው ርቀት ያየሩ ምጥቀት የውቅያኖሱ ጥልቀት ያብራጃው ደግነት የገሞራው ብርታት የበረዶው ቀዝቃዛነት የጨለማው ጥቁረት የወጀቡ ግነት አያሰናክለውም። ሁሉ ለእርሱ አንድ ነው። ይኸ ሁሉ ባንድ ቃል ይቆማል፤ ይሠራል ይፈርሣል እንዳልነበር ይሆናል። ከእምነበ አልቦም ይመጣል። በእርሱ ፊት ሁሉም አንድ ነው። ለእርሱ ኃይለኛው፣ ደካማው፣ ደፋሩ፣ ፈሪው፣ ድኃው፣ ሀብታሙ፣ ገዢው፣ ተገዢው ሁሉም አንድ ነው። ሁሉም በእርሱ ፊት ኢምንት ነው። በእርሱ ፊት ትንሽና ትልቅ የለም። በዚህ ዓለም ያመነውም ያላመነውም ትክክል ይኖራል። ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ያረጃል፣ ይሞታል። በወዲያኛው ዓለም ግን ሁሉም እንደምግባሩ እንደ ሀይማኖቱ ወይ ካሳውን ወይ ፍዳውን ይቀበላል። አሁን እኔና ልጄ እስትንሞት ድረስ አምላካችንን ከልብ እናምነዋለን። ብንሞት፣ ብትገሉንም አሁን ባበሳችን፣ በኃጢአታችን እንሞታለን እንጂ ለክርስቶስ ማዳን አቅቶት መስማት ተስኖት እንዳልሆነ እናውቃለን” አለና ተናገረ።

የተራቢ አንዳንድ አጋዥ አይጠፉምና ከንጉሡ ባለሟሎች መካከል ተቀብሮ ከድምጡ በቀር ያለበት የማይታወቅ ከነገሥታቱ ቤት ልማድ ነውና አንድ ድንክ ተቁመቱ አፍንጫው ላቅ ያለ፣ ተመዳፉ ጆሮው ሰፋ ያለ፣ ተግንባሩ ይልቅ አገጩ ለእንቅፋት የተመቸ፣ ከተረከዙ ቀድሞ ቂጡን አቃቅማ የሚወጋው፣ ተመቆሙና ተመቀመጡ መለዮው ያልታወቀ፣ አብሮ ንጉሡን ይከተል ነበር። ይኸ ድንክ የጦቢያ አባት “በክርስቶስ ፊት ሁሉም አንድ ነው ሁሉም ትክክል ነው ሁሉም ኢምንት ነው” ሲል በሰማ ጊዜ “ሁሉም ኢምንት ተሆነ እኔ ምን ልሆን ነው? እንግዲያው የለሁማ? ወይም ከዚህ ሞላላ ተራቢ ጋር ትክክል ነኛ! እንደዚህ ካፈር ንግግርስ ወይም ዛፍ አክላለሁ ወይም የለሁም” አለና እንኳን ሌላውን ፈርታ የምትንቀጠቀጠውን ጦቢያን አሣቀ። ንጉሡ በዚህ ጊዜ የሰውን ሳቅ አቋረጠና መንፈስ ቅዱስ እንደመራው “አላህ እንዳወቀ አለሙን ሁሉ ፈጠረ፣ አላህ እንዳወቀ ፍጥረቱን ሁሉ እንደ ሃይማኖቱ ያስረዳዋል። አላህ እንዳወቀ ሁሉንም እየቋንቋው ይሰማዋል፣ እየምግባሩ ያጸድቀዋል ይኮንነዋልም። ሰው ግን ከእርሱ ተገዛ ሃይማኖቱ በቀር የሌላው ሰው ሃይማኖት ምንም ረብ ያለው አይመስለውም። አሁንም የሰው

ሃይማኖት አታበጥል። አላህ ብቻ ነው የውነተኛውን ሃይማኖት የሚያውቅ፣ አላህ ብቻ ነው ሁሉን የሚገመግም ደግሞስ የካፊር ሃይማኖት ይበልጥ እንደሆን ማን ያውቃል" ብሎ ንግግሩን ጨረሰና እንደ መተከዝ አለ። አብረውት ያሉት ሁሉ በዚህ ባልታሰበ ንግግሩ እጅግ ተደነቁ።

ይኸ ሁሉ ሲደረግ ጦቢያ ይሉ አባቷ ይኸን ቃል የተናገረው ሰው፣ ማን እንደሆነ አላወቁም እንኳንስ ንጉሡ መሆኑን ይጠረጥሩ አንዳንድ ቱኪም አልቆጠሩት ነበር። ደግሞ ከዚያ ካሉት ሁሉ እርሱ ልጅ ነበር። የተከተሉት ሁሉ ተሽልመው ሳለ የእርሱ ልብስ እንደማንም ነበር። ብቻ መልካም መልካም ቃል ሲወጣው ጊዜ "ምነው ንጉሡም እንደዚህ ልጅ ደግ ሰው በሆነልን! እኒህ ማርከው ቢወስዱን ይሻለን ነበር" እያሉ በልባቸው ይመኙ ጀመር። ላባትና ልጁ ንጉሡ እስከ ባለሟሎቹ ድረስ ከድንኳኑ ዐርፎ የተቀመጠ መስሏቸው ነበር እንጂ ከዚያው ከተሸሸጉበት ድረስ ሄዶ ከፊታቸው ቆሞ ያነጋግራቸው ዘንድ በህልምም በውንም አላሰቡትም ነበር። ነገር ግን እንዳጋጣሚ ሁሉ ያው ልጅ ዋናው ንጉሡ ነበር።

በዚህ መካከል ጊዜ ፀሐይ እንደመቆልቆል ማለት ጀመረች። ንጉሡም "አገር ሳናይ መሸብን መነጥር አምጡ" አለና አራቱንም ማዕዘን ያይ ጀመር። ቀጥሎም የሠራዊቱን አሠፋፈር አምሮ ባየ ጊዜ ደስ እያለው ፍግግ ፍግግ ይል ጀመር። እውነትም አምሮ ነበር። የሰፈረበቱ ሜዳ ባይነ ኅሊና ተለክቶ የማያልቅ ነበር። ከዚያ ታሉበት ኮረብታ በቀር አባጣ ጎርባጣ መሬት እግር የሚጠልፍና የሚያደናግር ሥር ላይን የሚቆረቁር ጠጠር አልነበረበትም፤ ብቻ ነፋስ እርም ብሎ የተወው የረጋ ባሕር ይመሰል ነበር። የሰማዩና የምድሩ ዳርቻ እንደ ፍቅር ከንፈር ተሳስሞ እንደመሶብና እንደ ሙዳይ ከንፈር ለከንፈር ተጋጥሞ ለመላቀቅ የቸገረውና እንዳይላቀቅ መሐላ የገባበት ይመስል ነበር እንጂ ሌላም አይመስል ነበር። ብቻ የፀሐዩ ጠዳል ዳኛ ሆኖ ሰማዩን ከዚህ አትለፍ ምድሩንም ከዚህ አትውጣ ብሎ በየገዛ ቀለማቸው ወሰን ሰጥቶ ያካለላቸው ይመስሉ ነበር። ከዚሁ ሜዳ ላይ የዚያ ሁሉ ሠራዊት ድንኳን ተረጥርጦበታል። ሰፈሩ ከታችም የተጀመረበት ተላይም የተጨረሰበት ተቀኝም የተደፋበት ተግራም የተዘነበለበት አይታወቅም ነበር። ተሠፈሩ መካከል ቆሞ ለሚያይ ሰው በተራዛሚ የእንግሊዝ መነጥር እንኳ ከፊትም የፊታውራሪውን ከኋላም የደጀኑን ተቀኝም የቀኛዝማቹን ተግራም የግራዝማቹን ሠፈር ለማየት አይሆንለትም ነበር። ጊዜው ድንግዝግዝ እያለ በሄደ ጊዜ ይልቁንም ያ ሁሉ ድንኳን ደመና ያላሰናከለውን የታኅሣሥን ኮከብ ይመስል ጀመር።

በዚህ ጊዜ ንጉሡ "መሽብን ወደ ሠፈራችን እንሂድ" አለና ተነሳ። ነገር ግን ገና መንገዱን ሳይጀምር በፊት ወደ ጦቢያውና ወዳባትዬው ዘወር አለና "እናንተ ካፊሮች አይዟችሁ ሳትፈሩ ተከተሉን። ተእኛ ጋር መኖር ብትወዱ አሳምረን እናኖራችኋለን፤ ታገራችሁም መቅረት ብትወዱ ተእኛ ጋር ስንብታችሁ አገር አማን ሲሆን እንለቃችኋለን። አሁን ግን ብንለቃችሁ ለግዳይና ለምርኮ የሳሳ ወታደር ነገሩን ሳያውቅ ከመንገድ ያገኛችሁና ያጠፋችኋል" አለና መከራቸው።

የጦቢያ አባት ይኸን ቃል በሰማ ጊዜ በልቡ "እንግዲህ ልጄ ልትተርፍልኝ ነው መሰለኝ" ብሎ እጅግ ደስ አለው። ተዚያ ወዲያ ከዚያ ከነበሩበት ሰዎች ሁሉ እርሱ ዋና መሆኑን ጠረጠረ። ነገር ግን ገና ዋናው ንጉሡ እርሱ መሆኑን አልጠረጠረም ነበር። ብቻ ያንዱ የትልቅ ሹም ልጅ ወይም ቢበዛ የንጉሡ ባለሟል ይሆናል ብሎ ጠርጥሯል። ያም ሆነ ያም ሆነ ለእርሱው ለንጉሡ "ጌታው እስታሁን ድረስ እኔና ልጄ ፈርተን ስንንቀጠቀጥ ነበር እርስዎም አይተዋል። የእኔው መንቀጥቀጥ ግን ለእኔው ለራሴ መሞት ፈርቼ አይደለም ወንድ መቼም ለመከራና ለሞት ነውና የተፈጠረው። ነገር ግን የእኔው መፍራት የእኔው መንቀጥቀጥ ለዚህ ጮርቃ ልጄ ነበር። አሁን ግን እርስዎ በገዛ ራስ እንዳንፈራና ምንም እንዳይደርስብን ቃል ሰጡን እንግዲህ እርግጥ መዳናችንን የምናውቀው እርስዎ እንደ ደግነትዎ እንዳወቁ አድርገው ለንጉሡ ነግረው ያስማሩን እንደሆነ ነው" ሲል ልመናውን አቀረበ። ንጉሡ ይኸን ቃል በሰማ ጊዜ ንጉሥነቱን እንዳይናገሩ አብረው ያሉትን ሰዎች ባይኑ ገረመመና "እሺ ለንጉሡ ነግሬ አድናችኋለሁ" ብሎ አስከተለና ሄደ።

ከድንኳኑ በደረሰ ጊዜ ሳይገባ አዛዡን በፊት አስጠርቶ "እነዚህ ካፊሮች ከዚህ እንዳይርቁ አድርገህ ድንኳን ስጥና እንዳይርባቸውና እንደይጠማቸው አድርገህ አስቀምጥ" አለና ገባ። አዛዡም አሣምሮ አስመችቶ አሳደራቸው። አባትና ልጁ ለጊዜው ነገሩ ቸገራቸው። ንጉሡ እርሱ ነው እንዳይሉ ወዲህም ገና ልጅ ነው፤ ቢገፋ ቢገፋ የሀያ አመት እድሜ ቢኖረው ነው። ወዲህም ልብሱ አልባሌ ነው። ውቃቢው ግን እጅግ ያማረ፤ ንግግሩ የጠዳና የጣፈጠ፤ አተያዩ የተሰራና የተቀጣ፤ መልኩም የወይን ዘለላ የመሰለ ዳማ ነበር። ምንም ያረመኔ ዘር ምንም ገና ጢም ያላቀነቀነ ልጅ ቢሆን ጥላው የከበደ ግርማው የተፈራ ነበር፤ ልብሱ ብቻ ምንም ያማረና የጠዳ ቢሆን የዚህ ሁሉ ሠራዊት አሳዳሪ አያስመስለውም ነበር።

መቼም ነገሥታቱ ትልቅ ዓመት በዓል ካልሆነና ትልቅ እንግዳ ካልመጣ በስተቀር ሲያያዝ በመጣው ልማድ መሠረት ለራሳቸው ማጌጥ ነውራቸው ነው። ብቻ የነገሥታት ጌጣቸው ጀግና መሸለም ቤታቸውን ፈረስ በቅሏቸውን ማስጌጥ፣

አገራቸውን ማልማት፣ ፍርድ አለማጓደል፣ የበደላቸውን መማር፣ ሀብታምና ድኃ አለመለየት፣ በገዛ ራሳቸው አለመኩራት ነው እንጂ፤ በወርቅ፣ በብር፣ ባልማዝ፣ በዕንቁና በግምጃ እንደሥእል ቢለበጡ ክብርና ጌጥ እንዳይሆናቸው ያውቃሉ። ከቤተ መንግሥት ደግሞም ጌጣጌጥ ላዝማሪ ወይ ለድንክ ወይ ለቅሬና ለማንዘራሽ ነው የሚሰጥ። ይኸውም እንደ ጀግንነት ምልክት ተቆጥሮ ይቀቡበታል። ነገር ግን ነገሥታቱና የጨዋው ልጅ ሁሉ ጌጥም ባይኖረው እንዲያው በውቃቢው ይለያል። ደግሞም ወርቀዘቦና ደማስ ተለበሰ አህያና መጋዣ ሌጣውን ያለ ጮሌ ያምርበታል። በረጃጅም ጥርሱ ታጌጠ እከካም ዝኆን በለስላሳ አንፋሮውና በትንንሽ ጥፍሮቹ የኮራ አንበሳ ያምራል።

ስለዚህ ምንም ጌጥ ባይኖረው በንግግሩ በኳኋኑ በግንባሩ ጦቢያም አባቷም ንጉሡ እርሱ መሆኑን ተረዱት። አርቀው ሲያስቡ ንጉሡ ራሱ ሲያነጋግራቸው ማምሸቱ እየደነቃቸው የክርስቶስን ነገር ሲያደንቁ ሌቱን ሁሉ አደሩ።

በበነጋው ንጉሡ ጉዞ ሳይጀምር በፊት ከድንኳኑ ብቅ ባለ ጊዜ በሩቁ ጦቢያን ከአባቷ ጋር ቁማ አየና ቀረብ ብሎ እንደመሣቅ እያለ “አይዟችሁ! እንግዲህ ምንም የለባችሁ፣ ለንጉሡ ነግሬላችኋለሁ” አላቸው። አባትና ልጁም ደስ አላቸውና እጅ ነሱ። ንጉሡ እርሱ ራሱ መሆኑንም ያላወቁ መሰሉ። ንጉሡ ወዲያው ዘወር ዘወር አለና ለነዚህ አባትና ልጅ ደኅና ደኅና ፈረስ መርጠህ ስጣቸውና ተጉዘው ወታደር እንዳያንገላታቸው ከእኔ ኋላ ኋላ ተዛንተው ይጓዙ ብሎ አዘዘ።

ጉዞውም ተነሣ። አባትና ልጁም በማለፊያ በማለፊያ ጮሌ ተቀምጠው ንጉሡን ሲከተሉ ዋሉ፤ የመዳናቸውንም ነገር አስረገጡ፤ ተስፋቸውም እያደር አደገ። ድሮ ለራሳቸው ፈርተው ትተውት የነበረውን የዋሕድን ነገር በማሰላሰል “ወዴት ደርሶ ይሆን? ምን ሆኖ ይሆን?” ይሉ ጀመር። ወደ ቀትሩ ሠፈር ተጀመረ። እንደ ልማዱ ከፍ ታለ ዲብ ላይ የንጉሡ ድንኳን ፊጥ ባለ ጊዜ ከመቅፀበተ ዓይን ዙሪያውን ሁሉ ድንኳን ብቻ ሆነ። ወራሪውም ተግራ ተቀኙ የገደለ የማረከውን እየማረከ እያቅራራ እየዘፈነ እየተጅመለመለ፣ ሆ - ሆ - እያለ የደም ሽማውን በፈረሱ አንገት እያሰረ ያመጣ ጀመር። ንጉሡ በዚህ ጊዜ ካደባባዩ አፋፍ ላይ ባለ ወርቅ ወንበር ላይ ተቀምጦ ዙሪያውን ትልልቅ ሹማምንት ተቀምጠው በግራና በቀኝ ዐምድ ዐምድ የሚያካክል ሰይፈ ጃግሬ ሻንቅላ የዝኆን አንገት እንደዝሃ የሚቆርጥ የመሰለ ሰይፉን እየመለጠ ቁሞ ነበር። ከዚህ ቀደም ሲል ባለ ጫሜ፣ ባለቢተዋ፣ ባለአንበሳ፣ ባለግስላ ሽልሜ ሁሉ ተገርግሮ ቀኝ ቀኝ እጁን ተመክዱ ታውራሪሱ ላይ ጣል እያደረገ ቆሞ ነበር። ከዚህ ቀጥሎ ግራና ቀኝ በውቅ የተመረጠ ደንደሳም ደንደሳም

በገዛ ጡጫው ዝኖን ተመሬት የሚደባልቅ የመሳሰለ አምስት ሺ ዘበኛ ተገጥግጦ ቆሟል። ከዚህ ሁሉ ሰው አንድ ትንፋሽ አይሰማም። ንጉሡ ሳይቀር ዝም ብሎ ግዳይ ጣን ይጠብቃል። ያ ሁሉ ሽልሜ፣ ያ ሁሉ ጀግና ዝምታ ታክሎበት እንደሳት የሚገላምጥ ስጋጃና ወላንሳ በፊቱ ተለጥልጦበት፣ ግራና ቀኙ ኑግ ልጥልጥ የመሳሰለ ሻንቅላ የተሳለ ሰይፍን እየመዘዘ ቆሞበት በመካከሉ ከጠይምነቱ በቀር ቅዱስ ሚካኤልን የመሰለ ወዘላ ህፃን ንጉሥ በረጅም ወርቅ ወንበር ተደላድሎ ተቀምጦ ጦቢያና አባቷ ይህን ግርማ ይኸን ዝምታ ባዩ ጊዜ አመ ይመጽእን እንጂ ሌላም አልመሰላቸውም ነበር። ሁሉ እንዲህ አምሮ ተተሰናዳ በኋላ ግዳይ ጣይ ተጠራና በየተራው እየደነፋና እየፎከረ ግዳይ ይጥል ጀመር። ንጉሡም ደስ ደስ እያለውና ጥርሱን ፍግግ ፍግግ እያደረገ ይቀበል ጀመር። ጦቢያ ግን ይኸን ሁሉ ዓለም፣ ይኸን ሁሉ ደስታ፣ ባየች ጊዜ የሰውን ማለቅ፣ ያገሩን መጥፋት፣ የክርስቲያኑን ዘር መጠቃት፣ ያረመኔውን ዘር መልማት እያሰበች አንገቷን ወደ አባቷ ጎን ሸሽግ አድርጋ አዩኝ አላዩኝ እያለች ታለቅሳለች። ንጉሡ በሩቁ ሐዘኗን ዐወቀባት። ያንዱ መከራ ላንዱ ደስታ መሆኑን አሰበና ወዲያ ምንም ነገሩን ባያስታውቅ ግዳይ ጣዩን አቋርጦ ትቶ ወደ ድንኳኑ ገባ።

የንጉሡ ድንኳኖች ዋኖቹ አምስት ነበሩ፤ የንጉሡ አባቱም እናቱም ልጅ ሳለ ስለሞቱበት እንዳባትና እንደ እናት ሆኖ ያሳደገው አጎቱ ነው። አጎቱ አንድ ልጅ ነበረችው። ለንጉሡ እኅት ይሉ ወንድም አልነበረውምና ይህችን ያጎቱን ልጅ እጅግ አድርጎ ይወዳታል። እኅቴ ነው የሚላት፣ እርሷም እንደ ወንድሟ አያዋ ነው የምትለው፤ ዕድሜአቸውም ትክክል ነው። ከፍቅራቸው የተነሣ በየዘመቻው ሁሉ አብረው ይሄዳሉ፤ አይለያዩም። ስለዚህ አንዱ ማለፊያ ድንኳን የእርሷ ነው። አራተኛው ድንኳን ያጎትዬው ሲሆን አምስተኛው ድንኳን የትልልቅ እንግዳ መቀበያ ነው። እኒሁ አምስቱ ድንኳኖች በሸማ አጥር ተከፋፍለው ደጃፍ ለደጃፍ አይለያዩም። ከነዚህ ድንኳኖች ሸማ አጥር ቀጥሎ ለጦቢያና ላባቷ ትንሽ ማለፊያ ድንኳን ተተክሎላቸው ሰው ሁሉ ካፊር እያለ እንዳያላግጥባቸው ተብሎ ተቀምጠዋል። ከነዚህ ሁሉ ውጭ ግምጃ ቤቱ፣ ዕቃ ቤቱ፣ ጠጅ ቤቱ፣ ወጥ ቤቱ፣ እንጀራ ቤቱና ሥራ ቤቱ ተለቅልቆበታል። ከሥራ ቤቱና ከንጉሡ ድንኳኖች መካከል ትልቅ የግምጃ አጥር ዙሪያውን ተተክሎ ገና ከሩቅ እየተንቦገቦገ ዓይን ይጠነብራል። ከዚህ አጥር ውጭ አምስት ሺህ ዘበኛ ተቈመቱ የረዘመው ከደረቱ የሰፋው ከደንደሱ ያፈረጠመው በውቅ ተመልምሎ በብርና በወርቅ መሣሪያ እየተሸለመ ታጥሮበታል። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ እልፍ ፈረሰኛ ዘብ ይጠብቃል። ሠፈሩ ከዚህ ወዲያ ነው የሚጀመርበት።

ከግምጃው አጥር አጠገብ ጥቂት ተመሸ በኋላ የሚዛወር ነፍስ አይገኝም ነበር። ጭር ብሎ ወፍ ለቅሞ የሚነሣበት ይመስላል። ሰው አጥብቆ እንዳይነጋገር ዘበኛ ይከለክላል፣ ብቻ የሰውን ቁጣ የማይፈራ፣ የንጉሡን ቃል የማይሰማ፣ የድንኳኑ መርገፍ ከነፋስ ጋር ሲጋፋና ሲጣላ ያመሻል፤ ያነጋል።

በዚያ ዕለት ማታ ግብር ሊገባ እፍን እፍን ሲል ጥቂት ቀደም ብሎ ንጉሡ ጥቂት ለመናፈስ ከድንኳኑ ወጣ፣ ጦቢያ ታባቷ ጉልበት ግንባሯን ተክላ እየተከዘች ከተመሩበት ድንኳን ደጃፍ ተቀምጣ ነበር። ንጉሡ እንዳጋጣሚ ወዲያና ወዲህ እየዞረ ሲያይ አያት። ገና በቀን ግዳዩ ሲጣል ስታለቅስ አይቷት ነበርና እንደዚያው ታለቅስ መሰለውና ለማረጋጋት ቀረብ አለ። አባትና ልጁ ንጉሡ መሆኑን ባዩ ጊዜ ደነገጡና ተነሡ ንጉሡ ግን በጣም ቀረብ አለና "ከንጉሡ ባነጋግራችሁና መልኩን ትወዳላችሁ?" ብሎ ጠየቃቸው። መቼም የጨዋ ልጅ ንግግር አይጠፋውምና የጦቢያ አባት ቶሎ ብሎ "ጌታዬ ከእርስዎ ፊት በቀር የሌላ ንጉሥ ፊት ልናይ አንፈልግም" አለና መለሰ። ንጉሡም እንዳወቁት ገባውና "እንግዲያውስ ከእኔ በስተቀር ሌላ ሰው ካልወደዳችሁ እኔም አልጥላችሁም እመኑኝ" አለና ወደ ግብር ሄደ። የእርሱ ንጉሥነት ላባትና ልጁ ተተገለጠላቸው ዘግይቷል ለንጉሡ ግን የጦቢያ ሴትነት ይገለጥለት ዘንድ ገና ነበረ።

በማግሥቱ ከወሬሳ የደከመው ሰው ከብቱም እንዲያርፍ ውሎ ሆነ። ንጉሡም በማግሥቱ የሚያደርገውን ሲያስብ ዋለ። ተሁሉም የሚታሰበው ትላንትናውን ተቀምጦ ግዳይ ሲቀበል ጦቢያ የሰውን እልቂትና የአገሩን ጥፋት እያሰበች ያለቀሰችበት ጉዳይ ነው። ከዚህም ነገር የተነሣ ሰዉ በከንቱ እንዳያልቅና አገሩ በከንቱ እንዳይጠፋ አዋጅ ሊነገር አሰበ።

ሀ - የአዋጁ አነጋገር እንደሚከተለው ነው።

በፊት አዋጅ ነጋሪው ካደባባይ ወጥቶ ከፍ ታለ ደንጊያ ላይ ቆሞ እንዲህ እያለ ሦስት ጊዜ ይጮሃል። "ስማ! ስማ! መሰማሚያ ይንሳህ የንጉሥን ጠላት፣ የጌታችንን ጠላት ያገራችንን ጠላት።"

ለ - የአዋጁ ቃል

‹‹ክርስቲያን ሆይ! አንተ እንደምታውቀው ከጥንት ታያት ከቅድማያታችን ጀምረን በሃይማኖታችን ልዩነት የተነሳም ቢሆን ወይም በድንበር መጋፋት የተነሳም ቢሆን እኛና እናንተ ክርስቲያኖች እየተጣላን ስንዋጋና ስንተላለቅ እስከ ዛሬ ኖርን። ይኸ ሁሉ ጠባችን ከሁለቱም ወገን ንጉሦች እየቀረ ነው እንጂ ከሕዝቡ አይደለም።

የሁለቱም አገር ንጉሦች ልብ ለልብ ቢተዋወቁ ኖሮ እንዲህ አገር በከንቱ አይጠፋም ነበር፤ ድኃውም አለውል ሳያልቅ እያገሩ እየድንበሩ እየሃይማኖቱ ተስማምቶ ይቀመጥ ነበር። ይኸው አሁን ካያት ከቅድማያቴ በቆየኝ በቀል መሠረት እስከዚህ ድረስ መጥቼ አገር አለውል አጠፋሁ፤ ድኃውን በደልሁ፤ ሰዉንም ፈጀሁ። ይኸ ሁሉ ሲሆን አንድ የእኔ ባይ አንድ መካች ንጉሥ እንደሌላችሁ አየሁ፤ ስለዚህ እስከ ዛሬ ድረስ ባደረግሁት ነገር ጠጠት አደረብኝ። አሁንም ለእንግዴሁ በቃ ብያለሁና በዱር በገደል ያለህ ነፍስ የገደልህ፣ ቋንጃ የቆረጥህ፣ ምሬሃለሁ ግባ። ከዚህ በፊት ባደረክኸው ኃጢአትህ አትከሠሥ አትወቀስ።

“ነጋዴም ነግድ አራሽም እረስ፣ ቆፋሪም ቆፍር። ካህንም ቤተ ክርስቲያንህን አገልግል። ሁሉም በየሃይማኖቱ ይቀመጥ፤ ያንዱን ሃይማኖት አንዱ አያዋርድ፣ አያብጥልል፤ የጥንቱ ይብቃ። እኔ ክርስቲያን ባልሆን ሁሉንም እንደየሃይማኖቱ አክብሬ አስከብረዋለሁና አይዞህ እንደ ጥንትህ እንደ ልማድህ እንደሥራህ እደር።

“ድኃዬ ሆይ! አይዞህ መጣሁልህ እንጂ አልመጣሁብህም። እኔ ከዛሬ ጀምሬ ትልቁን አባቴ፣ ትንሹም ወንድሜ ብዬ አክብሬ፣ ሕዝቤ ዜጋዬ ብዬ ፍርድ ሳላጓድል እኖራለሁ። አንተም ከዛሬ ጀምረህ ንጉሣችን ብለህ ዕወቀኝ። የሸሸህ ሁሉ ተመለስ። እየርስትህ እየቦታህ ግባ። ድኃዬ ሆይ! በዘረፍሁ በገፈፍሁህ ፈንታ ካሣ እንዲሆንህና አገርህ እንዲያቀጥል የሁለት ዓመት የግብር ገንዘብና የድግር አሥራት ምሬሃለሁ።

“ደግሞ ባላልጋ የሆንህ የንጉሥ ዘርነት ያለህ ራስ ደጃዝማች፣ ቢትወደድ፣ ሹም ሽልም የነበርህ ሁሉ ግባ፤ አገርህን ግዛትህን ጉልትህን መርቄልሃለሁና ተመልሰህ የአስተዳደር ሥራህን ቀጥል። ከዚህ አዋጅ በኋላ ግን ከማዕረግህ አልገባም ብለህ አምጠህ አገሬን አውካለሁ ወይም መንግሥቴን እጋፋለሁ ያልህ እንደሆነ ለራስህ ዕወቅለት፣ ተርስትህ፣ ተጉልትህ ተግዛትህ እንደተነቀልህ ዕወቀው፤ ተገባህም ወዲያ ያ ከንቱ ምኞትህን እያወራህ የሰው ልብ አሻክራለሁ የምትል ሰው በጠላትህ ምስክር ተከሠሥ።

“ወታደርና ባላገር ተከባብረህ ኑር፤ ወታደር የሆንህ ድኃ አትበድል። አንተ ጎራዴ ታጥቀህ ጋሻ አንግበህ ብታገለግለኝ፤ ባላገርም ሞፈሩን ተሸክሞ ድግሩን ጠርቦ የሚያገለግለኝ እርሱ ነው። ሁሉም አገልግሎቱ አንድ ነው። ሁሉም እየውለታው አገሩን ንጉሡን ያገልግል” አለና አስነገረ። ይኸ ቃል በተሰማ ጊዜ ሁሉም አንድነት “ይበጅ! ያድርግ” ብሎ አጨበጨበ።

ከዚህ አዋጅ ወዲያ አገር መዝረፍ ሰው መግደል ቀረ። ጉዞውም ከዚህ እለት ጀምሮ ቀረ፤ ከዚያው ከተሠፈረበት ላይ ዋና ትልቅ ከተማ ተቆረቆረ። አንድ ላይ ተመቀመጥ የተነሣ በግድም በውድም ንጉሡ ጧትና ማታ ጦቢያን እስታባቷ ያያቸው ነበርና ከቀን ብዛት ውቃቢው ጦቢያን እጅግ ወደዳት። እርሷም ጉዞው ቀርቶ የቀን ፀሀይ የሌት አመዳይ ሲቀርላት ጊዜ በእንባ የታረሰው መልታሕትዋ እያማረ፣ በርኅብና በጥም የተጎዳው ገላዋ እየተመለሰ ሄደ። ምንም እርሷ እያፈረች ሴትነቷ እንዳይታወቅባት ራቅ ብትል፤ ንጉሡ ይልቁንም ያፈቅራትና ያቀርባት ጀመር። አባትየው ግን ንጉሡ እያደር ሲያቀርባት ባየ ጊዜ የልጁ የጦቢያው ሴትነት እንዳይገለጥባት ተጨነቀ። “አይዞሽ እንዳይገለጥብሽ አረማመድሽንም አነጋገርሽንም እንደ ወንድ አድርጊ” እያለ ይመክራት ነበር። ነገር ግን ልብስዋ ፈፅሞ እንደ ወንድ ነበርና የሴትነቷን ነገር ማንም አልጠረጠረም። ብቻ እንኳን ንጉሡ ሌላው ያያት ሰው ሁሉ በመልኳ ይወዳት ጀመር። እውነትም ጦቢያ እጅግ የተዋበች እጅግ የተደነቀች፣ ላያት ሁሉ የምታነሆልልና የምታዘነጋ ነበረች። ዓይንዋ አስቀድሞ የብር አሎሎ መስሎ ካጥቢያ ኮከብ ጋር የተፎካከሩ ነበር። በዚያ ላይ ደግሞ ሽፋሽፍቷ እንደበልግ ሣር ተጨብጦ የሚታጨድ ይመስል ነበር። አፍንጫዋ ቀጥ ያለ፣ ከንፈሯ መፈንዳት የጀመረ የማለዳ ጽጌ ረዳ ይመስል ነበር። እንደወንድ የተቆጠረችው ጠጉርዋ እንደ ሰኔ ቡቃያ ወይም እንዳዲስ መሬት ጤፍ እየጋሸበ የሐር ነዶ መሰለ። በፀሐይና በውርጭ የተጎሳቀለውና የጠቆረው ፊቷ እያሸለተ ሀጫ በረዶ ተመሰለው ጥርሷ ጋር ገና ከሩቅ እየጠቀሰ ከተሸሸገችበት ሴትነቷን ያሳጣባት ጀመረ። አጠረች ረዘመች፣ ወፈረች ቀጠነች፣ የማይሉትን ያካላቷን ነገር መናገር በከንቱ ነው። እሞብርሌ የመሰለው አንገቷ እንደደከመው እያረፈ የወጣ ነው። አለአጥንት የተሰራው የእጇ ጣት እጀ ስራ ከበዛበት አመልማሎ ጋር ይፎካከራል። እንደ ፈረስ ለኮ ሳብ ረገብ ያለው ዐጥንት የሌለበት ወገቧ ከንብ አውራ ጋር ይለካካል። ባቷ፣ ተረከዟ ይቆጡኛል ያለ የተሠራ የተቀጣ ነው። ስትፈራ ስትቸር የምትገልጠው ጥርስና ከናፍሯ ከዚያ አተያይ ጋር ብርቱውን ያዝላል፤ ሰነፉን ይገድላል። እንዲያው እግዚአብሔር ደስ ያለው እለት ተጨንቆና ተጠቦ ሥርቶ ነፍስ የዘራባት ትመስላለች እንጂ ጦቢያ እንደ ሰው የተፈጠረች አትመስልም ነበር። በከንቱ ነው ጦቢያ ሥጋ ተመልበሷ በስተቀር ዐመሏ ከነኪሩቤል የቅርብ ዝምድና የሚቆጣጠር ይመስል ነበር።

ይኸን ሁሉ የእግዚአብሔር ስጦታ ባየ ጊዜ፣ ያ ሕፃን ንጉሥ፣ መልከ መልካምን መልአክ እንኳ ይወደዋል እንደሚሉ ሁሉ፣ እጅግ አድርጎ ውቃቢው ወደዳትና የእልፍኝ ባለሟል ሊያደርጋት ተመኘ። ነገር ግን ይኸን ሁሉ ሲያስብ የጦቢያን

ሴትነት አልጠረጠረም ነበር። ብቻ በንፁሕ ልቡ ነው የሚወድዳት። ደግሞ ንጉሡና ይቺው ጦቢያ በዕድሜ እኩያ ሊሆኑ ጥቂት ነው የሚቀራቸው። ጦቢያ ወደ አስራ ስምንቱ ዓመት ይሆናት ነበር። ንጉሡም ወደ ሃያው ዓመት ሆኖት ነበር። ይኸም የሁለቱ አፍላነት፤ የፍቅር ድርብን የሚያበረክት ሆነ።

ንጉሡም “ልበልን ልተው” ሲል ቆይቶ አባትና ልጁን አስጠራና አስመጣቸው። እነዚሁ አባትና ልጁ “ምን ይሆን የተጠራንበት” እያሉ እየተጨነቁ ከፊቱ እስኪደርሱ ድረስ ባንድ ጊዜ ሺህ የሚሆን መላ ይጥሉ ጀመር፤ ይልቁንም የጦቢያ እግር ስንክልክል እያለባት አባትዋ እንደመከራት ሆና እንደ ወንድ መራመድና እንደ ወንድ ራሷን አቅንታ መሄድ ቸገራት። ነገርዋ ሁሉ ወደ ሴትነቷ እያደላ እንቢ አለ። ይልቁንም የፈሩት “ከአሁን አሁን የሴትነቷ ነገር ይታወቅባት ይሆን” እያሉ ነበር። ንጉሡ ግን ይኸን አልጠረጠረም፤ ወዲያው እንደ ደረሱ ሰዉን አስከለከለና አይኑን ወደ ጦቢያ መልሶ “ኧረ በል አንተ ልጅ፣ ከእኔ ጋር ብትኖርና ባለሟል ባደርግህ፣ አብረኸኝ ብታድግና ብሾምህ ብሸልምህ ደስ አይልህምን?” ብሎ ጠየቀ። ጦቢያ ግን አፍራም ይሁን ፈርታ ምላሹን ለአባቷ ተወች። ንጉሡ ገና እርስዋን እርስዋን እየተመለከተ ምላሹን ሲጠብቅ አባቷ መናገር ጀመረ። ንጉሡም ወደእርሱ ዞረና ያዳምጥ ጀመረ። በዚህ ጊዜ ጦቢያ ምንም አባቷ እሺ አንዳይል ብታውቅ ጊዜው ተመቻትና እየጠቀሰችና አንገቷን እያነቃነቀች “አይሆንም በል” አለችው።

አባቷ “ንጉሥ ሆይ እንደእርሶ ታለ ንጉሥ ጋር አብሮ መቀመጥ የእርስዎ ባለሟልና የእርስዎ እድግ መሆን እጅግ መታደል ነው። ለዚህ ልጄ እንዲህ ያለ ማዕረግ ስላሰቡለት እኔም ልጄም እናመሰግንዎታል፤ መንግሥትዎ ይስፋ ። ይኸ ደጉ አእምሮ አይለወጥብዎ ። ነገር ግን የእኔ ልጅ ጦቢያ የቤት ልጅ ነውና በቤተ መንግሥት ኑሮ አያውቅበትምና አይሆንም፣ አይዘኑብኝ። ደግሞ ጌታዬ ሆይ! ተኮረብታው ላይ ተሸሽገን ባገኙን ዕለት ብንወድ ልንቀመጥ ባንወድ አገር አማን ሲሆን ለቀውን ልንሄድ ቃል ሰጥተውናልና በዚያው በቃልዎ ይሰዱን ዘንድ እለምንዎታለሁ። አገሩ ከእርስዎ አዋጅ ወዲህ አማን ሳይሆን አይቀርም” አለና ንጉሡን ማለደው። ንጉሡ ግን የተናገረው ቃል ሳይዋጣለት ጊዜ አፈረ አዘነ ወዲያው “ቃሌስ አይናወጥም፤ ተፈለጋችሁ ደስ አሰኝቼ እሰዳችኋለሁ፤ ብቻ እኔም አንድ ነገር እንደትነግሩኝ አለምናችኋለሁ። ስለምን ነው ከእኔ ጋር መኖር የጠላችሁት? ወይስ በሃይማኖታችሁ ነገር ነው? ምናልባት በዚህ ምክንያት እንደሆነ ሁሉም እንደሃይማኖቱ እንዲኖር እንደሰማችሁት አዋጅ ሰጥቻለሁ ወይስ ሌላ የምትፈሩበት ነገር አላችሁ? አትፍሩኝ የልባችሁን ንገሩኝ” አላቸው። የጦቢያ አባት

እንዲህ ያለ ደግ ቃል ከዚህ ህፃን ንጉሥ በሰማ ጊዜ ድሮ ልቡ ወለል አለና ምስጢሩን ሁሉ አውጥቶ ሊነግረው አሰበ። ቀጥሎም “ንጉሥ ሆይ! ከቤቴ የቀረችው ሚስቴ ብቻ ናት። እኔ ከዚህ ልጄ ጋር ከቤቴ ተወጣሁ ብዙ ጊዜዬ ነው። አንዱ ልጄ አንድ ትልቅ ውለታ የዋለልን ሰው ያለበትን ስፍራ ለመፈለግ ከቤቱ ከወጣ ይኸው ዓመት ሆነው። እኛም ወሬውን ብንጠይቅና ብናስጠይቅ የደረሰበቱን፣ ደብዛውን አጣነው። አሁን የምናደርገውን ብናጣ አገር ለአገር እየዞርን እርሱን ለመፈለግ ሁለታችን ወጣን። በመፈለግ ላይ ሳለን “የእርሶ ሠራዊት አገር እያጠፉ መጣ፤ ደረሰ” ሲሉ በሰማን ጊዜ መጀመሪያ ወደኋላችን ለመሸሽ አሰብን ቀጥለንም እንዳላደረሰን ብናይ ፈረስ ተማይመታው ኮረብታ መውጣት ይሻለናል ብለን ወጣን፤ ነገር ግን መቼም ያጋጣሚ ነገር አይታወቅምና ንጉሥ ራስዎ አገኙን። ከዚህ የደረስንበት ጉዳይ ይኸ ነው” አለና ሲጨርስ የጦቢያን ሴትነት ገልጦ ሊናገር ‹ይቺ› ብሎ ገና እንደጀመረ ጦቢያ አፍዋን በእጅዋ እየተመተመች እንዳይናገር ተቆጣችውና ንግግሩን ለውጦ “ይህች ዓለም ላልታደላት ሰው ከንቱ ናት፤ እኛም ይኸው በልጄ መጥፋት ማልቀስ ከጀመርን አንድ ዓመት ሆነን። ስለዚህ ይኸ ልጄ ወዲህም ከእናቱ ተለይቶ፣ ወዲህም የሚወደው ወንድሙ ጠፍቶበት በሐዘን ሳለ ከዚህ ቤተ መንግሥት ገና ደስ ይለኛል ብሎ ለራሱ አድልቶ ይቀመጥ ዘንድ አይቻለውም” አለና ተናገረ። ጦቢያ ግን ሴትነቷን ገልጦ እንዳይናገር መከልከሏ አሕዛቦች ሴት አይተው አይለቁም ሲሉ ሰምታለችና ለዘለዓለሙ ከዚያው ይዞ እንዳያስቀራት ፈርታ ነው፤ ባንድ ወገንም፣ ሁሉን ቢናገሩ ሆድ ባዶውን ይቀራል እንደሚሉት ምስጥሩን ሁሉ ጨርሶ እንዳይዘረግፍ ብላ ነው አትናገር ያለችው።

ንጉሡ የጦቢያን ወንድም መጥፋት በሰማ ጊዜ “ምን ጊዜ ነው የጠፋው? ወዴቱንስ መልሶ ነው የሄደው? ከጠፋስ ስንት አመት ይሆነዋል?” አለና ጠየቀ። አባትየው “ከሄደም አንድ አመቱ ነው። ለመሄድ ያሰበበት የምስርና የሰናር ነጋዴ መሣፈሪያ ከሚባለው አገር ሽ(ን)ለቆ ነው። እድሜውም እንደዚሁ እንደ ጦቢያው ነው፤ ሁለቱም ይኸው ወደ አስራ ሰባቱና ወደ አስራ ስምንቱ ዓመታት ሊሆኗቸው ነው” አለና ነገረው። ንጉሡ አነሣና “እንግዲያውማ መንቶች ናቸዋ?» ሲል ጠየቀ። «አዎን ታሉስ በሁለንተናቸው አንድ አካል አንድ አምሳል ናቸው፤ ከቶም እንኳን ለባእዱ ለእኛም ለወላጆቹ ለመለየት አንዳንድ ጊዜም ያስቸግሩን ነበር። ይልቁንም ገና ልጆች ሳሉ በመልካቸው መለየት እየቸገረን በስማቸው ወይም በጥቅሻ ነው እንጠራቸው የነበር። ከፊታችን ሁለቱም ሲኖሩ አንዱን ታንዱ አንለያቸውም ነበር” አለና ተረከለት። ንጉሡ እያዘነ ሰማና “ከጠፋ አንድ አመት ከሆነው እርግጥ የእኛ ጦር አላገኘውም፤ የእኔ ሰው ቢይዘው ኖሮ ቶሎ አገኘው ነበር፤ ግን የእኔ ሠራዊት

ከዚህ አገር ተገባ ጥቂት ቀኑ ነው፤ ምን ይሆናል እኔ የምፈራለት የባሪያ ነጋዴ ብቻውን አግኝቶት ይዞ እዳይሸጠው ብዬ ነው” አለና ዝም ብሎ ይተክዝ ገባ። ንግግሩንም ቀጠል አደረገና፣ “ለሁሉም ነገር፣ ልጁ በዚህ ዓለም ካለ በምድር ላይ ቁሞ ከሄደ እንደምንም ፈልጌ አይገቡ ገብቼም ቢሆን ሳላገኘው አልቀርም፤ አይዟችሁ! ብቻ ይኸ ሁሉ ነገር ብዙ ጊዜ ያስፈልገዋልና እስከዚያው ድረስ እናንተው ከእኔ ጋር ተቀመጡ፤ ጦቢያ እልፍኝ ገቢ ከባለሟሎቹ ጋር ተቀማጭ ይሁን። አንተ አባትዬውም ከጨዋው ከመኳንንቱ ጋር ከአደባባይ አትለይ፤ ከፊቴም ለግብር አትለይ” አለና ፈቀደ።

አባትና ልጁ ለዚህ ቃል ምን ብለው ይመልሱ? አይሆንም ማለት የጠፋው ልጅ ወዲያው እንደጠፋ ይቅር ማለት ሆነባቸው፤ ለራሳቸውም ንጉሡ ከጨከነ በመከራ ላይ እንውደቅ እንደማለት ያለ ነገር መሆኑን ተገንዘቡና ተቸገሩ። የእዚህን ነገር ገና ባፋቸው ሲያንገራጩ ንጉሡ ተነስቶ “ዝግ ብላችሁ መከራችሁ ምላሹን ንገሩኝ” አለና ወደ ይላላ ሄደ። የጦቢያ አባት ከዚያ ወዲያ “ልጄ! ያንቺ ሴትነት እንዳይታወቅ ብዬ ብፈራ ነው እንጂ፤ ንጉሡ እንዳለን ሆነን ወንድምሽ ቢገኝልን እወድ ነበር። እንዳለን ካልሆነ እንኳን ወንድምሽ ሊገኝልን ለእኛውም ያስፈራናል፤ ምንስ ቢሆን የአረመኔ ንጉሥ መሆኑ ቀረ እንዴ?” አለና ነገራት። ጦቢያም «አባቴ ምን አድርጌ ከወንድ መካከል ተቀምጬ፣ እንደ ወንድ ተራምጄ፣ እንደ ወንድ ተናግሬ ይሆንልኛል? ደግሞስ ጊዜው የበዛብኝ እንደሆነ ደግሞ ገመናችን ይገለጥና የባሰ ነገር የመጣብን እንደሆን አሳዛኝ ነገር አይደርስብንምን? የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች እንደሚሉ ሁሉ ዋሕድ እንዲገኝ ስንጥር እስከኛውም የሰው መሳቂያ እንዳንሆን ብዬ እሰጋለሁ። ግና ቢሆን ምን አደርጋለሁ፤ ወንድሜ ከተገኘልን እሺ፤ ከዚሁ ገብቼ እንደባለሟሎቹ እቀመጣለሁ። ብቻ እግዚአትነ ማሪያም ገመናዬን ትሸሽግልኝ” አለችና ለአባቷ ነገረችው። አባትዬውም “እንግዲህ ከጨከንሽ ወዲያ አደራሽ እንዳይታወቅብሽ ንግግርሽም ቀጥ ያለ አረማመድሽም ሁለንተናሽም እንደ ወንዶቹ ይሁን” አለና መከራት። ንጉሡ ከይላላ እንደተመለሰ “ምን መከራችሁ?” ብሎ ጠየቀ። እነርሱም “እሺ ንጉሥ እንዳሉን እንሆናለን” አሉ።

ንጉሡ እንዳመኑት ባየ ጊዜ ደስ አለውና ወዲያው አባትና ልጅ እንዳይለያዩ አድርጎ የሚበቃቸውን ድንኳን የሚጭኑትን ፈረስና በቅሎ፤ የሚያዝዙትን አሽከሩን፣ ባሪያውን፣ ለጓሚውን፣ ጫኙን፣ ወጥ ቤቱን፣ የሚለግሡትን ብሩን፣ ወርቁን፣ አድርጎ በአንድ ጊዜ ንብረታቸውን አሟልቶ ሰጠና ከእርሱ አጠገብ ከሸማው አጥር ውስጥ ድንኳናቸው እንዲተከል አደረገ። ከዚህ ቀጥሎ ፊት እንደተናገረው ጦቢያን እንደ

ባለሟሎቹ ሽልሞ ወደ እልፍኝ አስገባ። አባትዬውንም እንደ መኳንንቱ አንቆጥቁጦ ሽልሞ በጨዋ ልጅ ሥፍራ አስቀመጠ።

ይኸን ባደረገ በበነጋው "ከአንድ ዓመት ወዲህ ወንድ ባሪያ የገዛህ አንድ የጠፋኝ ሰው አለና ሰብስበህ ወደ እኔ አምጣ። ይኸን ቃል በሰማህ ጊዜ እለቱን ይዘህ ወደ እኔ ተነሣ። ያን የምፈልገውን ሰው ይዘህ የመጣህ ሰው ይዘህ የመጣህበትን ዋጋ አሥር እጣፍ አድርጌ ሰጥቼ ወዲያው ሽልሜ እሰድሃለሁ" አለና በያገሩ፣ በያደባባዩ፣ በየሸንጎው፣ በየጣቢያው ሁሉ አዋጁን ለቀቀ። ከዚህ አዋጅ ወዲያ የሚገዛው አገር እጅግ ሰፊ ስለሆነ አንድ አምስት ስድስት ወራት ያህል አንድም ባሪያ ይዞ የመጣ ሰው አልነበረም። ይኸን ሁሉ ቀን ጦቢያና አባቷ ዝም ብለው ከንጉሡ ጋር ተቀመጡ፤ ከቀን ብዛት የተነሣ ንጉሡ ጦቢያን አጥብቆ ወደዳት እንደብርቅ ያያት ጀመር። ከጥንት ባለሟሎቹ አንድም እንደእርሷ አድርጎ የሚያቀርበው የለውም ነበር። ደግሞም ተመልኳ ጠባይዋ፤ ከንግግሯ ውበቷ እየተባበረ ጦቢያ የሰው ልብ ታዘናጋ ነበር። እንኳን ንጉሡ የንጉሡ አኅት እስተ ልጁ ከንጉሡ እልፍኝ አይለዩምና እያይዋት እጅግ ወደዷት፤ እጅግም አቀረቧት። ይልቁንም ያች የንጉሥ አኅት ልጅ ሥራዋ አይኗን ከጦቢያ ላይ መሰካት ብቻ ሆነ። ወሬዋ ሁሉ የጦቢያ ነገር ብቻ ሆነ። በዚህ ጊዜ ጦቢያን ያየችው የንጉሡ የአኅት ልጅ በጦቢያ ልቧ እንደተሰቀለና ፍቅር እንዳደረባት ዐወቀው። ከዚህም ወዲያ ለአኅት ልጅ "የገናው ባልሽ እንደዚህ እንደ ጦቢያው ቢያምር ትወጃለሽ?" እያለ ፍቅሯን ለማወቅ ባሽሙር ይጠይቃት ጀመር። እርሷም አብረው ታደጉ ዘንድ እንደ ወንድሟ አድርጋ ትወደው ነበርና ምሥጢር ታካፍለው ነበር። ስለዚህ ምሥጢር አድረጋ አባቷ ካፊር ወደደች ብሎ እንዳይቆጣት እርሱ እንዳይሰማ አድርጋ በጦቢያ ፍቅር እንዳደረባት ነገረችው። ከዚያ ወዲያማ እየጊዜው እንዲህ ትለው ገባች። "ከተወለድኩ እስከ ዛሬ ከአንተም ቤተ መንግሥት ቢሆን ከየትም ቢሆን እንደዚህ እንደአዲሱ ባለሟልህ እንደጦቢያ ያለ ወዘላ ከዚህ ቀረህ የማይሉት አላመል የተፈጠረ ጎበዝ አይቼ አላውቅም። እጅግ ሽንቅጥ ዓይናማ ነው። ምነው ካፊር ባልሆነ!" እያለች ትነግረው ጀመር። ንጉሡም "እውነትሽ ነው እህቴ ባገራችን እንደእርሱ ያለ ሰው አይገኝም" ይላታል። ይህችው ያኅቱ ልጅ ግን በመሽም በጠባም፣ በህልሟም በውኗም፣ ከጦቢያ በቀር ሌላ የሚታያት ነገር አጣች። በየጊዜው ከዚህ በቀር ለንጉሡ ሌላ የማታጫውተው ሆነ። ይህን ሁሉ ደፍራ የፍቅሯን ነገር ለንጉሡ ማጫወቷ፣ ከጦቢያ ጋር እንዲያጋባት ተስፋ አደርጋ ነው። ወይ አለማወቅ! ጦቢያ ግን ባትለብስ ነው እንጂ እንደእርሷው ሴት ነበረች።

ንጉሡ ግን ምንም የፍቅሯን ብርታት ቢያውቅ ባንድ ወገን አኅቴ እሺ ብሎ ልጁን ለክርስቲያን አይድርም ሲል ባንድ ወገን ደግሞ ጦቢያ እሺ ብሎ ያረመኔ ወገን አያገባም ሲል ፈራ። ከዚህ በቀር ጦቢያና ያኅቱ ልጅ ቢጋቡ ደስ ይለው ነበር።

ጦቢያ ግን ይህን ሁሉ ነገር አላወቀች፤ ዝም ብላ ቀን ቀኑን ከንጉሡ ፊት ትውላለች፤ ማታ ማታ ወዳባቷ ትሄዳለች። አባቷም "ልጄ እንዴት ውላ ይሆን፤ ነገራችን ታውቆብን ይሆን" እያለ በጭንቀት ይውልና ብቅ ስትልለት "ልጄዋ እንዴት ዋልሽ አገር ደኅና" ይላታል። ጦቢያም "በእግዜር ቸርነት እስካሁን ምንም የለብኝ፤ ንጉሡም የአኅቱም ልጅ በፍቅር ዓይን ያዩኛል" ስትለው፤ በማለዳም እንደልማዷ ተመልሳ ስትሄድ፤ አባቷም ሸኝቶ "የክርስቲያን አምላክ ይጠብቅሽ" እያለ ሲለቃት፤ ምንም ሽልታ ነገር ሳያገኛቸው ብዙ ቀን ተቀመጡ። ከቀን ብዛት አብሮ ከመዋል ዓይን ላይን ከመላመድ የተነሳ ያች የንጉሡ ዘመድ ጦቢያን ማነጋገርና አንዳንድ ቃል መወራወር ጀመረቻት። እርሷም፣ ያለበት ይበንበት እንዲሉ ሁሉ፤ ሴትነቷን እያወቀች ፈርታ ከወንድ ጋር፣ ከንጉሡም ጋር ቢሆን በግድ ታልሆነባት በቀር ደስ ብሏት አታነጋግርም ነበር፤ ያች የንጉሡ ዘመድ ስታነጋግራት ደስ እያላት እንደልቧ ትመልስላት ጀመር። ከዚህም የተነሳ ለሰዉም ለንጉሡም ይደንቀው ነበር። የንጉሡ ዘመድ ግን አብሶ "ፍቅሬ በከንቱ አልቀረም" ስትል ደስ ይላትና ተስፋዋም እያደረ ይገንባት ጀመር። ከንጉሡም ከእርሷም እያደር የጦቢያ ባለሟልነት በገነነ ጊዜ ባለሟል የተባለ ሁሉ ቅናትና ምቀኝነት አደረበት። "እንዴት በኋላችን ደርሶ አንድ ካፊር ይብለጠን!" ብቻ ሆነ የባለሟል ሁሉ ንግግር። በዚሁ ብቻ ጧትም ማታም ተጉተምታሚውና ተጉረምራሚው በዛ። ነገሩም አልቀረ። ለንጉሡ አኅት ነገሩን አሳቅለው ነግረው ጦቢያ በመከራ ላይ እንድትወድቅ ወይም ከእልፍኝ እንዳትገባ ለማድረግ አሰቡ።

ፊት እንዳልሁት ሁሉ ከዚያው ቤተ መንግሥት እንደ ጥንግ የተንከበከበ አንገቱና ወገቡ በሥፍራ የተጣሉበት ድንክ ነበርና ከእርሱ ጋር እንዲህ ብለው መሰጠሩ። ንጉሡ ከምሳ በኋላ ጥቂት እንቅልፍ ያሽልብ ነበርና እንደልማዱ እንቅልፍ ሲያሸልበው ያው ድንክ ጦቢያን የንጉሥ አኅት ልጅ ትጠራሃለች ብሎ ሊነግር፤ በዚህን ጊዜ ጦቢያ እሺ ብላ ያች የንጉሡ አኅት ልጅ ካለችበት ድንኳን ስትገባ ላባትዬውና ለንጉሡ አኅት ሄዶ ጦቢያ የሚሉት ካፊር ከልጅቱ ድንኳን አለጊዜው ገብቶ ተቀምጧል፤ የሚያደርገውን ነገር አናውቅም ብሎ ሊያሲዙ መከሩ።

በዚሁ ምክር ያ ድንክ አንዱን ቀን ንጉሡ እንደተኛ አይቶ ተፋጠነና “የንጉሡ ዘመድ ቶሎ ና ትልሃለች” አለና ለጦቢያ ነገራት። ጦቢያም በቅንነት እሺ ብላ ቶሎ ሄደች ደግሞም ይህን ሁላ ነገር አዙራ አላየችም ነበር። ነገር ግን ገና ከተጠራችበት ድንኳን ጥልቅ እንዳለች ያው የንጉሡ አጎት ነገሩን ሰምቶ ደረሰና ጦቢያ ተያዘች። ወዲያውም ባለሟል የተባለ ሁሉ ወሬውን በቶሎ ለሁሉ አደረሰው። ድሮ ያ ጦቢያ የሚባል አዲሱ ባለሟል ላቀንና የንጉሡን ዘመድ ብቻዋን ካለችበት ደፈራት። ጭር ባለበትም ጊዜ አይቶ አደጋ ጣለባት ተባለ። ንጉሡም ወዲያው ነገሩን ሰምቶ እውነት አልመስልህ አለው። አጎቱ ግን እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ደረሰና “ይህ ካፊር ካልተቀጣልኝ እሞታለሁ” አለና፤ ለንጉሡ ነገረ። ንጉሡም “ያን የመሰለ እንዲያ የረጋ ልጅ ሲጠይቁት እንኳ ለመመለስ ያፍር የነበር፤ እንዴት ደፍሮ እንዲህ ያለ ነገር ሊሰራ ይችላል?” ሲል መለሰ። አጎቱ ግን “እኔው በገዛ እጄ ደርሼ ይገፄዋሁና ካልተቀጣልኝ” አለ። ከዚህ በኋላ ንጉሡ “ይህ ነገር ከሆነ እርግጡን ከእርሱ ከጦቢያ ጠይቄ አባቱንም እርሱንም አንድነት ተፊቴ አርቃለሁ፤ መቅጣት ግን ገና ካገኘኋቸው ዕለት ጀምሮ ምንም እንዳላደርጋቸው ቃል ሰጥቻቸዋለሁና አይሆንልኝም” አለ። ወዲያውም ጦቢያን ከተያዘበት አስመጣና “ከቶ ነገሩ ምንድር ነው? በምን ነገር ነው ከእህቴ ድንኳን አለወትሮህ የገባኸው?” አለና ጠየቃት። ጦቢያም ምንም በዚህ ነገር ሴት ናትና ላለፈውም ለሚመጣውም ባትውልበት በዚህ ምክንያት የተሸሸገው ሴትነቷ እንዳይገለጥባት ፈርታ ሁለንተናዋ ይንቀጠቀጥ ጀመር። መልኳም በፍርሀት ተለዋወጠ። ነገር ግን ከፊቷ ላይ ከንጹሕነትና ከእውነተኝነት በቀር የሐሰተኝነትና የበደለኛነት ምልክት አይታይባትም ነበር። ይሁን እንጂ የምትመልሰውን ነገር አጣች። “ተጠርቼ ነው የሄድሁ” እንዳትል ያጎቱን ልጅ ማሳጣት መሰላት። ጭራሹን ዝም ብላ ሲያያት ጊዜ ንጉሡ “ምነው ዝም ትላለህ? ነገሩን አትነግረኝም እንዴ? ጭምት ነህ፤ የተሠራህና የተቀጣህ ጭምት ልጅ ነህ ብዬ ለብዙ ቁም ነገር ስመኝህ እንዲህ ታደርግ?” ብሎ ሲናገር አባቷ ደረሰና “ንጉሥ ሆይ! የእኔ ልጅ እንዲህ ያለ የእረኝነት ሥራ አያደርግምና የሰው ነገር አይስሙ፤ እኔን ይመኑ” አለና ተናገረ። አጎትዮው በዚህ ተናደደና “እኔ በገዛ እጄ ደረስሁበት ስል እኔን ማሳበሉ ነው እኮ?” አለ። ይህ ሁሉ ሲሆን ጦቢያ አንገቷን ሰብራ ምድር ምድሩን ስታይ የነበረችው ቀና አለችና እንዲህ አለች “ንጉሥ ሆይ! ጥንቱንም የቤተ መንግሥት ነገር ባለማወቄ ስፈራ እኔን ድኃውን ያልተገባሁትን እርስዎ መርጠው ከፊትዎ እንዳልለይና ከእልፍኝዎ እንዳሻዬ እንድገባ ፈቀዱልኝ። አሁን ግን እውነት ከመሰልዎ ማጥፋቴን ካወቁ ይቅጡኝ። ነገር ግን ታወቁኝ ጀምሬ አስካሁን ግብሬ በጀም፣ አልበጀም ያው ነው፤ ቢመስልዎ ይተዉኝ ባይመስልዎ ይቅጡኝ፤ ብቻ በእኔ

ኃጢአት አባቴን አይጥሉብኝ፤ በሰጡኝ ቃል ወንድሜንም ፈልገው ያስገኙልኝና ለአባቴ ያስረክቡልኝ። በእኔ ኃጢአት ወንድሜ እንደጠፋ አይቅር" አለች። ንጉሡም “ይኸስ ይሁን ምነው ነገሩን ከእህቴ ድንኳን የገባህበትን አትነግረኝም?” አለና አስጨንቆ ያዛት፤ እርሷ ግን ሰው ላለማሳጣት ብላ ጠቅጥቃ ዝም አለች ንጉሡም ተቸገረ። ሆነም ሊል ቸገረው፤ ካንደበቷ የሚወጣው ነገር ሁሉ የእውነት እንጂ አንድ የሐሰት ቃል እንደሌለበት ይታወቅ ነበር። አልሆነም እንዳይል ጦቢያ ሁሉንም ጠንክራ ይዛ አልናገር አለች። በኋላ ግን ነገሩ እንደጠነከረ አይቶ የጦቢያ አባት ልቡ ተሸበረ። ተስፋውንም ቆረጠ። በዚህ ነገር የጠፋውም ልጅ ሳይገኝ እንደሚቀር ጦቢያም ባልዋለችበት ነገር እንደ ምትቀጣና እርሱም ራሱ ተሁለቱም ልጆቹ አንዱንም አጥቶ በሐዘንና በኃፍረት እንደቤተ ክርስቲያን ውሻ ውቃቢውን ተገፍፎና ተባርሮ እንደ ሚሄድ ዐወቀና ፈራ። ቀጥሎ ገና ይህ ሁሉ ነገር ሳይደርስበት በፊት ምሥጢሩን ለንጉሡ ለማውጣት አሰበና “ሰዉ ሁሉ ይከልከልልኝ” አለ። ሰዉ ሁሉ እንደወጣ አይቶ “ንጉሥ ሆይ! ሰው ባልዋለበት ይሞት ዘንድ ዛሬ ብቻም አልተጀመረ፤ እርስዎም ምንም ብልኅ ምንም መሐሪ ንጉሥ ቢሆኑ እንደ ሁሉ ሥጋ ለብሰዋልና በሰው ልብ ገብተው እውነቱንና ሐሰቱን ይለዩ ዘንድ አይቻለዎም። ሰው የነገረዎትን እንደሚያምኑ የታወቀ ነው። አሁንም ነገሩን ሁሉ ገልጬ እነግርዎ ዘንድ ምሥጢሩ ከእኛ እንዳይወጣ ቃልዎን ይስጡኝ” አለ። ንጉሡም እሺ ብሎ ቃል ሰጠው። ከዚህ ወዲያ የጦቢያ አባት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ምሥጢሩን ሁሉ ለነገ ሳይል የጦቢያንም ሴትነት ገልጦ ነገረው።

ንጉሡ ይህን በሰማ ጊዜ እጅግ አዘነ፤ እጅግም ነገሩ ደነቀው። የጦቢያ ነገር ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው አሳዘነው። ወዲህም በወንድ ተመስላ መከራዋን እያየች ወንድሟን አገር ላገር መፈለጓ፤ ወዲህም እነዚያ ባለሟሎቹ በምቀኝነት ባሏለችበት ነገር አሻኩረው ሊያስቀጧት እንደነበር ስታውቀው አለማሳጣቷ ገረመው። ይኸው ንጉሥ ነገሩ ምንም ቢያሳዝነው ባንድ ወገን እጅግ በጦቢያ ሴትነት ደስ አለው። ፍቅሩ ጥንት በውቃቢ ብቻ ሴትነቷን ሳያውቅ ነበር። አሁን ግን ያው ፍቅሩ ወደ እውነተኛው ፍቅር ተለወጠና ተስፋው ሌላ ሆነ። ድሮ በእርሷ ፍቅር ልቡ ተሸወጠና ደረቱን ይገምሰው ጀመር። ፍቅር እንደ ቀጭን ብርድ በሁለንተናው ገባበትና ያንከፈከፈው ጀመር። ነገር ግን አባትና ልጁ እንዳያውቁበት ተጠንቅቆ ይናገር ነበር። እነዚያን ቅናተኞች ባለሟሎቹን ለመቅጣት ይወድድ ነበር። ነገር ግን ምሥጢራቸው እንዳይወጣ ተነጋግረዋልና የማይሆን ሆነ። ኋላ ግን ንጉሡ አሰበ አሰበና ለሰው ይምሰል ለቅጣት አስመስሎ ጦቢያ ዕለቱን የባለሟልነቷን ልብስ ለውጣ እንደ ጥንቷ ለብሳ ከእልፍኝ ልትወጣና ካባቷ ጋር በድንኳን ርቃ ልትሠፍር

ወደደ። ላባትና ልጁ ይኸን አሳብ ነገረና በምሥጢር አድርጎ ብዙ ወርቅ ብዙ ከብት ሰጠና ድንኳኑን ቤተሰቡን ጨምሮ "ሂዱ በሩቁ ስፍራ ተቀመጡ" አለና ስፍራውን አሳይቶ ጦቢያ ከድንኳን እንዳትወጣና ሰው እንዳያያት፤ አባትዬው ግን ከአደባባይ ተቀን አንድ ጊዜ ብቻ እንዲወጣ አድርጎ መካከረና ሰደዳቸው። የሚሰፍሩበት ስፍራ ግን ከንጉሡ ድንኳን ፊት ለፊት ነበር። ንጉሡ ባይሆን እንኳ በመነጠር ጧትና ማታ ጦቢያን ማየት ተስፋ መሰለው። ስለዚህ ለማየት ወደ ሚመቸው ስፍራ ሰደዳቸው። የንጉሡ አጎትና እኒያ ባለሟሎቹ ጦቢያ የባለሟለነት ልብሷን ትታ ከእልፍኝ ወጥታ ስትሄድ ጊዜ የቅጣት መስሏቸው ደስ አላቸው። ያች የንጉሡ ዘመድ ግን የጦቢያን ከእልፍኝ መባረር በሰማች ጊዜ ደንግጣ በሐዘን ጧትና ማታ ማልቀስ እንጂ እህል ውኃ መቅመስ ቸገራት። ንጉሡም እንደ እህቱ ነበረና ተቸገረ ተጨነቀ። ይልቁንም መጨነቁ የጦቢያ ፍቅር እንዳደረባት አይቶ ነው። በምሥጢር የጦቢያን ሴትነት እንዳይነግራት ምሥጢር እንዳይወጣ ቃል አለበት።

ጦቢያ ከእልፍኝ ከሄደች አያል ቀን ሆነ፤ ባለሟል የተባለ በሥራው ሥራ ደስ ብሎት ውስጥ ለውስጥ እየሳቀ ሲቀመጥ ንጉሡ ባንድ ወገን እንዳላወቀ ሁሉ ላይ ላዩን እየሳቀ ትዝብቱን በሆዱ እያሞራሞረ ተቀመጠ። ጦቢያ ግን ይህን ሁሉ አላቋረጠችውም በማንም ቂም አልያዘች፤ ብቻ "አዋጁ በየአገሩ ደርሶ መቼ ወንድሜ ዋሕድ ይመጣልኝ ይሆን?" እያለች ትመኛለች። ተስፋዋ እርሱ ተገኝቶላት በደስታ ሁሉም ባንድነት ወደ እናቷ መመለስ ብቻ ነበር።

ንጉሡም እርሷን ደስ ለማሰኘት ውስጥ ለውስጥ ለያገሩ ምስለኔ ሁሉ "አደራ አፋጥናችሁ ከአመት ወዲህ የተሸጠውን ባሪያ ቶሎ ላኩ" ብሎ ጻፈ። ይኸ ሁሉ ፈጥኖ በየአገሩ ተሰማና በዚያም በዚያም ሰዉ ባሪያውን እየያዘ ብቅ ይል ጀመር። ንጉሡ አዋጁን ሲነግር የተገዛበትን ወርቅ አሥር እጥፍ አድርጌ ሰጥቼ ወዲያውም እሸልማለሁ ብሎ ነበርና ባሪያ ከቤቱ ያለው ሁሉ እየሰበሰበና እየያዘ እኔ እቀድም እኔ እቀድም እያለ ደረሰ።

በዚያን ጊዜ ንጉሡ ደስ አለውና የጦቢያን አባት በስውር አድርጎ ከጦቢያ ጋር ሆኖ ሁለቱም የሚያልፈውን ባሪያ ሁሉ እንዲያስተውሉ መከረና ሰደደ። ከዚያ ወዲያ ያ የተሰበሰበው ባሪያ ሁሉ በነጦቢያ ድንኳን ፊት ለፊት እያደረገ ዝግ እያለ እንዲሻገር አዘዘ። በበነጋው አንዳንድ እያለ ከነግህ እስከ ሠርክ ድረስ ሲሻገር ዋለ። ጦቢያና አባቷ ከድንኳኑ አፍ ተቀምጠው ዓይናቸው እስኪፈዝ ድረስ ሲመለከቱ ዋሉ፤ ነገር ግን ዋሕድ ከዚያ ታለፈው ባሪያ ሁሉ መካከል አልተገኘም። ወደ ማታ ግድም ጦቢያም አባቷም ተስፋ መቁረጥ ጀመሩ። ጊዜውም መሸ የቀረው ባሪያ ነገ

ማለዳ ማለፍ ይጀምራል ተብሎ አደረ። ንጉሡም እንደ ዋዛ በመነጠር እያሾለከ "ካሁን አሁን ያገኙት ይሆን" እያለ እነጦቢያን ሲመለከት ውሎ እንዳላገኙት አወቀና አዘነ። ጦቢያም አባቷም ሌሊቱን ሁሉ በጭንቀት አደሩ። በማለዳ ግን እንደ ትላንትናው ከድንኳናቸው ደጃፍ ቁጭ ብለው እንደገና ያዩ ጀመር። ግን ቀኑን ሁሉ ምንም ሳያገኙት ዋሉ። ጊዜውም መሸ የቀረውም ባሪያ ለነገ ተባለ። የአባትና ልጁ ሐዘን እጣፍ ሆነ "ዋሕድ ሞቶ ነው እንጂ ይኸን ጊዜ እናገኘው ነበር" ይሉ ጀመር። በሦስተኛው ቀን እስከ ቀትር ድረስ ምንም ሳያገኙ ዋሉ ተስፋ ማድረጉንም ተዉት። የሚልፈውንም ባሪያ አተኩረው ለማየት ሰነፉ፤ ብቻ አንዳንድ ጊዜ ቀና እያሉ እያዩ ሲተክዙ ወደቀን እኩሉ የላይ ጢሙን ከተቆረጠ የእስላም ነጋዴ ጋር በጎኑ ከጫንቃው ላይ ርኮት አንጠልጥሎ እየተከዘ የሚሄድ አንድ ወጣት ልጅን ጦቢያ በሩቅ አየች። ዛላውና አረማመዱ የወንድሟን መሰላት ነገር ግን መልኩ በፀሀይና በአመዳይ ክስል ብሎ ጠቋቁሮ ነበርና ይሆንን አይሆንን ስትል ዋሕድ ወዙን በነጠላው እየጠራረገ በጣም ቀረበ። ጦቢያ እርግጥ ወንድሟ መሆኑን ባወቀች ጊዜ ለአባቷም መንገሩን ረሳች ብቻ ሁለት እጅዋን ወደ ዋሕድ ዘርግታ አእምሮዋ ጠፍቷት ወደቀች። አባትዬው ግን ነገሩን ሳላወቀ "ልጄ ምን ሆነችብኝ" ሲል እርሷን ለማንሳት ወደ ወደቀችበት ተጎነበሰ። በዚህ ጊዜ ዋሕድ አባቱ መሆኑን ለየውና የጫንቃውን ርኮት አምዘግዝጎ "አባዬዋ ከዚህ ምን አመጣህ?›" አለና አቀፈው አባትዬውም ገና ጦቢያን ከወደቀችበት ሳያነሳ የጠፋው ልጁ መሆኑን ባወቀ ጊዜ ዘሎ ወደቀ። ሦስቱም እየራሳቸው የናፍቆት ስስትና የደስታ ድንጋጤ ያዛቸውና ተፋዘዙ፤ ንግግርም ተሳናቸው፤ ሁሉም ዲዳ መሰሉ፤ ይህ ሁሉ ሲሆን ዋሕድ ጦቢያን አላስተዋለም ነበር። ጠጉርዋን ተቆርጣ እንደ ወንድ ለብሳ ለምዷን አጥልቃ ባያት ጊዜ ሌላ ሰው መስላው ነበር። ኋላ ግን ነፍሳቸው ጥቂት እንደተመለሰ እየተላቀሱ መጠያየቅ ሲጀምሩ ነፍሳቸው ጥቂት እንደተመለሰ እየተላቀሱ መጠያየቅ ሲጀምሩ መቼም ንጉሡ ሁሉንም በመነጥሩ ይመለከት ነበርና ያ የጠፋው ሰው መገኘቱን አወቀ። ወዲያውም ያው የተገኘው ልጅና እርሱኑ ያመጣው ሰው ወደ እርሱ እንዲመጡ አዘዘ። ንጉሡ ዋሕድን ባየ ጊዜ ደስታ ፈነቀለው። እውነትም የጦቢያን ቁርበት ገፎ የለበሰውን እንጂ ሌላም አይመስል ነበር። ጦቢያን ባለሟል ሳለች ያወቃት ሁሉ እንደገና ንጉሡ ምሯት እርሷው ራሷ የመጣች መሰለው እንጂ ሌላም አይመስል ነበር። ጥቂት ዋሕድና ጦቢያ የሚለያዩበት በአተያይ በአነጋገርና በንቃት ብቻ ነበር። ጦቢያ ምንም ልሸሽግ ብትለው ነገሯ ሁሉ ወደ ሴትነቷ ያደላባት ነበር። ንጉሡ ለሰው ባያስታውቅ ነው እንጂ ደስ ብሎት "እንግዲህ ለአህቴ

ባል አገኘሁላት። መቼም እርሷ ሌላ መሆኑን አትለየውም፤ ያው የወደድሁት ጦቢያ ተመለሰልኝ ብላ ነው ደስ የሚላት” እያለ በሆዱ ያሰናዳ ነበር።

ወዲያው ንጉሡ ዋሕድን ላመጣው ነጋዴ እስታነሳው ድረስ ወርቅና ብር ሰጥቶ ሸልሞ አሰናበተ ዋሕድን ግን “አሳድግሃለሁ አስመችቼ አኖርሃለሁ፣ ከእኔ ጋር ኑር” አለው። ዋሕድም በበኩሉ ተጨንቆ “ንጉሥ ሆይ፣ አንድ ትልቅ ውለታ የዋለልኝ ነጋዴ ጠፍቶኝ እርሱን ካላገኘሁ አርፌ እንዳልቀመጥ ምዬ ከቤቴ ወጣሁ። ይኸውና እርሱን ስፈልግ ብዙ መከራ አገኘኝ፤ ቀጥሎም ባሪያ ሆኜ ተሸጥሁ፤ አሁን እርስዎ ባያወጡኝ ከዚያው እንደሌሎቹ መቅረቴ ነበር። እንግዲህ ለዚህ ካበቁኝ እርሱን ስፈልግ እሞታለሁ እንጂ ራሴን ወድጄ ደስ ካለኝ ብዬ ከዚህ መቀመጥ አይቻለኝም፤ አይዘኑብኝ፣ እኔ ጌትነት ይቀርብኛል እንጂ ለእርስዎ አሽከር አይታጣም” አለና ነገረው።

ንጉሡ አስተውሎ ሰምቶ ቁም ነገረኛነቱን አድንቆ ሲያቆም “በዚህስ ከሆነ አታስብ፤ እንዳገኘሁ እርሱንም በየትም አስፈልጌ አስገኝልሃለሁ። አንተ ብቻ ከእኔ ጋር እንድትቀመጥ፣ እሺ በለኝ” አለው። ዋሕድም “ንጉሥ ሆይ ይኸንማ ታደረጉልኝ እንኳን በደስታ እኖራለሁ ሲሉኝ ባሪያ ቋሚ አድርገው ቢገዙኝም ደስ እያለኝ እገዛልዎታለሁ ምን ከፍቶኝ” አለና መለሰ። ንጉሡ ለዋሕድ እንዳደረገው ሁሉ ወዲያው እለቱን “ነጋዴ የሆንህ ወረታህንም የዘረፋው ጊዜ የተገፈፍህ ወረትህን እንዳስመልስልህ፤ ወረትህንም ያልተቀማህ ለእንግዲሁ በየሄድክበት ሁሉ እንዳትነካ ድብዳቤ እሰጥሃለሁና ከተት፤ አዋጁን እንደሰማህ ገስግሰህ ድረስ” አለና በያገሩ አስነገረ።

ዋሕድም በማግሥቱ ጦቢያ በነበረችበት ቦታ የባለሟል ጌጥ ተሸልሞ እልፍኝ ገባ። ንጉሡም እጅግ አቀረበው፤ ባለሟል የተባለ ሁሉ እንደልማዱ በቅናት ይፈጠረቅ፣ እርስ በርሱ ይመሳጠር ጀመር። ንጉሡ ግን የጦቢያ ነገር እንዳይደርስበት ፈርቶ ከፊቱ እንዳይለይ ከእሱ በቀር ማንም ቢጠራው እንዳይሰማ ከትእዛዝ ጋር መከረው። ከዚህ ወዲህ ንጉሡ እናዳለው ተጠንቅቆ ቀን ቀኑን ከእልፍኝ ከንጉሡ ጋር እየዋለ ማታ ማታውን ወደ አባቱና ወደ እኅቱ እየሄደ ያድራል። የንጉሡ ዘመድ ግን በጦቢያ ነገር ተታማች ወዲያ፣ አባቷ ባለሟሎች ከሚገቡበት ከንጉሥ እልፍኝ እንዳትገባ ለብቻዋ ከድንኳኗ እንድትቀመጥ አድርጎ ከልክሏል። ስለዚህ የዋሕድን እልፍኝ መግባት አታውቅም ነበር። ንጉሡ ግን አንድ ቀን መቼም በጦቢያ መሄድ እንዳዘነች እንዳለቀሰች ያውቃልና ለዚያችው ለዘመዱ በምሥጥር አድርጎ “አይዞሽ እህቴ ጦቢያ ሄደ ብለሽ አትዘኝ፤ ተወደድሽው ተመልሶ እንዲመጣ አደርጋለሁ”

አለና ነገራት። እርሷ ግን ይህን በሰማች ጊዜ ደስታና የጦቢያ ናፍቆት ይዟት ነበርና ዝም ብላ እንባዋን ታዝረከርክ ጀመር። ቀጥላም "ጌታዬ፣ ወንድሜ፤ ይህንማ ታደረግህልኝ፤ ይህ ሁሉ ጌትነቴ ማዕረጌ ቀርቶብኝ ወጠ ሰሪ፣ ገንቦ ተሸካሚ ሆኜ ወረታህን እከፍልሃለሁ፤ እውነት ነው ያንተ ወገን ሆኜ ምን የሚጎድለኝ ምን የሚቸግረኝ ነገር ይገኛል። ይኸ ሁሉ ማዕረግ፤ የተመኙት ነገር ካልሆነ በዚህ ዓለም ምንም ደስታ የለውም። ሁሉም ከንቱ ነው፤ ሁሉም አጓጉል ነው። ታጓጉል ጌትነት ሙሉ ድኅነት ይሻላል። አሁንም እውነት ጨርሳ ደስ ይበላት ያልህ እንደሆነ፤ በጦቢያ እጅግ ፍቅር አድሮብኛልና ለእርሱ ሚስትነት አብቃኝ። ሌላ ነገር አላስቸግርህም፤ ጌትነቱም ሁሉም ይቅርብኝ፤ እንዳንዲቱ ገረድህ ሰርቼ አገለግልሃለሁ" አለችና መደምደሚያዋን በእንባ አስረዳችው። ንጉሡ ገና ሳይመልስላት የእርሷ አባት የንጉሡ አጎት ደረሰና ትቷት ተነሣ፣ እርሷም ምላሹን ለማግኘት እንደቸኰለች ከዚያው ቀረች።

ንጉሡ ግን ለሰው የማይናገረው ነገር ሆኖበት ነው እንጂ ለራሱ በጦቢያ ፍቅር ልቡ ተነድፎ ሲናገርም ዝንጉ ሆነ። ለመናገር ያሰበውንም ጉዳይ ይረሳው ጀመር። የጀመረውም ነገር እየተረሳው አሥር አሥር ጊዜ መደጋገም ብቻ ሆነ። ማታ ግብር ከተመለሰ ወዲያ ሰውን ያሰናብትና ጭር ሲል ብቻውን ከድንኳኑ ውጭ አውታሩን ተደግፎ ቁሞ የጦቢያን ድንኳን ሲመለከት እስከ መንፈቅ ሌሊት ያመሸና እንቅልፍ ሲያሸንፈው ይገባል። በማግስቱም እንደዚሁ ያደርጋል። ምንም እንኳ ጦቢያ እንዳትታየው ቢያውቅ ያለችበትን ሥፍራ ማየቱ ተስፋው ነበር። ምን ያድርግ የመጀመሪያ ፍቅሩ ነው። ከጦቢያ በቀር ሴት ወድዶም አስቦም አያውቅም ነበር። እርሷን ሳያይ በፊት "ፍቅር የሚሉት ምንድር ነው?" እያለ ያላግጥ ነበር። ደግሞም እስከዚያ ድረስ ገና ያልባለቀ ልጅ ነበር። እርሷን ከወደደና ለሚስትነት ከተመኘ ወዲህ ግን የጦቢያ ነገር እንዲያውም ህልም ሆነበት። በጨለማ ቀስ ብሎ እየሄደ "እንዴት ዋልሽ? እንዴት አደርሽ?" ቢላት ደስ ይለው ነበር። የብርቱነቷን፣ ያፋራምነቷንና የሃይማኖቷን ነገር ያውቃልና እየፈራ ይቀር ነበር። ማለዳ ወንድሟ ዋሕድ ሲመጣ ሳስቶ "ጦቢያ እንዴት ናት?" ብሎ ይጠይቃል ይነበረው ተስፋ ይኸው ብቻ ነበር።

በዚህ መካከል በአዋጅ እያገሩ ያለ ነጋዴ ሁሉ ይሰበሰብ ጀመር። ገንዘቡን ከብቱን የተዘረፈውም እንዲመለስለት ገንዘቡ ያልሄደበትም ለገናው ፈርቶ ደብዳቤ ለመቀበል አንድ ለምልክት ነጋዴ አልቀረም። ሁሉም ተጎለጎለና/ተሰበሰበና/ ደረሰ። ንጉሡ በዚህ ጊዜ ደስ አለውና ዋሕድን ያን የምትፈልገውን ነጋዴ በፊቱ እንዲሻገር

አድርጎ አዘዘ። እርሱም እሺ ብሎ ካናቋው በር ሆነና የሚሻገረውን ነጋዴ ሁሉ ባይኑ ሲቀላውጥ ዋለ። ግን እስከ ተሲያት ድረስ አላገኘውም፤ በማግስቱም እንደትላንቱ በሩን አንቆ ሲመለከት ወደ ደረቅ ረፋዱ ያ ደግ አድራጊው ነጋዴ ወረቱን ሁሉ ተቀምቶ ኑሮ አዝኖ ተከዞ ከስቶ ወራዳ ልብሱን በጫንቃው ላይ ጥሎ ሲመጣ አየው። ዋሕድ የሚተነፍሰውን አቋርጦ ዘለለና ፊቱንና ጉልበቱን ሳመ፤ ቀጥሎም አንገቱን አቅፎ ይዞ ሳመ። እንደዚሁም "እንዴት ነህ ታዳጊዬ? እንዴት ነህ ለጋሱ ጌታዬ?" እያለ ይጠያይቀው ጀመር። ምንም ያው ነጋዴ በሐዘንና በመከራ መልኩ ቢለዋወጥና ቢጎሳቆል የዋለለቱ ደግ ስራ አላስረሳውም፤ አላስናቀውም። እርሱ ግን ዋሕድን ተሸልሞ አብቦ ባየው ጊዜ ያየበት ስፍራ ጠፍቶት ተጨነቀ። ኋላ ግን ነገሩን ሁሉ ዋሕድ በነገረው ጊዜ ጥንቱንም ስጦታው በዚህ ዓለም ቢታወቅበት አልወደደም ነበርና እንደ ከፉ አድራጊ ዐፈረ፣ ደነገጠ።

ንጉሡ የእዚህን ነጋዴ መገኘት እንዳወቀ ወዲያው አስጠራና እርሱ በገዛ አፉ "ይኸን ያህል ከብት ይኸን ያህል ወርቅና ብር ጠፍቶብኛል" ብሎ በተናገረው መሰረት ሁለት እጥፍ አድርጎ በሚገዛው አገር ነጋድራስ አሰኝቶ ሹሞ ለቀቀው። የሰው ውለታ ከፉም ቢሆን በጎ በወዲያኛው ዓለም ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ጊዜም በዚህ ዓለም ፍዳው ወይም ካሣው ባድራጊው ላይ ይደርሳል።

ይኸን ሁሉ ነገር አሣምሮ ከጨረሰ ወዲያ ንጉሡ ዋሕድንና አባትዬውን ለብቻቸው አድርጎ በምሥጢር "የምትወደው ልጅህ ጠፍቶብህ ስታለቅስ ፈልጌ አግኝቼ ይኸው አንተን ደስ አሰኘሁህ፤ እንባህንም አደረቅሁልህ" ደግሞ ወደ ዋሕድ ዙሮ "ስትፈልግ ከመሸጥ የደረስህበትን ሰው በአዋጅ አስፈልጌ አስገኝቼ አንተንም ደስ አሰኘሁህ። ስለዚህ ሁለታችሁም ወረታ መመለስ ይገባችኋልና፤ ወረታዬን መልሱልኝ" አላቸው። ይኸን ቃል በሰሙ ጊዜ ሁለቱም ተጨነቁ። ቀጥሎም "ንጉሥ ሆይ! እውነት ነው ትልቅ ወረታ ይገባዎታል፤ ነገር ግን እንደኛ ያለ ምስኪን ከማመስገንና ከመመረቅስ፣ እድሜዎም እንዲረዝም እግዚአብሔርን ከመለመን በቀር ምን የሚቻለን ነገር ይገኛል? ለእርስዎ በዚህ ዓለም የሚሳንዎና የሚቸግርዎ ስላልኖረ የተመኘነውን ሁሉ አደረጉልን። እኛ ግን ለእርስዎ የሚገባ ውለታ እናደርግ ዘንድ እንዳይሆንልን እርስዎ ያውቃሉ፤ ደግሞስ በዚህ ዓለም ምን የሚቸግርዎና የሚያቅትዎ ነገር አለና ከእኛ አንድ ወረታ ይጠብቃሉ?" አሉና በአክብሮት መለሱለት።

ንጉሡም አስተውሎ ሁሉንም ሰማና "እውነታችሁ ነው፤ ሁሉ ይቻለኛል ንጉሥ ነኝ፤ መንግሥቴም እጅግ ሰፊ ነው። እኔ ምንም ልጅ ብሆንና እናት አባትም ደጋፊም

ባይኖረኝ የእኔ አምላክ ሁሉን አሟልቶና አሳክቶ ሰጥቶኛል። ነገር ግን ጨርሶ ደስ ይለኝ ዘንድ አንድ ነገር ብቻ ይቀረኛል። ይኸውም ነገር ከእናንተ ዘንድ በቀር ከሌላ አይገኝም። ደግሞም ንጉሥና ሀብታም ብቻ አይደሉም ወረታ ማድረግ የሚቻላቸው። ንጉሥም ከድኃው ደገፋ ካላገኘ ከቶ በሰላማዊ ኑሮ ሊመራ አይቻለውም፤ መንግሥቱም መንግሥት፤ ትዳሩም ትዳር አይሆንም። አሁንም የማይቻላችሁን ነገር አልለምናችሁምና 'እሺ በሉኝ' " አላቸው።

እነእርሱም ቸገራቸውና "ነገሩን እስኪ እንወቀው፤ ከሆነልን ለንጉሥ እንቢ የምንለው ነገር የለንም" አሉ። በዚህ ጊዜ ንጉሡ እንዲህስ ታላችሁ "ከበግና ከፍየል መካከል ከሚኖር ቀበሮ፣ ከሚስቱ ጋር ጭሮ የሚኖር ዶሮ ይበልጣል። እኔም ምንም ሁለንተናው ተዘጋጅቶልኝ ብታዩት ጨርሶ ደስ አላለኝም። ጭራሽ ደስ ብሎት ይኑር ብላችሁ ታዘናችሁልኝ፤ አንተ አባትዬው ጦቢያን በሚስትነት መርቅልኝ እጅግ ወድጃታለሁ፤ ሞቴም ሕይወቴም በእርሷ ይሁን አንተም ዋሕድ የምወዳትን የአኅቴን ልጅ መርቄ እሰጥሃለሁና አግባ እርሷንም ታገባህ ወዲያ ከአንተ በላይ ሹም እንዳልሾም ቃሌ ነው" አለና ጨረሰ።

አባትዮው በሃይማኖት ነገር ጦቢያ እጅግ ብርቱ ነበረችና፤ ፈርቶ ተጨነቀ። ኋላ ግን "ቀን ይስጡኝ መክሬ እነግርዎታለሁ" አለና ተለያዩ። ዋሕድም ፊት የእኅቱን መጨረሻ ነገር ለማወቅ ዝም ብሎ ቆየ።

ጦቢያ ነገሩን በሰማች ጊዜ ደነገጠች፤ ነገሩም ደነቃት፤ ጦቢያ ከልጅነቷ ጀምራ የኩራትና የጌትነት ነገር አታስብም ነበርና ቶሎ እሺ አላለችም። ብቻ ታስብ ጀመረች። እንቢ እንዳትል ያ ንጉሥ የዋለላትን ወንድሟን ከባርነት ያዳነላትን ወረታ ማጥፋት ሆነባት፤ ባንድ በኩል የእርሷ እንቢታ ለአባቷና ለወንድሟ ጠንቅ እንዳይሆንባቸው ፈራች። እሺ ብላ ያልተጠመቀ፣ ክርስቶስን ያላወቀ ሰው ማግባት ሃይማኖት እንደመለወጥመና ከክርስቶስ እንደመራቅ፣ በዚህ ኃላፊ መንግሥትም የወዲያኛውን የማያልፈውን ክብር እንደማቃለል ያለም ነገር ሆነባትና አይሆንም በማለቷ ቆረጠች። ከዚህ በኋላ አስቀድማ ወንድሟንና አባቷን ከመከራ እንዲያድንላት ክርስቶስን ተጨንቃና ተጠባ ለመነች። ቀጥላም ለንጉሡ እንዲህ ብላ ጻፈች።

"ንጉሥ ሆይ! የእኔን እጅ ስጠኝ ብለው አባቴን ለመኑ፣ ነገሩን በሰማሁት ጊዜ እጅግ ደነቀኝ። አሁንስ ጌታዬ እንደ እርስዎ ያለ ትልቅ ንጉሥ፣ እንደእርስዎ ያለ ጌታ ዓለምን በእጁ የጨበጠና በእግሩ የረገጠ፤ አዳሙ የሰገደለት አጀማመሩ ያማረለትና የገናው ያልተገመገመበት ሕፃን ንጉሥ እንዴት ተዋርዶ እንደ እኔ ያለች ድኃ ልጅ

ለሚስትነት ይመኛል? ይህ ነገር ቢፈጸም ለእኔማ እጅግ ክብርና ከፍተኛ ማዕረግ ይሆንልኝ ነበር። ነገር ግን ለእርውስዎ መሆን አልገባምና ይተዉኝ። ልቅርብዎ፤ እኔም የእዚህን አላፊ ክብር፣ የእዚህን አላፊ ዓለም ደስታ ተመልክቼ፤ ክርስቶስን ያላወቀና ያልተጠመቀ ንጉሥ ማግባት ክርስቶስን መክዳትና የዘለዓለሙን ሕይወታዊ ክብሬን መናቅ ይሆንብኛል፤ ስለዚህ እጄን ወደ እግዚአብሔር እዘረጋለሁ እንጂ ላልተጠመቀና ክርስቶስን ላላወቀ እጄን አልሰጥም፤ እንዲያውም በእውነቱ መሐላ አለብኝና አይሆንልኝም፤ አይዘኑብኝ። ትልቅ ውለታ ሰርተው እኛን ደስ ስላሰኙንና ወንድሜንም ከባርነት ስላወጡልኝ ወረታውን ቸሩ እግዚአብሔር ብቻ እንጂ ሰው ችሎ አይከፍልዎም። እርስዎ ባያውቁት ክርስቶስ ያውቅዎታልና ወረታዎን ይከፈልዎ” አለችና በመጨረሻው “ንጉሥ ሆይ! ካንዴ ሁለቴ ወደቤታችሁ በደኅና እንድትመለሱ አደርጋለሁ ብለው ቃል ሰጥተውን ነበር፤ አሁንም በሰጡን ቃል መሰረት ወዳገራችን ለመሄድ አንድነት ያሰናብቱን ዘንድ በትህትና እለምናለሁ” ስትል ጻፈች። ወረቀቱንም ሸሽጎ እንዲሰጥ አደራ ብላ ለዋሕድ አሳለፈችው።

ንጉሡ ነገሩ እንዳልተዋጠለት ባየ ጊዜ እጅግ ተከፋ፤ በግድ እንዳያገባት በግድ የሆነ ፍቅር፣ ትዳር እንዳይሆንና ንጉሥ የሆነ ሰው በገዛ ጉልበቱ ተመክቶ እንደወደደው ማድረግ እንዳይገባው ያውቃል። ባንድ ወገንም ሊለቃቸው ከጥንቱ ቃል ሰጥቷቸዋልና የንጉሥ ቃል የማይታጠፍ ሆኖ ቸገረው። ደግሞ እንዲያ ሲወድዳት ለቅቆ እንዳይሰዳት ለእርሱ ሞት መሰለው። የመሄድዋን ነገር ባሰበ ጊዜ ያንቀጠቅጠው፣ ያዝመው፣ ያብረከርከውና ያልበው ጀመር። በጦቢያ አንጻር መንግሥቱም ዘውዱም አጀቡም ሠራዊቱም ከንቱ ሆነበት። ከዓለም አልቆጥርህ አለው። ሁሉም ቀርቶበት ለጦቢያ ባል መሆኑን ብቻ ወደደ። በእርሷ ነገር ልቡ ተሸበረ፤ታመልጠኛለችን ሲያስብ ልቡ ባባ፣ ሆዱንም ይቆርጠው፣ ራሱንም ይፈልጠው ጀመር። ምን ያድርግ? ከሰው እንዳይነጋገር ታመምሁ ብሎ ተኛ። ከዋሕድ በቀር ከፊቱ ሰው እንዳይደርስ አደረገና ዝም ብሎ ያስብ ጀመር፤ አሳቡ ግን በከንቱ ነው። ጦቢያ ክርስቲያን ያልሆነ እንዳታገባ ማለች፤ ተከተተ ነገሩ። እርሱ ክርስቲያን ካልሆነ በቀር ሁሉም ቀረ ማለት ነው። አሳቡ በዚህ ቆመና “ዋሕድ ሂድ ከእኅትህ አይዞሽ ደስ ይበልሽ እንዳንችው ክርስቲያን ሆኜ አገባሻለሁና የሚጠምቀኝ ቄስ በሸሽግ አስፈልጊልኝ» ብሎ ላከባት። ጦቢያም ከእርስዋው ንግሥትነት ይልቅ በእርሷው ምክንያት ያን ያህል ትልቅ ያረመኔ ንጉሥ ክርስቲያን በመሆኑ ደስ አላትና “ይኸማ ከሆነ አማረ” አለች። እግዚአብሔርንም አመሰገነች።

ንጉሡ ግን ከዚህ ዕለት ጀምሮ ብልኅቱን ሳያስታውቅ ትልቅ ዓመት በዓል አለብኝ እያለ ያሳላ፣ ጠጁን ያስጥል፣ ጠላውን ያስጠምቅ፣ ፍሪዳውን ያሰበስብ፣ ሁለንተናውን ያሰናዳ ጀመር። ደግሞ ሌት ሌቱን በስውር ትልቅ የገዳም መምህር እየመጣ የሃይማኖትን ነገር፤ የጌታችን መውረድና መወለድ፤ መሞቱንም ያስተምረው ጀመር። የአጎቱንም ልጅ በጦቢያ አስመስሎ ከዋሕድ ለማጋባት "የወደድሽውን ጦቢያን እንዳጋባሽ ክርስቲያን ሁኚ እኔም የክርስቲያን ወገን ለማግባት ክርስቲያን መሆኔ ነው" ብሎ ነግሮአት አብራው ትማራለች። ንጉሡም፣ ያቺም ያጎቱ ልጅ የክርስቶስ ሃይማኖት/ትምህርት/ ገባቸው። ከዚህ ወዲያ ንጉሡ ውስጥ ለውስጥ በየመሣሪያው ሁሉ ላይ መስቀል ያስቀርጥበት ጀመር። ሶበድአት በነበረበት ሥፍራ፣ በሰንደቅ አላማው ሁሉ መስቀልና ሰፍነግ፣ ጦር፣ አክሊለ ሶክ ያስጠልፍበት ጀመር። በየነጋሪቱም በየመለከቱም በየጋሻውም ሁሉ ላይ የጣዖት ስም ነበረበትና ያንን እያስጠፋ የክርስቶስን ስም አስጻፈበት።

የሠርጉ መሰናዶ ባለቀ ጊዜ ከሠርጉ አንድ ቀን ቀደም ብሎ በመንፈቀ ሌሊት እርሱም የአጎቱም ልጅ በዚያ መምህር እጅ ተጠመቁ። ወዲያው ሳይነጋ በፊት በድንኳኑ ላይ መስቀል ያለበት ሰንደቅ ዓላማ አስተከለና የጥንቱን ከእሳት አስጨመረው። ወዲያው ጎሕ እንደቀደደ ወፍ ጭው ጭው ማለት ሲጀምር ከአደባባዩ ላይ የአዋጅ ነጋሪት ወጣና በግራና በቀኝ መስቀል የተለጠፈበት ዓላማ በንፋስ ሲውለበለብ ነጋሪቱ ይደበደብ ጀመር። ገና ሰዉ ከመኝታው አልተነሣም ነበርና ያ ሰንተል ነጋሪት እየቆየ እንደልማዱ ድዝ ድዝ ሲል በሰማ ጊዜ የአዋጁ ነጋሪ መሆኑን ዐወቀ። አዋጁን ለመስማት እየተቻኮለ ሰዉ ከእንቅልፉ ባንኖ እየተነሣ ዓይኑን በእጁ በአይበሉባው እያሻሸ ጨርሶም ያልለበሰ ልብሱን በአንደኛው እጁ ከምድር እየጎተተ አዋጁ እንዳያመልጠው እየተቀዳደመ ከግራና ከቀኝ ተሰበሰበ። በአንድ ጊዜ ሰዉ ከአደባባዩ ሣር ቅጠል ሆነና ይትበለበል ጀመር።

ንጉሡ በሩቁ ሁሉንም ሲመለከት ነበርና የሰውን መጠራቀም ባየ ጊዜ የአዋጅ ነጋሪውን አለቃ በወርቅ ለምድ፣ በወርቅ ጫማ፣ በወርቅ ዝናር፣ በሐር ቀሚስ፣ በአረንጓዴ ሱሪ አንቀልቅሎ ሽልሞ፤ በወርቅ የተሟሸ ዘንግ አሲዞ የአዋጁን ቃል ጽፎ ሰጥቶ ሰደደውና በአጀቡ ከአደባባዩ ደረሰ። በአዋጅ ነጋሪው ጀርባ አለፈና ሲቆም ጊዜው መድረሱን ለማስታወቅ ነጋሪት መቺው ምቱን ያፋጥን ጀመር። የአደባባዩም ሰው ምን ይሆን ሲል ለመስማት ይጋፋና ይንሸቀሸቅ ጀመር። ቃል እንዳያመልጠው አንዱ በአንዱ ላይ እየወጣ እየተዛለለ ጆሮውን አቁሞ ሲጠብቅ አዋጅ ጯሂው (አዋጅ ነጋሪው) ከትልቅ ደንጊያ ላይ ወጣና ፊት እንደልማዱ ሦስት ጊዜ

እየተንጠራራ «ስማ! ስማ! ስማ! መሰማሚያ ይንሣው የንጉሥን ጠላት” ብሎ እንደጨረሰ ዋናው አዋጅ እስነጋሪ ወረቀቱን እያነበበ ይመራው ጀመር። ቃሉም እንዲህ ይል ጀመር።

«ሠራዊቴ ሆይ! አገሬ ሆይ! ዓለምን ምድርን ሰውን አራዊትን እንስሳትንና በዚህ ዓለም ያለውን ፍጥረት ሁሉ አንድ አምላክ ብቻ ነው የፈጠረው፤ ሁለተኛ ፈጣሪ ከዚህ ቀደም አልነበረም። ለእንግዲህም አይመጣም። ይኸው አምላክ ብቻ ከዓለም በፊት እንደነበረ ዓለምንም አሳልፎ ይቀራል። በሦስትነቱ ስናምን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ እንላለን። በአንድነቱም በሦስትነቱም አንድ አምላክ መሆኑን እናምናለን።

«ይኸው አምላክ አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ እንዲወልዱ እንዲዋለዱ ዓለምን እንዲሞሉ አዘዘ። በዚህ ጊዜ እንኳን አዳምና ሔዋን አራዊቱ እንስሳቱ፣ አዕዋፉ አምላካቸውን ዐውቀው አመሰገኑ። ከብዙ ዘመን በኋላም ሰዉ ከመራባትና ዓለሙን ከመሙላቱ የተነሣ ቋንቋው በዝቶ እየራሱ ሆነ። እንደ ቋንቋውም ብዛት ሃይማኖቱም አምልኮቱም ተለወጠ። የእውነተኛውን አምላክ ረስቶ ለየራሱ ጣዖት አበጀ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር አብ አንድ ልጁን ‘ሂድ’ ብሎ ወደ ምድር ላከው። ይኸው ልጁ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ እንደእኛ ሰው ሆኖ አስተማረ፤ ተሰቀለ፣ ሞተ።

የእርሱ ተማሮች ሐዋሪያት የእርሱን ቃል እንዳስተማራቸው እየዞሩ አስተማሩ። እነእርሱ የደረሱበት አገር ወይም ቃላቸውን የሰማ ብርሃን ወጣለት፣ አመነ፤ የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል ዐወቀ፤ ክርስቲያን ሆነ፣ ተጠመቀ። የሐዋርያትን ቃል ያልሰማ እስከዛሬ ድረስ በጣዖት፣ በጅኒ፣ በኢጋንንት፣ በዛፍ፣ በገደል ያመልካል።

“እኔም ከአያት ከቅድም አያቴ በቆየኝ ድንቁርና ለጣዖት ስሰግድ ኖርሁ። አሁን ግን ክርስቶስ ልብ ሰጠኝ ከድንቁርና አወጣኝ፣ የእውነተኛውን ፈጣሪ እንዳውቅ አደረገኝ። የእውነተኛው ሃይማኖት የክርስቶስ ወገን መሆን ነውና የእኔ ሃይማኖት ነው ዕወቀው። እኔን የወደድህ እንደእኔ ተጠመቅ። እኔን ያልወደድህ ተለይ። ክርስቲያን መሆን የወደድህ ወደቀኝ፣ እንደጥንትህ መኖር ያደላብህ ወደ ግራ ሥፈር» አለና ጨረሰ።

ከዚህ አዋጅ ወዲያ ግራ ሠፋሪ ጠፋ፣ ሁሉም ወደመጠመቁ አደላ፤ ክርስቲያን መሆኑ ተረገጠ፤ ሁሉም አስቀድሞ እንዳወቀው ሆነና ረጋ። ንጉሡ ደስ አለው። “ብቻዬን እቀር ይሆን!” ሲል ይፈራ የነበረ ቃሉ እንደተዋጣለት ሃይማኖቱ

እንደተከበረለት ባየ ጊዜ ወዲያው፤ ክርስቲያን ይግዛ እንጂ አይገዛ” ብሎ ደነገገ። ከዚህ ሕግ የተነሳ በየአገሩ እንደ ባሪያ ተሸጦ የነበረ ክርስቲያን ሁሉ ከባርነት ወጣ።

ባንድ ነጋዴ ሰበብ ሁሉ ዳነ። ባንድ ሴት ምክንያት ሁሉ አመነ። ባንድ ንጉሥ ቃል ኢትዮጵያ ቆመ።

የሥርጉ ዳስ ተጣለ አቁልቋዩ ተዘረጋ ወጡ ተሠራ፣ ጠጁ ተሾመ። አረቄው ቀረበ ፍሪዳው፣ ሙክቱ ተጣለ ብርሌው፣ ብርጭቆው ተለቀለቀና ተደረደረ። ሁለንተናው ግጥም ብሎ ተሳላ። ንጉሡ አስቀድሞ የሚስቱን ጌጥ አሰናድቶ ነበርና ሰደደ። ድንኳኑ ለእርሱ ተብሎ የወርቅ ግምጃ ተመርጦ ተሰፍቶ በወርቅ ተጎብግቦ ነበርና ሄዶ ተተከለ። ዙሪያውን የደማስ ግምጃ አጥር ታጠረና ጦቢያ ገባች። የድኅነቷ ድንኳን ተነቀለ። በዙሪያው ዘበኛና ሽልሜ ታጠረበት። ደንገጡሩ እየተመረጠ ተሸልሞ ተሸልሞ ሄደና በዙሪያዋ ሠፈረ። ሺህ አቡሱዳ ሻንቅላ ለሰይፈ ጃግሬነት ሰይፋን በጁ እየሸፈነ ቀይ ኩፍታውን እያደረገ ሄደና ከዘበኛና ከሽልሜ መካከል ገባና ሠፈረ። የጦቢያ ሠፈር ለዓይን ይገረምም እንደ እሳት ይፋጅ ጀመር። ከዋናው ከንጉሡ ሠፈር የእርሷ ደመቀና እንደ መስከረም አበባ ተንቦገቦገ።

ይኸ ከሆነ ቀጥሎ ንጉሡ ዋሕድን ራስ ቢትወደድ አሰኝቶ ራስ ወርቅ አሠረለት። ሠፈሩም ለብቻው ተለየና ተገጠገጠ። ንጉሡም ሰው እንዲገባለት ጦሩም እንዲደነድን ብሎ የክርስቲያን አገር መኳንንት ተሻግሮ በዋሕድ እግር እንዲሠፍር አዋጅ አደረገና በአንድ ጊዜ ለፎው በዛለት።

ንጉሡም ዋሕድም በአንድነት ዕለቱን ለማግባት ተሰናዱ። ነገር ግን ያች የንጉሡ ዘመድ ገና የዋሕድንና የጦቢያን ነገር ሳታውቅ የሚያገባኝ ጦቢያ ነው ስትል ነበርና ከሥርጉ በፊት የምትለውን ለመስማት ንጉሡ ዋሕድን ለማሳየት ከአጎቱ ልጅ ዘንድ ወሰደው። እርሷም ዋሕድን ተሸልሞ አጊጦ ራስ ወርቅ አስሮ ባየችው ጊዜ ጥንቱንም ጦቢያ እንጂ ሌላ ሰው ነው ብላ አላወላወለችም። ብቻ ወዲያው እንዳየችው የፍቅር ናፍቆት እድሮባት ነበርና ደስ ብሏት ታለቅስ ጀመረች። አንድ ብቻ ቃል ያገኘችው ቀስ ብላ ባልተያየንባቸው ጥቂት ቀናት ውስጥ እንዴት ረዘመ ማለት ብቻ ነው። ንጉሡ ይኸን በሰማ ጊዜ “ስሙ ዋሕድ ይሁን ብያለሁና የባልሽ ስም እንደተለወጠ ዕወቂው። ዋሕድ ማለት አረመኔና አማራ አንድ ሆነ ማለት ነውና ስለዚህ ተለወጠ። የእርሱንም ስም ለእኔ ሚስት አድርጌዋለሁ” ብሎ ነገራት። እርሷ “እሺ መልካም ስም ነው፤ መልካም ትርጉም አለው” ብላ ደስ ብሏት ተቀበለች።

ሠርጉም ተሠረገ፤ ጋብቻቸው እስከልጅ ልጅ የደስታ ግቢ ሆነ፣ መንግሥቱም የጠና ሃይማኖቱም የበረታ ሆነ።

ዋሕድ ከዚህ በኋላ ነጋዴ ደብድቦ ጥሎት የሄደ ጊዜ አስታመው ያዳኑትን ሰዎች ልጅ ከተሸጠበት አስመጥቶ ስለ እናት አባቱ ወረታ የእርሱ እንደራሴ አድርጎ ሾመው

ንጉሡ ከዚህ ወዲያ ጦቢያን አገባና እንዲህ ብሎ ገጠመላት።

እንዷች ያለች ጽጌ ከወዴት በቀለች
እንዲያው መላከ ኑራ ከላይን ወረደች።
አላመል ተፈጥራ ሰውን አስጨነቀች።
እንኳን ወንዱንና ሴቱን አዘነጋች
ይኸም ሁሉ ሆኖ መኩራት አላሰበች።
ሳዱላዋን ትታ ጠጉሯን ተሸለተች።
ጠልሰሟን አውልቃ አጎዛ ደረበች
ሥጋጃዋን ንቃ አቃቅማ ረገጠች
ከዙፋኗ ወርዳ ተኮረብታ ወጣች።
እንኳን ለመዋረድ ለሞት ያልተገባች
ዓለም ሲሰግድላት በድንክ ተከሠሠች።
በምቀኛ ተንኮል ተልፍኝ ተሰደደች
ለወንድሟ ስትል በወንድ ተመሰለች
ዳሩ ግና ቢሆን ወንድ ሁናም አልቀረች
የሁለት አገር መንግሥት አንድነት ገጠመች።
እርሷ ጦር አትፈራም ከሰልፍ ትገባለች።
ይኸው ጀግና ቀድማ ንጉሡን ማረከች።
እንኳን ለወደዳት ባሏን ታኮራለች።
ጦቢያ ዞራ ዞራ ዘውድ አትርፋ ገባች።

ዝናብ እንዳጣ እህል
በበልግ የበቀለ
ባንቺ አፈጣጠር
ፍጥረት ነሆለለ

=

ተዪው አታቋጥሪው
ይነሁልል ፍጥረቱ
ባንቺው ተሰገደ ፍጥረት ሠራዊቱ።

አንድ ዐመል አገኘሁ
ከሥራ አካላትሽ
እግዜር የሠራውን
ልብ ማፈራረስሽ።

=

ምንም ወንጌል ብማር
ሃይማት ቢገባኝ።
ምን ቢሆን አላምንም
እንዳንች ያለ ሊገኝ።

=

ጦቢያ ለዚህ ግጥም እንዲህ ብላ ለንጉሡ ለባሏ ገጠመች

ይህ ሁሉ ወቀሳ
እንግዲህ ምን ባለች
እሴት ወተት ሳትል
ንጉሥ ማር ባገባች።

=

እልፍ አእላፍ አማራ ያስሸሸ የነበረ
ራስ ደጃዝማቹን ይወር የነበረ
ባለ ትልቁን ዘውድ ይሽር የነበረ
እንኳን ጦርና ሰይፍ መድፍ አይፈር የነበር
ወሬው ገና በሩቅ ያስረብድ የነበር
የገዳሙን በሬ ይሰብር የነበር
ጅቦና ሰንሰለት አይገታው የነበር
እጅግ አስገረመ በማተብ ሲታሰር።

=

እንኳን ሌላ ንጉሥ ባበሻ ያለው
በኢየሩሳሌምም መድፍ የሚሠራው
በሺህ ዓመት ውጊ ሊሽር አያቃጣው
ዛሬስ ይፈር ጀመር ይደናገረው
ገና ሙጫው ነግሦ ውጊያ ያልገባው።
ያንን ሁሉ ለፎ
ያንን ሁሉ ጀግና

ያንን ሁሉ ጦሩን
ያንን ሁሉ ሰልፉን በቄስ አስፈታው!

## ከእዚህ መጽሀፍ ውስጥ ጠጣር መስለው የታዩ ቃላትና ፍቻቸው፡-

### ለ

ለኮ – ከፋሎ ላይ የሚታሰር መሳቢያ

ለገተ-– ከአፍ አስጠጋ

ለጋ – ያልጠና፣ ጮርቃ

ለፎ – እግረኛ ወታደር

ሉል – የከበረ ድንጋይ

ላህይ – የገጽታ ወዝ

ላቀ – አንደኛው ከሌላው በለጠ

ልጥልጥ – በመወገጡ ተያይዞ የተሞለሞለ ኑግ

ሎሌ – ሠራተኛ፣ አገልጋይ

### መ

መልታሕት – ጉንጭ

መርግ – ናዳ

መሰገ – ጨመረ፣ አስቀመጠ፣ አደረገ

መቁነን – ድርሻ፣ ልክ

መተለገ – ራበ፣ ሞረሞረ

መንዶ – አጭር ወፍራም ዱላ

መከር – የደረሰ አዝመራ ወይም የደረሰ ሰብል

መደመደ – መደዳውን ከሥር ቆረጠ

መደብር – የነጋዴ ሠፈር (በአሁኑ ጊዜ ሱቅ)

መዳፍ – ማኸል እጅ

መጣምር – ከብር የሚሰራ የፈረስ ጌጥ

/የ/ሙያ ሠራተኛ – በጥሬ ገንዘብ ሳይሆን በእህል ዓይነት የቀን ሥራ የሚሠራ

ማገጥ – በክፉ ቀን የሚበላ የዳጉሣን ፍሬ የሚመስል የሚያፈራ የአክርማ ዓይነት ሣር

ምስባሕ – የእስላም መቁጠሪያ

ምሽግ – የማይደፈር ባለቅጥር ግቢ፣ እርድ

/ይኸን/ ምጣት – /ይኸን/ አመጣጥ

ምጥቀት – ወደ ሰማይ ያለው ርቀት ወይም ከፍታ፣ ወደ ሰማይ ያለው ውፅአት

ሞራ – ሆድ ዕቃን የሚሸፍን የቆዳ ሥር ስብ

## ረ

ረሞጫ – በፀሐይ ኃይል የጋለ፣ የቆላ የአሸዋ ሙቀት/እንደረመጥ የሚፋጅ/

ረጠበ – ረዳ፣ ራሰ፣ ረሰረሰ

ራስወርቅ – ልዩ ልዩ ሥራ ያለው መሳፍንት የሚሸልሙትና በራሳቸው ላይ የሚያሰፉት

## ሰ

ሰንተል – በትልቅ በዓል ቀን የሚመታ ትልቅ ነጋሪት

ሰከከ – አንገቱን መዝዞ አተኩሮ ተመለከተ።

ሰፍነግ – የባሕር አረንጓዴ የውኃ መጠጫ፣ ያዞ ከል፣ መራራ ቅል

ሳዱላ – ቃሬ፣ ልጅገረድ፣ በተለይ በባላገር ከማኸል ራስዋ ወደ ኋላ ሲል በትንሹ በክብነት የተላጨችው ሥፍራ

ሶበድአት – ከወገቡ በላይ ሰው ከወገቡ በታች ግን አውሬ የሆነ ሥዕል ምልክት

## ሸ

ሸጥ – ተረተር

ሻኍራ – ዘርፍ፣ መርገፍ፣ አጨዋች፣ ለምሳሌ የጥና ሻኍራ

ሻፎ – ሱፋጭ፣ ስል ጥቁር ደንጊያ

## ቀ

ቀላወጠ – በፍርሃት ሁናቴ ዓይኑን ግራና ቀኝ አንከራተተ

ቀረመት – ቅርጫ፣ የሥጋ ከፍያ

ቀነቀነ – አቀመቀመ /ለጢም/

ቀንበጥ – የለጋ ለጋ

ቅልጥም – ከጉልበት እስከ ቁርጭምጭሚት

ቅራት – የዛፍ ዓይነት

ቅናት – ቀበቶ

ቅጥር – ዕድሞ የግንብ አጥር

/ከመ/ቅጽበተዓይን — ወዲያው ያኔውኑ

ቋጫ — ጮጮ የስፌት አሆሌ

## በ

በልግ — በበጋ ዝናም የተዘራ አዝመራ

በነቻ — መጣምር

በሰንደል ኀጥር — ጥሩ ሽታ ካለው ከሰንደል እንጨት የተቀመመ ሽቱ

በጢኀ — በርጭቅ ዱባ

ቢተዋ — ማልደያ፣ አንባር፣ አንደዋጫ ያለ፣ ገዳይ በክንዱ ላይ የሚጢልቀው

ባለቀ — አደገ ከፍ አለ ጎረመሰ

/የ/ባሕር ዐረብ — ነት ዓይነት፣ የበግና የፍየል ቆዳ፣ ከውጭ አገር ይመጣ የነበር

ብርኩማ — ባለሶስት እግር ካንድ ግንድ የተጠረበ መቀመጫ፣ ትራስ

ብሶት — ችግር

ቧሂት — ወደ ሰማይ የሚነሣ አውሎ ነፋስ

## ተ

ተለቀለቀ — በብዛት ሠፈረ

ተለጠለጠ — ዧ ብሎ ተነጠፈ(ተዘረጋጋ)

ተረጠረጠ — በብዛት ተተከለ/ለድንኳን/

ተሳነ — አቃተ

ተራዳ — የድንኳን ምሰሶ

ተቀሠፈ — ተቀጠፈ፣ በድንገት ሞተ

ተሸወጠ — ተነሣሣ፣ ተቀሰቀሰ

ተትመከመከ — ተተላፈ፣ ወዲያና ወዲህ አለ

ተትበለበለ — ተርመሰመሰ

ተቸነነ — ኮራ፣ ተኮፋነነ

ተንሸቀሸቀ — ፈራ፣ ራደ፣ ተንቀጠቀጠ

ተንሽቃሸቀ — ተጫነቀ ተጠጋጋ አንዱ ባንዱ ላይ ሆነ።

ተከባከበ — በምቾት ያዘ

ተዛና — እንደልብ ሆነ፣ ያላሓሳብ ሆነ ተመቻቸ

ተደመመ — ተደነቀ፣ ተገረመ

ተዳፋት – መቆላቆያ

ተገተረ – ሳይነቃነቅ ቆመ

ተገደረ – ተጎዳ፣ የከፉ ሥራ ውጤት መጉዳቱን ያመለክታል። ተሸጠ ማለትም ይሆናል።

ተገጠገጠ – ትልቅ አዳራሽ ተሠራ፣ ግድግዳው ገረገራው እየተነባበረ ተገጠገጠ(ተሠራ)።

ተፈጠረቀ – ተከሰከሰ፣ ተገመሰ

ቱኪ – የጭቃ ሹም ወይም የዝቅተኛ ሹም ወኪል

## ነ

ነቀለ – መዘዘ፣ መለጠ፣ በኃይል አነሣ።

ነቻፈ – ቦጨቀ

ንክ- መጠነኛ ፍዝ ዓይነት እብድ፣ መቆምና ዝምታ የሚቢዛ

## አ

አሉማ – ቅጠሉ እንደጎመን ተቀቅሎ የሚበላ

/ከእምነበ/ አልቦ –ካለመኖር

አመዳይ – ግግር ውርጭ

አመናመነ – አወጣ አወረደ፣ አውጠነጠነ

/በ/አመይመጽእ –በምጽአት (ጌታችን በሚመጣበት ጊዜ)

አሚቀለ – በጎን አጠፈ

ዐምድ – የግንብ ቤቶችን እንደ ወጋግራ የሚሸከም

አሞራሞረ – አወጣ አወረደ፣ አውጠነጠነ

አሞጭ – የቅጠላቅጠል ሥር

አሜከላ – እሾህ

አስነቻፈ – አስቦጨቀ አወጣ/በዋጋ/

አሸነጠ – ታጠቀ

አሻኮረ – አሳብቆ አንድ ነገር ለማስደረግ ነገርን ጎንጎነ

አሽካፋ – አምራ ነቅታ

አሽኮኮ – ልጅን በትከሻ ላይ ማስቀመጥ

አቁማዳ – የጀግንነት ምልክት፣ በተለይ አዳል ይገድል ለነበረ የሚሰጥ

አቃቅማ – ኩርንችት
አቆልቋይ – ገበታ፣ ሰደቃ
አብራጃ – በራድ ሽውሽውታ /ነፋስ/
አተያይ – ገጽታ፣ የሚያመለክተው ሁኔታ
አንሆጫሆጨ – አቅጨለጨለ፣ አንሸዋሸዋ
እሞብርሌ – አንገቱ ሰንበር ያለው ብርሌ
እርድ – በቦይ መልክ የተቆፈረ የጉድጓድ አጥር፣ የቅመም ዓይነት
እነስድስቶም – ስድስቱ ኮከቦች
እንሶስላ – ጥፍር የሚያቀላ ቀለም፣ ግርሽጥ/የሐረግ ሥር/
እንቅብ – ከሦስት ቁና በላይ የማይዝ መሥፈሪያ
ዕድሞ – የግንብ ቅጥር
እድግ – ባንድ ርዳታ የዳነ
አንባር – በእጅ ወይም በክንድ ላይ የሚደረግ ቀለበታዊ ጌጥ /በማዕረግ ምልክት/
አንቧቀሰ – አዛጋ
አንከፈከፈ – አንቀጠቀጠ፣ አርገበገበ
አክሊለ ሶክ – ከእሾ የተዘጋጀ ዘውድ
አኮረሰ – አጎረበ
አንገራገረ – አስፈራራ
አንጣር – አቅጣጫ
አንፊላ ዝል ሥጋ – በፈላ ውኃ ውስጥ ጨውና ቅመም ተጨምሮበት እየተነከረ የሚበላ ዝል
አንፋሮ – የአንበሳ ጎፈር
አውተፈተፈ – አወሳሰበ/እንደወፍ/ ቤትን ሠራ
አዛመ – ከማንቀጥቀጥ አልፎ አርገፈገፈ/በንዳድ በሽታና በፍቅር ይነገራል/
አይበሉባ – የመዳፍ ጀርባ/ተቃራኒ/
አደናቆረ – አጭበረበረ፣ በማስመሰል ተፈላጊውን ነገር ሸፋፈነ
አደገደገ – አከሳ፣ አቧደነ(ልብሱን)
አዳ – በባላገር የአገሬው መንገድ
አጅባር – ትልቅ ድንኳን
አገር አማን ሲሆን – አገር ሲረጋጋ
/የ/አገር ቤት ጎናዴ – የአገር ቤት ሰው ወይም ባላገር

አገዘ – ረዳ
አጉድኖ – አሻርፎ
ኢጋሞ – አነስተኛ ባለእሾህ ግንድ የለሽ እንጨት
ኢጋፈፈ – ዘረፈ፣ ቀማ
አጎረበ – ለስላሳ እጅ ባልለመደው ሥራ አቆርብጮ ውኃን ቋጠረ
አጠነከረ – አጠበቀ፣ አመቻቸ
አፋቀ – ጎበዘ
አፍህን አካፍትሃለሁ – አነጋግርሃለሁ
አፎቄ – ጦር ነው ነገር ግን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በሰይፍ ሥራ ገብቷል።
ኢምንት – የሌለ
እህልገብ – በእህል ፈንታ የሚበላ ቅጠላቅጠል ወይም የሣር ፍሬ ሊሆን ይችላል።

## ከ

ከለቻ – እንደ ቡሽ ባርኔጣ ያለ የቀድሞ ወታደሮች የራስ ቁር
ኩራቢ – መደረቢያ፣ ያንገት ልብስ
ካፊር – ባረብኛ ከሐዲ ማለት ነው።
ክስል – እንደከሰል ጥቁር
ኮለኮለ – ርካብ ረግጦ ፈረስን ወይም በቅሎን መኮርኮር
ኮረምቱ – አፍላ ዝኖን/ጎረምሳ/
ኮደኮደ – አሰረ

## ወ

ወላንሳ – ለስላሳ ከቡር ምንጣፍ
ወረት – ሽቀጥ
ወሬሳ መታ – ወረረ ዘረፈ አገር አጠፋ
ወርቀ ዘቦ – ባለወርቅ ካባ
ወርቅ ኩፍታ – ፩- በራስ ላይ ኩፍ፣ ጉብ ብሎ የሚታሰር ጥምጥም
፪ – የራስ ላይ ቆብ
/ሕባኔ/ – የቤተ ክህነት ሻሽ
ወርድ – ጎን፣ ስፋት ዓርብ፣ ማዕዘን ላለው ነገር
ወዘላ – ቆንጆ፣ ሸጋ

ወደዚያው – ገረፉ ወደዚያው ጋለቡ።
ውርፍ – እጅግ በጣም አስቀያሚ ክልፍልፍ እግዜር የተቆጣው
ዋመነ – ቋመጠ፣ ጎመጀ

## ዘ

ዘተር ዱባ – ጥሬውን የሚበላ ጣፋጭ ዱባ፣ በጢጎ ወይም በርጭት ዱባ
ዘነፈጠ – ገነጠለ
ዛኒጋባ – በባላገር፣ በቤተ ክርስቲያን ወይም በማናቸውም አገር ቤት ታዛ፣ ከቅይድ ግቢ ያለው ሥፍራ

## ደ

ደረቅ ረፋድ – በጣም ሲረፍድ
ደሴት – በባሕር የተከበበች አገር
ደቃ – ደረት መታ የሚያሳዝን ወሬ ሲሰማ
ደቦል – ወዳቦ፣ በሦስትና በሰባት ዓመት መካከል ያለ ልጅ
ደነጎረ – ቀረቀረ ከተተ ጨመረ
ዲብ – ሰው ሠራሽ ከፍታ ቦታ የቀጣኖች መለያና ወይም የቀጣና አፈሮች ማገጃ
ዳሸ – ረጋገጠ
ዳባት – የሠርከ ብርሃን ደብዛዛ ብርሃን
ዳከረ – ሄደ /የድካም አካሄድ/

## ጀ

ጀንዲ – ጸጉር ያልተለየው ትልቅ ቁርበት

## ገ

ገልዳ – ገንዳ
ገመገመ – ገመተ፣ አበላለጠ (በሐሳብ ለካ)
ገረረ – ቆረፈደ፣ ደረቀ፣ ከረረ ጠነከረ(ለፀሀይ)
ገረመመ – ገላመጠ፣ በዓይን አስጠነቀቀ
ገርበብ – የገጠመ ነገርን እጅግ ጥቂት ከፈት ማድረግ
ገረገንብ – የግድንፍር ሥር

ገጠጠ – ፊት ነሣ

ጉር – ከናዳ የመጣ የደንጊያ ክምር የበዛበት ሥፍራ

ጉብጉብ – አንጥረኛ የሚሠራው ባለቅርጽ

ጉብር – እብጠት ወይም የእጅ መጅ

ጉዶ – አጭር ጎራዴ፣ አፏ ባላራት ስለት መሣሪያ

ግልብ – ሳያጥል በቁም የሚያሻግር ውኃ ቢከፍቱት ተልባ ወይም ምሥጢር የማይቋጥር

ግራር – ባለእሾህ ግንድ ያለው ዛፍ

ግፋን – ወደፊት

ጎመደ – ቆረጠ፣ ዋሸ፣ መታ አልፎ አልፎ በጎመድ የታሰረ ዱላ

## ጠ

ጣመነ – አመመ ደከመ

ጢሻ – ዳዋ፣ ያነስተኛ እንጨቶች ጫካ

ጣፋ – ከብርና ከኒኬል ተሰርቶ በጋሻ ላይ የሚለጠፍ ጌጥ

ጥብልያኮስ – ጥቁር ዲያቢሎስ

ጨ

ጫሜ – በጎራዴ ሰገባ ላይ የሚሰካ የብርና የወርቅ ጌጥ

ጮርቃ – ትንሽ ልጅ፣ ለጋ

## ጸ

ጽጌ- አበባ

## ፈ

/የ/ፋሲካ በግ – ለእርድ የቀረበ በግ ሌሎቹም እንደዚሁ በተለይ በፋሲካ ዕለት

ፋና – መብራት

ፋና ወጊ – መብራት ይዞ ቋሚ



## ስለደራሲው በጥቂቱ

ፕሮፌሰር አፈወርቅ ገ/ኢየሱስ በ1860 ዓ.ም ጎንደር ዘጌ በተሰኘችው ስፍራ ተወለዱ፡፡ የእቴጌ ጣይቱ ብጡል የሥጋ ዝምድና እንዳላቸው የሚነገርላቸው አፈወርቅ በልጅነት ዕድሜያቸው አዲስ አበባ መጥተው አደጉ።

ለዘመናዊት ኢትዮጵያ ሥልጣኔ መስራች የሆኑት ዳግማዊ አጤ ምኒሊክ ያውሮፓን ሥልጣኔ ቀስመው እንዲመጡ ወደውጭ ሀገር ከላኳቸው ብልህ ወጣቶች መካከል አንዱ አፈወርቅ ገ/ኢየሱስ ናቸው።

አፈወርቅ የ20 ዓመት ብላቴና ሳሉ በአጤ ምኒልክ በጎ ፈቃድ ከሁለት ወጣቶች ልጅ ጉግሳ ዳርጌ እና ልጅ ቅጣው ዛማኑኤል ጋር በ1880 ዓ.ም ወደ ስዊዘርላንድ ተላኩ። ከዚያ ከደረሱ በኋላ በገዛ ፈቃዳቸውና ባልታወቀ ምክንያት ወደ ጣሊያን ቱሪን ሄደው በኮሌጅ ኢንተርናሲዮናል ደ.ቤሊ አርቲ ከፍተኛ የሥነ ጽሑፍ ትምህርት ተከታተሉ። ከአድዋ ጦርነት በ1986 በፊት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በ1882 በቤተመንግስት ባለሟልነትና በሠዓሊነት ሙያ ያገለገሉት አፈወርቅ፥ በተለይ ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በመቀያየማቸው በ1888 ዓ.ም. በስደት መንፈስ ወደ ኢጣሊያ ተመለሱ። በናፖሊ የምስራቅ ጥናት ኢንስቲቲዩት የአማርኛ ቋንቋ በማስተማር የፕሮፌሰርነት ማእረግ አግኝተዋል።

አፈወርቅ በኢጣሊያ ሳሉ ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ሥነ ጽሁፍ ዕድገት የበኵር ልጅ ሊያሰኙዋቸው የቻሉትን የአማርኛ መጻሕፍት የጻፉ ሲሆን እንደገና ወደሀገራቸው በ1922 ዓ.ም. እስከተመለሱ ድረስ፥ በግእዝ፥ በአማርኛ፥ በኢጣሊያንኛ እና በፈረንሳይኛ ቋንቋዎች የመማሪያ መጻሕፍት፥ የታሪክ እና የፈጠራ ልቦለድ መጻሕፍትን አሳትመዋል።

አፈወርቅ በ1902 ዓ.ም. ሮማ ባሳተሙት ዳግማዊ ምኒሊክ በሚለው የታሪክ መጽሐፋቸው ከግዕዝ ጽሑፍ ባህል ወደ ዘመናዊ አማርኛ ኪናዊ ሥነጽሑፍ ለተደረገው ሽግግር በተለይ በ1908 ዓ.ም. በሮም ባሳተሟት ጦቢያ-ልቦለድ ታሪክ የፈጠራ ሥራቸው-በኢትዮጵያ የአማርኛ ዘመናዊ ሥነጽሑፍ መሥራች ካሰኛቸው

ማእረግ ባሻገር በአፍሪካ ቋንቋዎችም ታሪክ- በሀገርኛ ቋንቋ በመጻፍ የመጀመሪያው ጥቁር አፍሪካዊ የሚል ምስክርነት አግኝተዋል።

ቀደም ሲል ለሀገራቸው በአስተርጓሚነት፥ በጉምሩክ ሥራ ኃላፊነት ነጋድራስነት እና በአምባሳደርነት ሮም ያገለገሉት አፈወርቅ በኢትዮጵያና ኢጣሊያን ጦርነት ወቅት 1924 - 1933 ኢጣሊያን ወገን ሆነው በ የቄሣር መንግስት መልእክተኛነት በሀገራቸው ልዩ በደል ፈጽመዋል በሚል ከነፃነት በኋላ በ1933 የዕድሜ ልክ እሥራት ተፈርዶባቸው በጅማ ጅሬን እሥር ቤት ለ6 ዓመታት በግዞት ቆይተው፥ በእርጅና እና በጤና ማጣት መስከረም 15 ቀን 1939 ዓ.ም በ79 ዓመታቸው አረፉ።

**ምንጭ:** ብርሀነመስቀል ደጀኔ 2000ዓ.ም ብራና.ማ.ቤ ካሌንደር።

<u>የደራሲው ሥራዎች</u>

1. ጦቢያ(**ልብወለድ**)
2. ዳግማዊ አጤ ምኒልክ(**ታሪክ**)